

**የኮርፖሬት አደረጃጀትን ለሀገር ውስጥ ተቋራጮች** ገጽ 14



**ከትናንትናው እውነታ ...** ገጽ 16


# አዲስ ዘመን

አፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 280 ሰኔ 10 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# የመቀሌ ኢንዱስትሪ ፓርክ
## በቅርቡ ወደሥራ ይገባል

**ፋንታነሽ ክንዴ**




አዲስ አበባ፡- በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በነበረው ግጭት ምክንያት ሥራ አቁሞ የነበረውን መቀሌ ኢንዱስትሪ ፓርክ ወደ ሥራ ለማስገባት ሲደረጉ የቆዩ ዝግጅቶች መጠናቀቃቸውንና በቅርቡ ወደሥራ እንደሚገባ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ።

የኮርፖሬሽኑ ሥራ አስፈጻሚ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ፍፁም ከተማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የመቀሌ ኢንዱስትሪ ፓርክ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በነበረው ጦርነት ረዘም ላለ ጊዜ ሥራ አቋርጦ ቆይቷል። የፕሪቶሪያን የሰላም ስምምነት ተከትሎ በአካባቢው የነበረው ጦርነት በመቆሙና ሰላም በመስፈኑ ፓርኩን ወደ ሥራ ለማስገባት እንቅስቃሴ ሲደረግ መቆየቱን ጠቁመው፤ በአሁኑ ወቅትም ሲደረግ የቆየው ዝግጅት ተጠናቋል ብለዋል።

በኮርፖሬሽኑ የተቋቋመ ቡድን ቦታው ላይ ተደጋጋሚ ጉብኝት በማድረግ ነባራዊ ሁኔታውን የማየትና መሟላት ያለባቸውን ጉዳዮች በተመለከተ በኮርፖሬሽኑ ደረጃ ውይይቶች እንደተደረገበት ገልጸው፤ ጎን ለጎንም ፓርኩ ውስጥ መዋዕለ ንዋያቸውን ያፈሰሱ ባለሀብቶች ተመልሰው ሥራቸውን እንዲቀጥሉ የሚያስችሉ ውይይቶች ተደርገዋል፤ ባለሀብቶችም ደስተኛ ሆነው ሥራ


**የመቀሌ ኢንዱስትሪ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**




# የኢትዮጵያ
## አየር መንገድ 6 ነጥብ 1 ቢሊዮን ዶላር ገቢ አገኘ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ በበጀት ዓመቱ ስድስት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘቱን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚ


**የኢትዮጵያ አየር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**


# ለዓባይ ግድብ
## ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ ተሰበሰበ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በበጀት ዓመቱ አስር ወራት ለዓባይ ግድብ ግንባታ ከአንድ ቢሊዮን 188 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡን የግድቡ ብሔራዊ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት አስታወቀ፡፡ ግድቡ ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ እስከ ሚያዝያ ወር መጨረሻ የተሰበሰበው ጠቅላላ ገንዘብ ከ17 ቢሊዮን 971 ሚሊዮን ብር በላይ መሆኑ ተመላክቷል፡፡

የዓባይ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት የሚዲያ ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ኃይሉ አብርሃም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለህዳሴ ግድብ ግንባታው በበጀት ዓመቱ 10 ወራት አንድ ቢሊዮን 188


**ለዓባይ ግድብ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**



የሩዝ ሰብል

# በክልሉ ከ5 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የሩዝ ምርት ይጠበቃል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በመጪው የመኸር ምርት ዘመን ከአምስት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ሩዝ ለመሰብሰብ ማቀዱን የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡

በአማራ ክልል ግብርና ቢሮ የሰብል ዳይሬክተር አቶ አግደው ሞላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ክልሉ በመጪው የመኸር የምርት ዘመን ከአምናው የተሻለ የሩዝ ምርት ለማግኘት ከወዲሁ በትኩረት እየሠራ ይገኛል፡፡ ከመጪው የመኸር ምርት ዘመንም


**በክልሉ ከ5 ሚሊዮን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**




















ዶክተር ንጉሡ ስገሰ

## ድርጅቱ የተቋረጠውን የውጭ የሰብዓዊ ድጋፍ ግንኙነት ለመመለስ ተግዳሮት ገጥሞታል

**ታደሰ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የክርስቲያን የበጎ አድራጎትና ልማት ማህበራት ኅብረት ድርጅት ባለፈው ሥርዓት ያጋጠመውን የውጭ አገር የሰብዓዊ ድጋፍ መልሶ ለማግኘት ተግዳሮት እንደገጠመው አስታወቀ፡፡

የክርስቲያን በጎ አድራጎትና ልማት ማህበር ኅብረት ዳይሬክተር ዶክተር ንጉሡ ለገሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ድርጅቱ የቋቋመው የሰብዓዊ ድጋፍ ለመሥራት ቢሆንም ያለፈው ሥርዓት ከሰብዓዊ እርዳታ በአዋጅ ወደ ልማት ሥራ እንዲዞር በመደረጉ ከውጭ የሰብዓዊ ድጋፍ ከሚያቀርቡለት ድርጅቶች ጋር የነበረው ግንኙነት ተቋርጧል፡፡ የነበረውን ግንኙነት ለመመለስ ተግዳሮት ሆኖበታል፡፡

ድርጅቱ በለውጡ መንግሥት የተከለከለበት ረቂቅ አዋጅ ተነስቶለት የሰብዓዊ ድጋፍ ለዜጎች እንዲያቀርብ ቢደረግም፤ የነበረው ግንኙነት ለዓመታት በመቋረጡ ምክንያት አስፈላጊውን የሰብዓዊ ድጋፍ ለማድረግ መቸገሩን ተናግረዋል፡፡

ድርጅቱ በወሎ በደረሰው የድርቅ አደጋ በሰው ልጅ የሚደርሰውን ስቃይና ሰቆቃ በሰብዓዊ ድጋፍ ለማስቆም ታስቦ በዘመኑ በነበሩ የክርስቲያን የሃይማኖት አባቶች መመስረቱን አስታውሰው፤ ለተቸገሩ አርሶ አደሮች የተለያዩ እርዳታዎችን ሲያደርግ ለዓመታት ቢቆይም ባለፈው ሥርዓት የሰብዓዊ ድጋፍ ሥራውን ትቶ ወደ ልማት ሥራ እንዲሰማራ ተደርጓል፡፡

ይህ መደረጉ በስፋት ይገባ የነበረው የሰብዓዊ ድጋፍና ግንኙነት እንዲቋረጥ ሆኗል፤ መልሶ ለማጠናከር ትልቅ ተግዳሮት እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

ድርጅቱ ለዜጎች የተለያዩ መሠረተ ልማቶችን ለማኅበረሰቡ ተደራሽ እያደረገ እንደሚገኝ የጠቀሱት ዶክተር ንጉሡ፤ በአሁኑ ሰዓት ለዜጎች የተለያየ የሰብዓዊ ድጋፍ በማስፈለጉ ድጋፉን ለማሰባሰብ እየሠራ ነው፤ እየተሠራ ባለው ሥራም 15 ሚሊዮን ብር ተሰባስቧል ብለዋል፡፡

ሆኖም ከውጭ አገራት ጋር የነበረው የሰብዓዊ ድጋፍ ሥራ ግንኙነት መቋረጡ አሁን እየተሠራ ያለው የሰብዓዊ ድጋፍ ሥራ እንቅስቃሴ ተግዳሮት ሆኖበታል ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

የነበረውን ግንኙነት መልሶ የተለያየ የሰብዓዊ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች አስፈላጊውን የሰብዓዊ ድጋፍ ለማድረግ እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ድርጅቱ የተመሠረተበትን 50ኛ የምስረታ በዓል ከትናንት በስቲያ አክብሯል፡፡

# በሁመራ ከተማ ከዘጠኝ ሺህ በላይ ነዋሪዎች ለጎርፍ አደጋ ተጋላጭ ሆነዋል

## - ጉዳቱን ለመቀነስ 200 የሚሆኑ ቦዮች ጸድተዋል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮው ክረምት በሰቲት ሁመራ ዞን ሁመራ ከተማ ከዘጠኝ ሺህ በላይ የከተማው ነዋሪዎች ለከፍተኛ የጎርፍ አደጋ ተጋላጭ መሆናቸውን የሁመራ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ። የጎርፍ አደጋውን ጉዳት ለመቀነስም 200 የፍሳሽ ቦዮች መጽዳታቸውን አመልክተዋል።

የሁመራ ከተማ የመሠረተ ልማት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ደሳለኝ ፈለቀ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከተማዋ በክረምት ወቅት በተደጋጋሚ ለጎርፍ አደጋ ትጋለጣለች። በተለይ ከዘጠኝ ሺ. በላይ ነዋሪዎች ለከፍተኛ የጎርፍ አደጋ ተጋላጭ ናቸው።

ሁመራ ከተማ ከ37 ሺ. በላይ ሕዝብ የሚኖርባት ከተማ መሆኗን ገልጸው፤ ከዚህ ውስጥ ከዘጠኝ ሺህ በላይ ነዋሪ በከፍተኛ ደረጃ የጎርፍ ተጋላጭ መሆኑን ተናግረዋል።

ባለፉት ዓመታት የክረምት ወቅት በሁመራ ከተማ ነዋሪዎች ጎርፍ ወደ መኖሪያ ቤታቸውና ወደ ንግድ ሱቃቸው የሚገባ መሆኑን አውስተው ዘንድሮም ተመሳሳይ አደጋ እንዳይከሰት የጎርፍ አደጋ በሚያሰጋቸው የከተማው ክፍሎች የሚኖሩ ነዋሪዎች የሚበላሹ ቁሶችንና ሌሎች አስፈላጊ የቤት ዕቃዎቻቸውን ወደ ሌላ ቦታ አካባቢ ወስደው እንዲያስቀምጡ ማስጠንቀቂያ እንደሚሰጥም ገልጸዋል።

ይህንን ችግር በዘላቂነት ለመፍታትና በከፍተኛ የጎርፍ አደጋ ያጋጥማቸዋል ተብለው የተለዩ መኖሪያ ቤቶች ቢኖሩም ከተማዋ ካለባት የበጀት እጥረት የተነሳ ተተኪ መኖሪያ ቤት መስጠት አልቻለም ነው ያሉት። በዚህ ምክንያትም ችግሩን በዘላቂነት መፍታት አለመቻሉን ገልጸዋል።



ባለፉት ዓመታት በነበረው ጦርነትና በበጀት እጥረት ምክንያት የፍሳሽ ማስተላለፊያ ቦዮች ማጽዳት ባለመቻሉ በቆሻሻ ተደፍነው የቆዩ ቦዮች ለጎርፍ አደጋው ተደማሪ ችግር መሆናቸውን ገልጸው፤ በዚህም የከተማው ነዋሪ ለከፍተኛ የጎርፍ አደጋ ተጋላጭና ተጎጂ ቆይቷል ብለዋል።

እንደ አቶ ደሳለኝ ገለጻ፤ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የአካባቢውን ኅብረተሰብ በማስተባበር ጭምር ቦዮች እየጸዱ ናቸው። እስካሁን ድረስም 200 የሚሆኑ ቱቦዎች ፍሳሽን በደንብ ማስወገድ በሚችሉ መልኩ ማጽዳት ተችሏል።

ከተማዋ በወንዞች ዙሪያ መገኘቷና ተዳፋት መሆኗ ለጎርፍ አደጋ የበለጠ ተጋላጭ እንድትሆን አድርጓታል ያሉት አቶ ደሳለኝ፤ ይህንን ችግር ለመቅረፍም የወንዞችና የከተማዋ የተፋሰስ ሁኔታ መሻሻል በማስፈለጉም የወንዙን አቅጣጫ ማስቀየርና ግድብ መሰል የውሃ ማጠራቀሚያዎች በመሠራት ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል።

አቶ ደሳለኝ ችግሩ ሰፊ እንደመሆኑ እየተሠራ ያለው ሥራ በቂ አለመሆኑን ጠቁመው፤ በቀጣይም ከተማዋ ለጎርፍ አደጋ ተጋላጭ እንዳትሆን ለማድረግ ሰፊ ሥራን ይጠይቃል፤ ወደፊት በተቻለ መጠን ጊዜና ገንዘብ ተመድቦለት ችግሩን ለማቃለል ይሠራል ብለዋል።

# በአፍሪካ የሚከሰቱ ግጭቶችን በሠላማዊ መንገድ በመፍታት የተማሪዎችን እንግልት ማስቀረት ይገባል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በአፍሪካ የሚከሰቱ ግጭቶችን በሠላማዊ መንገድ በመፍታት የተማሪዎችን እንግልት ማስቀረት እንደሚገባ የአፍሪካ ተማሪዎች ኅብረት ገለጸ።

የአፍሪካ ተማሪዎች ቀን የተለያዩ አገራት ዲፕሎማቶችና የተማሪ ኅብረት ተወካዮች በተገኙበት በትናንትናው ዕለት ተከብሯል።

በመርሃ ግብሩ ላይ ንግግር ያደረገው የአፍሪካ ተማሪዎች ኅብረት ፕሬዚዳንት ኦሲሲጉ ኦስኬኚ፤ በአፍሪካ የሚከሰቱ ግጭቶችን በሠላማዊ መንገድ በመፍታት የተማሪዎችን እንግልት ማስቀረት እንደሚገባ ተናግሯል፡፡

በተለያዩ አፍሪካ አገራት ያሉ ተማሪዎች ሰለባ እየሆኑ በመሆኑ ግጭት ውስጥ ያሉ አካላት ከግጭት ወጥተው ተማሪዎችን እንዲታደጉ ጥሪ አቅርቧል።

ኢትዮጵያ ከነበረችበት ግጭት ለመውጣት የሄደችበት ርቀት ለሌሎች የአፍሪካ አገራት አርአያ ሆናለች ያለው ፕሬዚዳንቱ፤ አፍሪካውያን ተማሪዎች ለትምህርት ትኩረት በመስጠት በዓለም ተፅእኖ ፈጣሪ ሊሆኑ ይገባል ሲል አሳስቧል።



ኦሲሲጉ ኦስኬኚ

የመላው አፍሪካ ተማሪዎች ኅብረት ዓለምአቀፍ ግንኙነት ተወካይ አቶ አሊ. በዳኔ በበኩላቸው፤ ቀኑ ቀደም ሲል ዋጋ የከፈሉ ተማሪዎችን የምናስብበትና በአህጉራችን አፍሪካ ተማሪዎች ላይ የሚፈጸሙ በደሎችን ለማስቆም ድምጽ የምንሆንበት ቀን ነው ብለዋል።

በመርሃ ግብሩ የትምህርት ሚኒስቴርን በመወከል ንግግር ያደረጉት አቶ አብዱ ናስር በበኩላቸው፤ የመላው አፍሪካ ተማሪዎች ቀን በአገራችን መከበሩ ለምናስበው አህጉራዊና ዓለምአቀፍ ትብብር መንገድ የጠረገ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የአፍሪካ ወጣት ተማሪዎች ለትምህርት ጥራት ትኩረት ሊሰጡ ይገባል ያሉት ደግሞ በመርሃ ግብሩ በክብር እንግድነት በመገኘት ንግግር ያደረጉት የዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ሀብታሙ አበበ ናቸው፡፡

የአፍሪካ ተማሪዎች ኅብረት እ.አ.አ 1982 በአዲስ አበባ የተመሠረተ ድርጅት ነው፡፡

# በዞኑ ከአንድ ሺህ 500 ሄክታር በላይ በቆሎ እሸት ለመሸጥ ደርሷል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በወላይታ ዞን ከአንድ ሺህ 500 ሄክታር በላይ መሬት ላይ ያለ በቆሎ ለእሸት መድረሱን የዞኑ ግብርና መምሪያ አስታወቀ፡፡

የዞኑ ግብርና መምሪያ ምክትል ኃላፊና የእርሻ ዘርፍ ኃላፊ አቶ አሸናፊ ዓለሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በዞኑ ከአንድ ሺህ 500 ሄክታር በላይ በቆሎ ለእሸት ደርሷል፡፡ በዚህም እስካሁን ስምንት መቶ ሄክታር መሬት በቆሎ በእሸትነት ባለበት ደረጃ ተሸጧል፡፡

እንደ አቶ አሸናፊ ገለጻ፤ በበልግ እርሻ ልማት ሥራ ከ124 ሺህ ሄክታር መሬት በላይ በተለያዩ ሰብሎች ተሸፍኗል፡፡ በስፋት ከተዘሩት ሰብሎች አንዱ በቆሎ ነው፡፡

የበቆሎ ምርት አብቃይ በሆኑ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ወደ በቆሎ ምርት ሥራ ገብተዋል ያሉት ኃላፊው፤ አጠቃላይ በዞን ደረጃ 16 ሺህ ሄክታር መሬት በቆሎ ሰብል ተሸፍኗል ብለዋል፡፡

ከበቆሎ ሰብል ጋር ተያይዞ እርጥበት ያለባቸውና ቀደም ብለው ወደ በልግ እርሻ የገቡ አካባቢዎች መኖራቸውን ጠቅሰው፤ እነዚህ ስፍራዎች በቆሎ እሸትን ለገበያ የሚያቀርቡ አካባቢዎች ናቸው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ዳሞት ቱላንሳ፣ ዱጉና ፋንጎ እና በከፊል የዳሞት ጋሌ ወረዳዎች በበቆሎ ምርት የሚታወቁ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ በአካባቢዎቹ ከአራት ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በበቆሎ ምርት ተሸፍኗል፡፡ በዚህም እስካሁን ስምንት መቶ ሄክታር መሬት በቆሎ በእሸትነት መሸጡን አስረድተዋል፡፡

የበቆሎ እሸቱ አዲስ አበባን ጨምሮ ለተለያዩ ከተሞች እየቀረበና እየተሸጠ እንደሚገኝ የገለጹት አቶ አሸናፊ፤ አርሶ አደሮች የእሸት በቆሎ ወደ ገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ በመሆን ላይ ይገኛሉ ብለዋል፡፡

ግብርና መምሪያው አርሶ አደሩ በጊዜ ወደ ሥራ እንዲገቡ የግብርና ግብዓቶችን አስቀድሞ በማቅረብ ላይ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይም የተለያዩ የሞያ ክህሎት ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረጉን አቶ አሸናፊ ጠቁመዋል፡፡

ዘንድሮ እንደ አገር የግብዓት አቅርቦት እጥረት ማጋጠሙን የገለጹት አቶ አሸናፊ፤ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ችግሩን መፍታት መቻሉን ገልጸዋል፡፡

እሸት በቆሎ ወደ ገበያ በቀላሉ ማቅረብ እንዲችሉና የገበያ ትስስር እንዲፈጠር እየተሠራ ነው፡፡ በዚህም በበልግ እርሻው ከበቆሎ በተጨማሪ በጥራጥሬና በፍራፍሬ ሰብሎች ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አቶ አሸናፊ ገልጸዋል፡፡



አቶ መስፍን አበበ

# ባለፉት አስር ወራት ከወጪ ንግዱ 2 ነጥብ 9 ቢሊዮን ዶላር ተገኝቷል

**በዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት አስር ወራት ከወጪ ንግዱ 2 ነጥብ 9 ቢሊዮን ዶላር መገኘቱን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ክትትል ከሚያደርግባቸው ምርቶች 702 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘቱን አመልክቷል፡፡

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚኒስትሩ አማካሪ አቶ መስፍን አበበ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ባለፉት አስር ወራት ከወጪ ንግድ ሁለት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡

ከተገኘው አጠቃላይ የወጪ ንግድ ገቢ ግብርና 78 ነጥብ 26 በመቶ፣ ማኑፋክቸሪንግ 11 ነጥብ 76 በመቶ፣ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ 2 ነጥብ 62 በመቶ፣ ማዕድን 6 ነጥብ 41 በመቶ እንዲሁም ኤሌክትሪክና ሌሎች 3 ነጥብ 57 በመቶ ድርሻ እንዳላቸው ጠቅሰዋል፡፡

እንደ አማካሪው ገለጻ፤ በአገሪቱ በአስር ወራት አራት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ ሁለት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር ገቢ ነው የተገኘው፡፡ ይህም የወጪ ንግዱ አፈፃፀም 69 በመቶ ነው፡፡

በሌላ በኩል ሚኒስቴሩ ክትትል ከሚያደርግባቸው የወጪ ንግድ ምርቶች ማለትም የቅባት እህል፣ ጥራጥሬ፣ ጫት፣ የቁም እንስሳት፣ ቆዳ፣ እጣንና ሙጫ 702 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ባለፉት አስር ወራት በርካታ ተግባራትን ማከናወኑን ያመላከቱት አማካሪው፤ የግብይት ሥርዓቱንና የምርት አቅርቦትን የሚያሳልጡ አማራጭ አሠራሮችን መፍጠር መቻሉንም አመላክተዋል፡፡

የወጪ ንግዱን ለማሳደግም በውልና የኢንቨስትመንት እርሻ የለማ ምርት የግብይት መመሪያ እና የምርት ገበያ አሠራር ሥርዓት መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉንም ተናግረዋል፡፡

የወጪ ንግድ ምርት አቅርቦትን በመጠን እና በጥራት ለማሳደግ የአሠራር ሥርዓት የመዘርጋት እና የጫት ምርት የመላኪያ ዋጋ እንዲሻሻል የድጋፍና ክትትል ሥራዎች ተሠርተዋልም ሲሉ አማካሪው ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ በቅባትና ጥራጥሬ ላይ ከፍተኛ የሆነ ገቢ ማግኘት ብትችልም በጫትና በቁም እንስሳት ላይ ግን አገኛለሁ ብላ ያቀደችውን ያህል ማግኘት አልቻለችም ያሉት አማካሪው፤ ለገቢው መቀነስም ኮንትሮባንድ፣ አላስፈላጊ ቀረጥና በየክልሉ የተስፋፉ ሕገ ወጥ ኬላዎችን በምክንያትነት ጠቅሰዋል፡፡

# የሸገር ከተማን ዘመናዊና ለዜጎች ምቹ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን አስተዳደሩ አስታወቀ

## - የከተማ አስተዳደሩ ከተመሠረተ ወዲህ 7 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር ገቢ ተሰብስቧል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የሸገር ከተማን ዘመናዊ በማድረግ ለዜጎች ምቹና በምሥራቅ አፍሪካ ቀዳሚ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን የከተማ አስተዳደሩ አስታወቀ:: አስተዳደሩ ከተመሠረተበት ካለፉት አምስት ወራት ወዲህ 7 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር ገቢ መሰብሰብ መቻሉም ተገልጿል::

በሸገር ከተማ ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ናስር ሁሴን ከተማው ከተመሠረተ የተከናወኑ ተግባራትና ወደ ፊት አቅጣጫዎች ዙሪያ ትናንት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ እንደገለጹት፣ 2030 ሸገር ከተማ በምሥራቅ አፍሪካ በኢኮኖሚ የበለጸገች፣ በቴክኖሎጂ ያደገችና ለዜጎች ምቹ ከተማ እንድትሆን ታስቦ እየተሠራ ነው::

እንደ አቶ ናስር ገለጻ የሸገር ከተማን ስማርት ከተማ ለማድረግ ሰፊ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው::

ሸገር ከተማ ዘመናዊ፣ ሳቢና የልማት ማዕከል እንድትሆን ታስቦ የተመሠረተች መሆኑን ጠቁመው፤ በዚህም የዜጎችን ባህል በመያዝ እራሷን ችላ የምትቆም ከተማ ለመገንባት እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል::

ሰላምና መረጋጋት የሰፈነባት ከተማ ለመመስረት እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ናስር በተለይም ማራኪና የአካባቢ ብክለትን በመቀነስ ምሳሌ የምትሆን ለማድረግ ነው:: ይህም ለዜጎች ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያስችል ነው ብለዋል::

የከተማውን አርሶ አደሮች ተጠቃሚነትና ተሳታፊነት



አቶ ናስር ሁሴን

ለማረጋገጥ የተቋቋመ ከተማ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይም ዘመናዊ የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎችን ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ ነው:: ይህ ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ከተማ ለመሆን የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል::

ከተማ በፕላንና እቅድ መመራት ካልተቻለ ከተማ መሆን እንደማይችል በመግለጽ የመሬት ሀብትን ለማወቅና የዘርፉን ችግር ለመቅረፍ ሪፎርም ተካሂዷል:: በዚህም ዘመናዊ የሆነ የመሬት ማስረጃ አያያዝና ቆጠራን ዲጂታል ማድረግ ሰፊ ሥራ መሠራቱን ገልጸዋል::

የሸገር ከተማ የመሬት ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ሥራ ተሠርቷል ያሉት ኃላፊው ሕገ ወጥ የመሬት ወረራን ለማስቀረት በተደረገው ጥረት ወደ ሕግ አግባብ እንዲመለስ ተደርጓል:: በዚህም አራት ሺህ 51 ሄክታር መሬት ወደ መንግሥት ተመላሽ መደረጉን አስረድተዋል::

የሸገር ከተማ ተግባራት በፕላን ላይ የተመሠረተ እንዲሆን አቅጣጫ መቀመጡን ጠቅሰው፤ የከተማው የመሬት ፕላን ተሠርቶ ተጠናቋል:: በቀጣይ ፕላኑን ተግባራዊ ለማድረግ እየተሠራ ነው ብለዋል::

በከተማው የሥራ ዕድል ፈጠራ ከ62 ሺህ በላይ የሚሆኑ ወጣቶች ተጠቃሚ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ በሌላ በኩል በዘመናዊ ግብርና ዙሪያ 78 ሺህ ለሚሆኑ አርሶ አደሮች ሥልጠናዎችን መስጠት ተችሏል:: ይህም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚረዳ መሆኑን አስረድተዋል::

በከተማው ስምንት ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 7 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ተችሏል:: በቀጣይም የከተማውን ገቢ ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥራዎች በመሠራት ላይ ነው ብለዋል::

ከተማው በትምህርት፣ጤናና በተለያዩ ዘርፎች ላይ ሰፊ ሥራዎችን መሠራታቸውን ጠቅሰው፤ በመጪው ክረምት በጎ አድራጎት ተግባራት ተጠናክረው ይቀጥላሉ:: በተጨማሪም ከዘጠኝ ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል መታቀዱን አመላክተዋል::

# እንጉዳይ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ትልቅ ድርሻ አለው

**አዲሱ ገረመው**

ሆለታ፡- የእንጉዳይ ምርትን በስፋት ጥቅም ላይ በማዋል የአገሪቱን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ እንደሚገባ ተገለጸ:: ሁለተኛው ብሔራዊ የእንጉዳይ ቀን ተከብሯል::

በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ስር የሚገኘው የሆለታ ብሔራዊ ባዮቴክኖሎጂ ምርምር ማእከል ሁለተኛውን የእንጉዳይ ቀን ትናንት አክብሯል::

የሆለታ ብሔራዊ ባዮቴክኖሎጂ ምርምር ማእከል ዳይሬክተር ለታ ቱሉ (ዶ/ር) በመርሀ ግብሩ ባደረጉት ንግግር፣ እንጉዳይ ለምግብነትና ለጤና የጎላ ጠቀሜታ ያለው ቢሆንም፣ በመረጃ እጥረት ምክንያት እንደ አገር ለረጅም ጊዜ ትኩረት ሳያገኝ ቆይቷል::

ምርቱ ከሚሰጠው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አንጻር የምግብ ዋስትናን ሊያረጋግጥ የሚችል በመሆኑ በስፋት ጥቅም ላይ ሊውል ይገባል:: ለዚህም የግሉ ዘርፍ ተሳትፎና የመንግሥት ቁርጠኝነት ወሳኝ ድርሻ ከፍተኛ ነው::

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ የእንጉዳይ ምርት ከሌሎች የምግብ ሰብሎች የማይገኝ ልዩ ንጥረ ነገሮችን የያዘ ሲሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም ተፈላጊነቱ ከፍ ያለ ነው:: ከጤና አንጻር ከካንሰር፣ ከልብና ደም ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ በሽታዎችን የሚከላከልም ነው:: ይህንን ታሳቢ ያደረገ ግንዛቤ በሰፊው በመፍጠር በሚፈለገው ልክ ጥቅም ላይ ማዋል ይገባል::

እንደ መሠረታዊ የምግብ ሰብሎች በመጠቀም በአገር ደረጃ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥም ወሳኝነት ያለው ሥራ ነው ያሉት ዶክተር ለታ፤ በዚህ ረገድ የሆለታ ብሔራዊ ባዮቴክኖሎጂ ምርምር ማእከል የእንጉዳይን ዝርያ ከመለየት ጀምሮ በርካታ የምርምር ሥራዎችንና ሥልጠናዎችን እያከናወነ ይገኛል ብለዋል::

ማዕከሉ መሠረተ ልማቶችን በማሟላት፣ ላብራቶሪ በመገንባትና ተመራማሪዎችን በማሳተፍ ዘርፉ እንዲጠናከር በማድረግ ላይ እንዳለም ዳይሬክተሩ ገልጸዋል:: ወጣቶችን በማደራጀት፣ የሥራ ዕድል በማመቻቸትና የገበያ ትስስር በመፍጠር ኅብረተሰቡ



እንጉዳይን እንዲለምድ እያደረገ መሆኑንም ጠቅሰዋል::

የግብርና ምርምር ካውንስል የባዮቴክኖሎጂ አስተባባሪ መላኩ አለሙ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ እንጉዳይ በምርምር ደረጃ ቆየት ባሉ ጊዜያት ቢታወቅም አሁን ላይ በመቀዛቀዙ ዳግም ማነቃቃት እንደሚገባ ገልጸዋል:: አብዛኛው የእንጉዳይ ምርት ከውጭ እንደሚገባ ጠቅሰው፤ የአገር ውስጥ ዝርያን ከመጠቀም አኳያ ክፍተቶች እንዳሉም ተናግረዋል:: ምርቱን በጥናትና ምርምር በመደገፍ የምግብ ዋስትናን ሊያረጋግጥ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ መሥራት እንደሚገባም ተናግረዋል:: ይህንን እውን ለማድረግም መንግሥት በበጀትና በሰው ኃይል መደገፍ እንዳለበት፤ ኅብረተሰቡም የአመጋገብ ባህሉን በማሳደግ እንጉዳይን እንደ አማራጭ ምግብ መጠቀም እንዳለበት አመላክተዋል::

እንጉዳይን በሰፊው ጥቅም ላይ ለማዋል ብሔራዊ ባዮቴክኖሎጂ ምርምር ማእከል ላለፉት ሁለት አመታት በዘርፉ በርካታ የምርምር ሥራዎችን ሲሠራና ስልጠና ሲሰጥ መቆየቱንም ጠቅሰዋል:: ዘርፉን ለማሳደግ የእንጉዳይ ምርምር ስልጠና ቤተሙከራ መገንባቱን በመግለጽ፣ በተለያዩ የምርምር ሥራዎች አበረታች ውጤቶች እየተገኙ እንደሆነ ጠቁመዋል::

እንጉዳይ ከምግብነት ባሻገር በሥራ ዕድል ፈጠራ ትልቅ ገቢ እንደሚያስገኝና ማዕከሉ ለተጠቃሚዎች መረጃን ከመስጠት ጀምሮ እንጉዳይ በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ በትኩረት እንደሚሠራ ገልጸዋል::

ዕለቱን አስመልክቶ፣ በእንጉዳይ ዙሪያ የተዘጋጀ መጽሐፍ ምረቃና ኤግዚቢሽን ተካሂዷል::

ዜና




# የጃፓን መንግሥት በጦርነት ለተጎዱ አካባቢዎች የስምንት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ አደረገ

ኢዩኤል ክፍሉ

አዲስ አበባ፡- የጃፓን መንግሥት በሰሜኑ ጦርነት የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ለማቋቋም የሚውል ስምንት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ አደረገ።

በኢትዮጵያ የጃፓን አምባሳደር ኢቶ ታካኮ እና በዩኒሴፍ (UNICEF)የኢትዮጵያ ተወካይ አቡበከር ካምፖ (ዶክተር) የድጋፍ ስምምነቱን በትናንትናው ዕለት ፈርመዋል።

የድጋፍ ስምምነቱ በአማራ እና ትግራይ ክልሎች የሚኖሩ ማኅበረሰቦችን በተሻለ ኑሮ፣ የጤና እና የማህበረሰቡ ደህንነት በሚሻሻሉባቸው ዙሪያ እንደሆነ በወቅቱ ተገልጿል።

አምባሳደር ኢቶ የድጋፍ ስምምነት በፈረሙበት ወቅት እንደተናገሩት፣ ድጋፉ በአማራ እና ትግራይ ክልሎች በጦርነቱ ለተጎዱ ትምህርት ቤቶች፣ ለትምህርት ቤቶች የውሃ አቅርቦት እና የንፅህና መጠበቂያ የሚውል መሆኑን ገልፀዋል።

አምባሳደሯ ለወደፊት አገሪቷ ላይ ተጽእኖ የሚፈጥሩ ሕፃናትን ለማፍራት የተሻለ የትምህርት አካባቢን መፍጠር እና ክህሎታቸውን ማዳበር ወሳኝ ነው ያሉ ሲሆን በዚህም ፕሮጀክቱ 17 ትምህርት ቤቶችን መልሶ ለማቋቋም ተደራሽ ይሆናል ብለዋል።

አምባሳደር ኢቶ አክለው እንዳስታወቁት፤ በሦስት አመታት ውስጥ ተፈፃሚ በሚሆነው ፕሮጀክት ወደ 12 ሺህ ለሚጠጉ ተማሪዎች እና 47 ሺህ ሰባት መቶ ለሚጠጉ ነዋሪዎች የትምህርት እና መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለመስጠት ያለመ ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ የዩኒሴፍ (UNICEF) ተወካይ አቡበከር ካምፖ (ዶክተር) በበኩላቸው በማንኛውም ጊዜ ግጭቶች ሲፈጠሩ በቅድሚያ ሕፃናት ለጥቃት የተጋለጡ ናቸው ያሉ ሲሆን በዚህም ትምህርታቸውን ለማቋረጥ የሚገደዱ መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ ዶክተር አቡበከር ካምፖ ገለጻ፤ የተደረገው ድጋፍ የትምህርትና የውሃ አቅርቦትን ወደነበረበት ለመመለስ እንዲሁም ከትምህርት ገበታቸው ለወጡ ሕፃናት ወደ ቀድሞ ሁኔታቸው እንዲመለሱ ይረዳል።

በሰሜኑ ግጭት በአጠቃላይ ከአራት ሺህ ስድስት መቶ በላይ በአማራ ክልል የሚገኙ ትምህርት ቤቶች እና ሁለት ሺህ የሚጠጉ በትግራይ ክልል የሚገኙ ትምህርት ቤቶች በከፊልና በሙሉ ጉዳት ደርሶባቸዋል ያሉት ዶክተር ሞሪሃራ፤ ከሰባት መቶ ሺህ በላይ ሕፃናት ከትምህርት ገበታ ውጪ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ዶክተር አቡበከር ካምፖ አክለውም፤ የተደረገው ድጋፍ 12 ሺህ ሕፃናትንና 48 ሺህ የማኅበረሰብ ክፍሎችን የትምህርት ተደራሽነት እና መሠረታዊ ፍላጎቶችን ተደራሽ ለማድረግ ያግዛል ብለዋል።

## የኢትዮጵያ አየር መንገድ 6 ነጥብ 1 ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

አቶ መስፍን ጣሰው እንደተናገሩት፤ በበጀት ዓመቱ የዓለም ኢኮኖሚ ዕድገት መቀዛቀዝ፣ የሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት እና የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ የፈጠሩት ተፅዕኖ ለአቪዬሽን ዘርፉ ትልቅ ፈተና ሆነው ቆይተዋል፡፡ ሆኖም አየር መንገዱ ያጋጠሙትን ፈተናዎች በመቋቋም እየተገባደደ በሚገኘው በጀት ዓመት ስድስት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ዶላር ገቢ አግኝቷል፡፡

ይህ የአየር መንገዱ አፈጻጸም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸርም የ20 በመቶ ብልጫ ማሳየቱንም ዋና ሥራ አስፈጻሚው ጠቁመዋል።

በዘርፉ ላይ ተግዳሮቶች ቢያጋጥሙም እነዚህን ፈተናዎች በመቋቋም አየር መንገዱ 13 ነጥብ 7 ሚሊዮን መንገደኞችን እና 723ሺህ ቶን ጭነት በማጓጓዝ የተሻለ ገቢ ለማግኘት ችሏል ያሉት አቶ መስፍን፤ አፈጻጸሙ ከእድገትና ስትራቴጂው ጋር የተጣጣመ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

አየር መንገዱ በበጀት ዓመቱ 11 አዳዲስ የመንገደኞች አውሮፕላኖችን በመግዛት አጠቃላይ የአውሮፕላኖቹን ቁጥሮቹን ከ140 በላይ ማሳደጉን አቶ መስፍን ገልጸው፤ እንዲሁም ሁለት የመንገደኞችን አውሮፕላን ወደ ጭነት አውሮፕላኖች በመቀየር በበጀት ዓመቱ ያሉትን የጭነት አውሮፕላኖች ቁጥር ወደ 15 ከፍ ማድረግ መቻሉን አብራርተዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በበጀት ዓመቱ ከኮቪድ ወረርሽኝ በኋላ ዳግም ካስጀመራቸው በረራዎች በተጨማሪ ኮፐንሃገን፣ አትላንታ እና ካራቺን ጨምሮ ሰባት አዳዲስ የመዳረሻ ጣቢያ መክፈቱን ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በ125 የመንገደኞች መዳረሻዎች ኔትወርክ ሆኖ እያገለገለ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 20ዎቹ የአገር ውስጥ እና 44 የጭነት ማመላለሻ መዳረሻዎች ናቸው።

አየር መንገዱ በቶጎ እና በማላዊ ሁለተኛ ደረጃ ማዕከሎች ያሉት ሲሆን በተጓዦች፣ በመዳረሻዎች ብዛት እና በገቢ በአፍሪካ ትልቁ አየር መንገድ ነው።

## ለዓባይ ግድብ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ሚሊዮን 957 ሺህ 606 ብር ተሰብስቧል፡፡

ገቢው የተሰበሰበው ከአገር ውስጥና ከውጭ አገራት ቦንድ ሽያጭ፣ ከ8100 አጭር የጽሑፍ መልዕክት እና ከልዩ ልዩ ገቢዎች መሆኑን የጠቆሙት አቶ ኃይሉ፤ ከአገር ውስጥ ቦንድ ሽያጭና ስጦታ ከ920 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡን ገልጸዋል፡፡

ከዲያስፖራ ቦንድ ሽያጭና ስጦታ ከ35 ሚሊዮን ብር በላይ እንዲሁም በኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል የስጦታ አካውንት ከ111 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ተገኝቷል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ከአጭር የሞባይል መልዕክት አገልግሎት በ8100 ከ122 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡን ጠቅሰዋል፡፡

በዘንድሮው በጀት ዓመት አስር ወራት ለዓባይ ግድብ የተሰበሰበው ጠቅላላ ገንዘብ ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በተወሰነ መጠን መጨመሩን ጠቁመዋል፡፡

የዓባይ ግድብ ከተጀመረበት መጋቢት 2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 2015 ዓ.ም በአገር ውስጥና ውጭ ካሉ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የተሰበሰበው ጠቅላላ ገንዘብ ከ17 ቢሊዮን 971 ሚሊዮን ብር በላይ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የተሰበሰበው ጠቅላላ ገቢ ከአገር ውስጥ ቦንድ ሽያጭና ስጦታ ከ15 ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር በላይ፣ ከዲያስፖራ ቦንድ ሽያጭና ስጦታ አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በላይ እና ከልዩ ልዩ ገቢዎች ከ777 ሚሊዮን ብር በላይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

## የመቀሌ ኢንዱስትሪ ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ለመጀመር ዝግጅታቸውን በማጠናቀቅ ላይ ናቸው ብለዋል::

በተጨማሪም የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ከመቀሌ ከተማ አስተዳደርና በክልልም ደረጃ ፓርኩን ሥራ ለማስጀመር በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ሁሉን አቀፍ ውይይት ተደርጓል ያሉት አቶ ፍፁም፤ ባለሀብቶች ወደ ሥራ የሚገቡበት ሙሉ ዝግጅት መደረጉንም ጨምረው ገልጸዋል::

በተደረገው የዳሰሳ ጥናት በፓርኩም ሆነ በባለሀብቶች ንብረት ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት እንዳልደረሰበት ያመለከቱት አቶ ፍፁም፤ ይህም ፓርኩን ወደ ሥራ ለመመለስና ባለሀብቶችም በቀላሉ ተመልሰው ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ለማድረግ ትልቅ አቅም ይፈጥራል ብለዋል::

እንደ ጽሕፈት ቤት ኃላፊው ገለጻ፤ የፓርኩ ወደ ሥራ መመለስ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት፣ የእውቀት ሽግግር ለማድረግና አካባቢው ላይ ተፈጥሮ በነበረው አለመረጋጋት ያጋጠመውን የኢኮኖሚ መዳከም ለማነቃቃት ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል::

ኮርፖሬሽኑ ሙሉ ትኩረቱን መቀሌ ኢንዱስትሪ ፓርክ ላይ አድርጎ ቀደም ሲል በፓርኩ ተፈጥሮ የነበረውን የሥራ ዕድልና የውጭ ምንዛሪ ግኝት ወደነበረበት ለመመለስ ርብርብ እየተደረገ መሆኑንም ጠቅሰዋል::

## በክልሉ ከ5 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የሩዝ ምርት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ከአምስት ሚሊዮን ኩንታል በላይ የሩዝ ምርት ለማግኘት ታቅዷል፡፡

በክልሉ ባለፈው የመኸር የምርት ዘመን 61ሺ ሄክታር መሬት በሩዝ ልማት መሸፈኑን አስታውሰው፤ ከዚህም በቅድመ ምርት ትንበያ መሠረትም ከሦስት ሚሊዮን በላይ ኩንታል የሩዝ ምርት መሰብሰቡን ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ አግደው ገልጻ፤ ክልሉ በመጪው የመኸር የምርት ዘመን ከ100 ሺ ሄክታር በላይ መሬት በሩዝ ምርት ለማልማት እቅድ ይዟል፡፡ በአንድ ሄክታር 52 ኩንታል ምርት እንደሚገኝ የሚገመት ሲሆን በአጠቃላይም ከአምስት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ ዝግጅት ሥራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

ዕቅዱን ለማሳካትም የዝግጅት ሥራዎች ተሠርተዋል ያሉት አቶ አግደው፤ ክልሉ ሩዝ የማልማት አቅም በአግባቡ ለመጠቀምም ለአስፈጻሚዎች ሥልጠና በመስጠትና አጠቃላይ ክልላዊ የንቅናቄ መድረክ በማካሄድ ዕቅዱን ለማስፈጸም የሚያስችሉ ተግባራት በመከናወን ላይ ናቸው ብለዋል፡፡

ከ42 ሺ ሄክታር በላይ መሬት በሩዝ የሚለማው ደቡብ ጎንደር ዞን መሆኑን ጠቁመው፤ ቀሪው58ሺ ሄክታር መሬት ምዕራብ ጎጃም፣ ምዕራብ ጎንደር፣ አዊ ብሔረሰብ ዞን፣ ማዕከላዊ ጎንደር እና በሌሎችም ዞኖች የሚለማ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ አግደው ገለጻ፤ የሚለማው ሩዝ ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚውል ነው፡፡ ይህም ኢትዮጵያ ሩዝ ለማስገባት የምታወጣውን የውጭ ምንዛሬ ይቀንሳል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በክልሉ የሩዝ መፈልፈያ መሣሪያ አቅርቦት ውስንነት፣ ከበሽታ ነፃ የሆነ የዝርያ አቅርቦት እጦት፣ ማዳበሪያና የመሰል ግብአቶች እጥረት በሩዝ ምርታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ መፍጠሩን ዳይሬክተሩ ጠቅሰው፤ እነዚህ ችግሮች ከተፈቱ ክልሉ ሩዝን የማልማት አቅሙ ከፍተኛ ነው ብለዋል፡፡

እስካሁን ባለው መረጃም የአማራ ክልል በሩዝ ምርት 63 በመቶ አገራዊ ድርሻ እንዳለው ታውቋል፡፡

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ውሃችን ነዳጃችን ነው››

- አቶ አበራ እንዳሻው

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ከፍተኛ አማካሪና የውጭ ጉዳዮች ኃላፊ

አስቴር ኤልያስ

**የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በማናጅመንት፣ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ደግሞ በማኅበረሰብ ሳይንስ ይዘዋል። የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን እንደያዙ ስራ የጀመሩት በውሃ ዘርፍ ላይ ነው። በእርግጥ ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ሳለፉት 17 ዓመታት ያህል በዚሁ በውሃ ዘርፍ ላይ ሲሰሩ ቆይተዋል - የዛሬው የዘመን እንግዳችን የውሃና መስኖ ሚኒስትር ከፍተኛ አማካሪና የውጭ ጉዳዮች ኃላፊው አቶ አበራ እንዳሻው።**

**አቶ አበራ፣ ገና ከዩኒቨርሲቲ እንደተመረቁ በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥረው ባይሰሩም፤ ለ14 ዓመታት ያህል ግን በተለያዩ መንግስታዊ ባልሆኑ ዓለም አቀፍ ተቋማት ውስጥ በውሃው ዘርፍ አገልግለዋል። ወደውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት የመጡት ከ14 ዓመታት አገልግሎት በኋላ ሲሆን፣ በመጀመሪያ ሲያማክሩ የቆዩት የቀድሞውን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዶክተር ስለሺ በቀለን ነበር።**

**እኚህ የዛሬው እንግዳችን በተለያየ የስራ አጋጣሚ በተለይ ከውሃ ጋር በተያያዘ ጉዳይ የብዙ አገሮችን ተሞክሮ ለማየት እድሉን አግኝተዋል። በአንድ መንግስታዊ ድርጅት ውስጥ የሰራ አንድ ሰው የሚያከናውነው ተግባር ለአንድ አገር ብቻ ሳይሆን ለብዙዎች እንደመሆኑ እርሳቸውም ከዚሁ የተነሳ በዘርፉ ያለውን የብዙ አገሮች ተሞክሮ ለማየትና ለመቅሰም ችለዋል።**

**በተለየያዩ መንግስታዊ ባልሆኑ ዓለም አቀፍ ተቋማት መስራታቸው እድሉን እንዲያገኙ አግዟቸዋል። አህጉር አቀፍ ተሞክሮዎችንም የመቅሰም እድል ያገኙም ሰው ናቸው። የዓለም አቀፍ የውሃ ጉባኤም ሆነ በሌላው የውሃ ጉባኤ መሳተፍም ችለዋል። የዛሬው እንግዳችን በውሃ ዘርፉ ላይ የካበተ ልምድ ያላቸው በመሆኑ አዲስ ዘመን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን የሚመለከቱ የውጭ ጉዳዮችን ከተለያዩ ኤምባሲዎች፣ ከአጋሮችና ከሌሎች የልማት ፕሮግራም አጋሮች ጋር ያሉ ግንኙነቶችን በዋናነት ሚኒስተሩን ከሚያማክሩ ከእኚሁ ከአቶ አበራ እንዳሻው ጋር ያደረገውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርቧል።**

**አዲስ ዘመን፡- ብዙዎች ኢትዮጵያን ‹‹የውሃ ማማ ናት›› ይሏታል፤ በዚህ ሐሳብ ይስማማሉ?**

**አቶ አበራ፡-** በእርግጥ ከዚህ ቀደም በነበሩት የጥናት ውጤቶችና መሬት ላይ ያሉት ጠቋሚ መረጃዎች በሚያሳዩት መሰረት ኢትዮጵያ የውሃ ማማ ናት ሊባል ይችላል። ለምሳሌ አንዱ ማሳያ ወሰን ተሻጋሪ ወንዝ ያሏት መሆኑና ከእነዚህም መካከል በሙሉ አቅማቸው የሚፈሱ ትልልቅ ወንዞች በመሆናቸው ነው። ከዚህ በተጨማሪ የከርሰ ምድርና የገጸ ምድር ውሃም ሌላው ማሳያ ነው።

ይሁንና ‹‹የውሃ ማማ ናት›› የምንለው በንጽጽር ነው። ለምሳሌ ከምስራቅ አፍሪካ አገራት ከሱዳን ወይም ከግብጽ አሊያም ከጅቡቲ ወይም ከኬንያ አንጻር ስናይ ነው እንጂ ከሌሎች ሀገራት አንጻር ‹‹ኢትዮጵያ የውሃ ማማ ናት›› የሚለውን ለመጠቀም በአሁን ወቅት ይከብዳል። ምክንያቱም አንዳንድ የሩቅ ምስራቅ አገራትን ስናይ በአብዛኛው በውሃ የተከበቡ አገራት ናቸውና ከዛ አንጻር እኛ ምን ያህል የውሃ ማማ ነን ብለን እንናገራለን የሚለው መጤን ያለበት ነው።

ሌላው ከዚህ ቀደም የነበሩ አስተምህሮዎች ‹‹ኢትዮጵያ የውሃ ማማ ናት›› የሚለውን አባባል ያሰረጹት ይመስለኛል። ለምሳሌ ‹‹ኢትዮጵያ የአፍሪካ የውሃ ማማ ናት›› ሲባል እውነት ውሃው አለን ወይ የሚለው ነገር አጠያያቂ ነው፤ ይህ እውነት ስለመሆኑ ጥናት ተጠንቶ ግኝቱ ይፋ የሆነው መቼ ነው። ከዛ በኋላስ ምን ሆነ፤ ከነበረው ውሃስ በትነትም ሆነ በአገልግሎት ምን ያህሉ ሔደ፤ የሚለው መፈተሽ አለበት። ከዚህ አኳያ እኛ አንድን ነገር በመፈተሽ ረገድ ብዙም ብርቱ አይደለንም። ከዚህ ጎን ለጎን የአቅም ውስንነቱም አለብን።

ካለፉት ከሃያና ሰላሳ ዓመታት በፊት እንደነበረው ሁሉ ዛሬም ‹‹የውሃ ማማ ነን›› ካልን ልንሆን አንችልም፤ ሌላውን ትተነው አሁን ባለው ሁኔታ ያሉን ወንዞች ወቅታዊ ናቸው። ወንዞቻችን የፍሰት መጠናቸውም ሆነ የፍሰት ጊዜያቸው እየቀነሰ ነው። ከዚህ አንጻር እኔ ‹‹የውሃ ማማ ነን›› ብዬ ለመናገር አልደፍርም። ስለዚህ በአሁን ወቅት ‹‹የውሃ ማማ ነን›› የሚለው አባባል አያስኬድም። እንዲያውም ወንዞች እየነጠፉ ባለበት በዚህ ጊዜ ‹‹የውሃ ማማ ነን›› ማለት ራስን እንደማሞኘት እመለከተዋለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- በቀጣዮቹ ጊዜያት ጦር ሊያማዝዝ የሚችለው አንገብጋቢ ጉዳይ ነዳጅ ሳይሆን ውሃ ነው ይባላል፤ ኢትዮጵያ ከዚህ አንጻር ያላት እድል ምንድን ነው?**

**አቶ አበራ፡-** ይህ አባባል ትክክል ነው። ለምሳሌ በአገራችን ብቻ ያለውን አንድ ምሳሌ ላንሳ፤ 17ቱ ዘላቂ የልማት ግቦች ተብለው የታቀዱ ስራዎች አሉን። በዘላቂ የልማት ግቦች ውስጥ ከሚካተቱት መካከል የምግብን ዋስትና፣ ጤና፣ ትምህርት፣ ኃይል እና ሌሎችም ይገኙበታል። እነዚህ ሁሉ ትስስራቸው ከውሃ ጋር ነው። እነዚህን 17ቱን ግቦች ብዙዎቹን ከውሃ ውጪ ማሰብ አይቻልም።

እንደሚታወቀውና በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን እንደምንሰማው ኢትዮጵያ በከርሰ ምድሯ የማዕድን ሀብት በተለይ ነዳጅ እንዳላት ይታወቃል። ይህም ተስፋ ሰጪና አበረታች ነው እየተባለ ሲነገር ይሰማል። ነገር ግን ከነዳጅ ባልተናነሰ የሚያገለግለን ያለንን የውሃ ሀብት በአግባቡ መጠቀም ስንችል ነው ባይ ነኝ። በዚህ ብዙ ነገሮችን መቀየር እንችላለን ብዬ አምናለሁ።



ፎቶ ፡- ኤጋፔ ገዬን

**ኢትዮጵያ በጋራ የልማት ትብብር ፕሮግራም የምታምን እና የትብብር ስምምነት ማዕቀፍ ላይ አበክራ የምትሰራ ሀገር ናት።**

በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ የአቅም ውስንነት አጠቃላይ የኢኮኖሚ የማስፈጸም፣ የዕውቀትና የክህሎት እንዲሁም የሰው ኃይል ውስንነቶች ጠርንፈው ያዙን እንጂ አቅም ቢኖር ኖሮ ወንዞቻችንን በመጠቀም የበለጠ ውጤታማ መሆን እንችል ነበር።

ለምሳሌ እስራኤልን ማንሳት ይቻላል። እስራኤል በዓለም ደረጃ በግብርናው ቁጥር አንድ መሆን የቻለችው ምንም ለም አፈር በሌለበት ጨንጫ በሆነ መሬት ላይ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ነው። በአሁኑ ወቅት ፍራፍሬና አትክልትን ወደውጪ አገር በመላክ እስራኤልን የሚወዳደር የለም። በረሃማ የሆነውንም ስፍራ ወደገነት ቀይረዋል ማለት ይቻላል።

እንደ እድል ሆኖ የሰቆጣ ቃል ኪዳን ፕሮግራም ላይ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር መስሪያ ቤትን በመወከል ለስድስት ዓመት ያህል ሰርቻለሁ። ስራውን ስንሰራ በትግራይ ክልል 13 ወረዳ፣ በአማራ ክልል 27 ወረዳ በጥቅሉ ለመጀመሪያ አምስት ዓመት ስንሰራ የነበረው 40 ወረዳ ላይ ነበር። ይህ ፕሮግራም ከአስር በላይ የሚሆኑ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን ወደ አንድ ያመጣ ነው። ይህን ስራ ስንሰራ እስራኤላውያን ልምዳቸውን እንዲያጋሩን ጠይቀናቸው ነበር። በትግራይ ለቀላሚኖ እና ኤልሻዳይ ልምዳቸውን አጋርተው ያመጡት ለውጥ የሚያስገርም ነው። ሰርቶ ማሳያውን እንደ ማሰልጠኛ አድርገው በመስራታቸውም የአካባቢውን ወጣቶች አሰልጥነው ቦታውን እንደ ልህቀት ማዕከል አድርገውት ሳይ ምን ያህል ቴክኖሎጂው ውጤታማ መሆኑን እንድገነዘብ የሚያደርገኝ አሰራር ነው። ምንም እንኳ አካባቢው በረሃማ ቢሆንም ያለውን ውሃ በአግባቡና በቴክኖሎጂ በመታገዝ የተሰራው ስራ አስደናቂም ጭምር ነው። ውሃ የልማት ቁልፍ ከመሆኑም በተጨማሪ ችግሮቻችንን የምናይበት መነጽርም ጭምር ነው ብዬ እስባለሁ።

ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት ኢንዱስትሪያል ፓርኮች በመስፋፋት ላይ ናቸው። ለአብነት ደግሞ ኢትዮጵያ ከኬንያ ጋር እንድትገናኝ ተሰርቷል። እንዲሁም ደግሞ ከደቡብ ሱዳን፣ ከሱዳን እና ከጅቡቲ ጋርም ለመገናኘት እየተሰራ ያለ ፕሮግራም አለ። እንዲሁም ከሱማሊያ ጋር የምንገናኝባቸው የልማት ፕሮግራሞችም አሉ። ዋናው የምንገናኝበት ደግሞ ኃይል ነው። 90 በመቶ ያህል የኃይል ምንጫችን ሃይድሮፓወር ነው። ስለዚህ ፕሮጀክቶችን ተፈጻሚ ለማድረግ ኃይል ማመንጨት የግድ ነው። ኃይል በሌለበት ቦታ ኢንዱስትሪ ልማት ሊታሰብ አይቻልም። ከዚህ አንጻር ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ውሃችን ነዳጃችን ነው ማለት እችላለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ወሰን ተሻጋሪ ወንዞች ያሏት አገር ናት፤ ይህ የቀጣናውን አገራት ከማስተሳሰር አንጻር ምን ሚና አለው?**

**አቶ አበራ፡-** ኢትዮጵያ በጋራ የልማት ትብብር ፕሮግራም የምታምን እና የትብብር ስምምነት ማዕቀፍ ላይ አበክራ የምትሰራ ሀገር ናት። መቆም የሚቻለው በጋራና በመተባበር ነው፤ ይህ ካልሆነ በስተቀር ማንም ቢሆን በራሱ ብቻውን ሊቆም አይችልም። ለምሳሌ የኢትዮጵያ፣ ኬንያና ደቡብ ሱዳን የልማት ኮሪደር በሚል እየተሰራ ያለ ፕሮግራም አለ። ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ በእርሷ በኩል ያለውን ነገር ጨርሳለች ማለት ይቻላል። ለአብነት ፈጣን መንገዶች ተሰርተዋል። የአግሮፕሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ተሰርተዋል። ከዚህ በተጨማሪ የኢንዱስትሪያል ፓርኮች ተሰርተዋል። ከዚህ ጎን ለጎን በእኛ በኩል ያለው የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮች ተዘርግተዋል።

በኬንያ በኩል ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ባይሆንም የተወሰነ ርቅት መሄድ ችለዋል፤ ነገር ግን በጣም ብዙ ነገር ይቀራቸዋል። ደቡብ ሱዳን ላይ ደግሞ ምንም አልተጀመረም ማለት ያስደፍራል። ለምሳሌ ከኢትዮጵያ የሚሔደው የአባይ ውሃ ፍሰት አለ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ደቡብ ሱዳን ሰፊ መሬት አላት። ስለዚህ በመሪዎች መካከል ጠንካራ የሆነ የትብብር ስምምት ማዕቀፍ መኖር ቢችል ጥሩ የሆኑ የልማት አጋሮች መሆን ይቻላል። ምናልባትም አፍሪካን ከፍ የሚያደርጋት ብቻ ሳይሆን ለሌሎች አገሮች ሊተርፍ የሚችል ምርት ማምረት ይቻላል የሚል እምነት አለኝ።

ያንን ለማድረግ ግን በሐቅና መተማመን ላይ የተመሰረተ የአገራት የጋራ የትብብር ስምምት ማዕቀፍ መኖር አለበት። ይህ ከመጠባበቅ በዘለለ እና አንዱ ሌላውን ከመጠራጠር በዘለለ በባለሙያዎች የተፈተነ እና ለውሳኔ ሰጪ አካላት ግብዓት ሊሆን የሚችል ተጨባጭ ነገር ነው ብዬ አምናለሁ። ይህ አይነቱ ትብብር ካለ በርካቶችን የስራ እድል ተጠቃሚ ማድረግ ይችላል። ከዚህ ውጪ በሕገ ወጥ መንገድ በስደት የሚሄዱ ወጣቶችን ማስቀረት ይቻላል። በጥቅሉ በልማቱ ላይ ትኩረት ተደርጎ ማስተሳሰር ቢቻል ትውልዱ የራሱን ኑሮ በመለወጥ ጉዳይ ላይ ራሱ እንዲወጣ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

## የዘመን እንግዳ

# ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ውሃችን ...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

እድል የሚፈጠር ነው። ይህን ለመጠቀም ግን የትብብር ስምምነት ማዕቀፍ ያስፈልጋል። ከዚህ ባሻገር ቴክኖሎጂም ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ከሌላው የቀጣናው አገራት አኳያ ሲታይ የውሃ ሀብት እንዳላት ይነገራል፤ ይህን የውሃ ሀብት በአግባቡ ከማስተዳደር አኳያ ምን እየተሰራ ነው? የዘርፉ ምሁራን ኢትዮጵያ ውሃን ማዕከል ያደረገ የውሃ ስትራቴጂ እንደሚያስፈልጋትም ይናገራሉና እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ አበራ፡-** ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም የውሃ ፖሊስና ስትራቴጂ ሰነድ አላት። ነገር ግን ያ ፖሊሲና ስትራቴጂ አሁን ያለንበትን ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ ተደርጎ መቃኘት አለበት። 40 ሚሊዮን ሕዝብ በነበርን ወቅት የነበረን ፖሊሲና ስትራቴጂ አሁን 120 ሚሊዮን ሕዝብ ሆነንም ተገቢ ሊባል አይችልም። የምናስበው የውሃ ሀብት አስተዳደር ስርዓታችን ቀደም ሲል በነበረው መልኩ መሆን የለበትም።

በአሁኑ ወቅት የሕዝብ ቁጥር ከመጨመሩ በላይ ጠያቂ ትውልድ ተፈጥሯል። የአገራችን የቆዳ ስፋት ግን ያለው ባለበት ቦታ ነው። ባለን የቆዳ ስፋት ላይ የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ ነው። ስለዚህ የኢኮኖሚ ጥያቄዎች ከቀን ቀን እየጨመሩ ይመጣሉ። የኢኮኖሚ ጥያቄ ሲባል ደግሞ አንደኛው ምንጩ ውሃ ነው።

ስለዚህ የውሃ አስተዳደር ስርዓታችን በሚገባ መቃኘትና ዘመኑን በሚዋጅ መልኩ በአግባቡ በፖሊሲ ደረጃ መቀረጽ መቻል አለበት። ያንን ከማድረግ አኳያ በቅርቡ የእኛ የውሃ ሀብት አስተዳደር ፖሊሲም፣ ውሃ እና ሳኒቴሽን ፖሊሲም እንዲሁም ኢነርጂ ፖሊሲ ሶስቱም ዘርፎች ፖሊሲያችን ላይ ክለሳ አድርገዋል።

ለምሳሌ ለሚኒስቴሩ ተጠሪ የሆኑ ተቋማት አሉ። የአዋሽ ተፋሰስ፣ የአባይ ተፋሰስ፣ የስምጥ ሸለቆ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች አሉ። በጽህፈት ቤት ደረጃ እነዚህ ሶስቱ አሉ። ለምሳሌ የአባይ ተፋሰስ ቅርጫፍ ጽህፈት ቤት ያለው ባህርዳር ቢሆንም በንዑስ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች የአሶሳውን ጨምሮ አሉን። ስለዚህ አይናችን ትልቁ ዝሆን ላይ ማተኮር አለበት የሚል እምነት አለን። ለምሳሌ በሰሜን ተከዜ ወንዝ አለ፤ በምዕራብ ደግሞ በለስ ወንዝ አለ። በደቡብ ደግሞ ዋቤ ሸበሌ በሌሎችም እንዲሁ ትልልቅ የሚባሉ ወንዞች አሉ። የት ቦታ ማድረግ የምንችለው ምንድን ነው? የትኛው ዘርፍ የሚጠበቅበት ምንድን ነው? የሚለውን በጋራ ማየት አለብን። ለምሳሌ ቦረና አካባቢ ለተከታታይ ዓመታት ዝናብ ባለመዝነቡ ሰው ተጎድቷል፤ ከብቶችም አልቀዋል። ከዚህ የተነሳ በኢኮኖሚውም በኩል ብዙ ነገር አጥተናል። በድርቁ ምክንያት የበርካታ ከብቶች ባለቤት የነበረው አርብቶ አደር ከብቶቹን በድርቁ ሳቢያ ተነጥቋል።

ይህ አይነት ችግር እንዳይደገም ከአጭር ጊዜ ይልቅ የረጅም ጊዜ እቅዶችን ታሳቢ ያደረጉ የልማት ስትራቴጂዎች መቀረጽ መቻል አለባቸው። ከዚህ የተነሳ የተቀናጀ የልማት አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት አለበት። ይህ ሲሆን መሬትና ውሃን አስተሳስረን መያዝ ያስችለናል።

ለምሳሌ ግብርና ሚኒስቴር በሰብል፣ በእንስሳት፣ በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ማተኮር ይችላል። የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ደግሞ የሚገነባው ግድቦችን እንዲሁም የመስኖ ካናሎችን ነው። ከዚህ አንጻር ሁለቱ መስሪያ ቤቶች እንዴት ነው ተቀናጅተው እየሰሩ ያሉት? ለምሳሌ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የመስኖ ግድብ ሲገነባ እግረ መንገዱንም ለምን ለመጠጥ ውሃ አገልግሎት የሚሆን ግድብ አብሮ አይገነባም? ምክንያቱም ለእያንዳንዱ እንቅስቃሴ በርካታ መዋዕለ ንዋይ ይፈስባቸዋልና መስሪያ ቤቶቹ ለዘርፉ ብዙ ዓላማ መስራት ይኖርባቸዋል ብዬ ስለማምን ነው።

ለምሳሌ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብን ስንገነባ ታሳቢ ያደረገው ኃይል ለማመንጨት ብቻ አይደለም። ጎን ለጎን ለቱሪዝም አገልግሎት፣ ለዓሳ እርባታ፣ ለመዝናኛነት ብሎም በኢኮሎጂው ላይም የሚያሳድረው በጎ ተጽዕኖ ሁሉ ከግምት ውስጥ ገብቶ ነው። ፕሮጀክቶች ሲቀረጹ ግራ ቀኙ ታይቶ ዘርፉ ብዙ ጥቅም የሚያመጣ መሆኑ ከግምት



ውስጥ ገብቶ መሆን አለበት። ስለዚህ ከውሃ ሀብት አስተዳደር ስርዓት አኳያ በጣም ብዙ የሚቀሩን ስራዎች አሉ።

ለምሳሌ ወንዞቻችንን በተመለከተ እንዲሁም ተፋሰሶችን በተመለከተ ማስተር ፕላን እንደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን አለን፤ ማስተር ፕላን ያላቸውን መከለስ፤ በትክክል በሚፈለገው መልኩ እንዲሄድ ማድረግ ተገቢ ነው። የሌላቸውን ደግሞ እንዲንዲኖራቸው ማድረግ፤ ያሉንን ዋና ዋና ተፋሰሶችንና ንዑስ ተፋሰሶችን ማስተሳሰር፤ እንዲሁም በዙሪያቸው ያሉት የልማት ፕሮግራሞች ምን እንደሚመስሉ መረዳትም የራሱ የሆነ ፋይዳ አለው። በጥቅሉ የብዝሃ ሴክተር ቅንጅት ስርዓት መዘርጋት መቻል አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በቂ ዝናብም ሆነ በቂ ውሃ አላት፤ ይህን ውሃ በአግባቡ ይዞ ወደ ምግብ እና ወደ ኢነርጂ ለመቀየር ምን ያህል እየተሰራ ነው?**

**አቶ አበራ፡-** መጀመሪያ ኢነርጂው ላይ ምን ተሰራ? ላልሸው፤ ለምሳሌ ኢትዮጵያ ያላት አጠቃላይ የተፈጥሮ ጸጋ ብዙ ነው፤ ጸሐይን ብቻ ብንወስድ ከዚህ አኳያ ብዙ መጠቀም የሚያስችለን ሀብት ነው ማለት ይቻላል። አውሮፓውያኑን ብንወስድ በየጊዜው የበረዶ ግግር የሚያጠቃቸው ናቸው። በእነርሱ አካባቢ ጸሐይ ብርቅ ነው። እንደ እድል ሆኖ ጸሐይ ከወጣ ከወጣችው ጸሐይ ሙቀቷን ለመቋደስ ሰው ሁሉ ጎዳና ወጥቶ ይቆማል።

ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያን ስንመለከት በጋ ከክረምት ተመጥኖ የተሰጣት አገር ናት ማለት ይቻላል። ከፍተኛ የሆነ እምቅ የጸሐይ ኃይል አቅም ብቻ ሳይሆን የነፋስም የእንፋሎትም ኃይል አለን። የሃይድሮፓወርን እንኳ ሳንጨምር በእነዚህ ታዳሽ ኃይል ብቻ እንኳ መስራት ብንችል ከፍ ያለ ለውጥ ማምጣት እንችላለን። ትንንሽ ግድቦችን በመገንባትና የጸሐይንና የነፋስ ኃይልንም በመጠቀም 300 እና 400 አባወራዎችን በቀላሉ ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችል ሁኔታ ሰፊ ነው። በዚህ ረገድ ያለን ሀብት ገና አልሰራንበትም፤ አልተነካምም።

ያለን የጸሐይ አቅም ሰፊ ሆኖ ሳለ በእስካሁኑ ሒደት ያለን አሸጎዳና አዳማ ላይ ብቻ ነው። በአሁኑ ወቅት በግንባታ ላይ ያሉ አሉን። ይህም ወደ ሶማሌ፣ አፋርና ድሬዳዋ አካባቢ ሲሆን፣ ይህም ወደማጠናቀቂያው የተቃረበ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ አሰላ ግንባታው እየተካሔደ ነው። ነገር ግን ካለን እምቅ ሀብት የተነሳ ይህ በቂ አይደለም። የወደፊቱ የአስር ዓመት የልማት ግባችን ላይ በብዙ የተካተተበት ፕሮግራም ነው። ምክንያቱም ትኩረት አድርገን የምንሰራው በታዳሽ ኃይል ነውና።

**አዲስ ዘመን፡- በዝናብ የሚገኘውን ውሃ በአግባቡ ይዞ ከመጠቀም አኳያ የሕዝቡ አረዳድ ምን ላይ ነው ያለው?**

**አቶ አበራ-** የዝናብ ውሃ እንደዘበት በጎርፍ መልክ እብስ እንዲል ከማድረግ ይልቅ ከጣሪያችን የሚፈሰውንም ጭምር ሰብስቦ መጠቀም ወሳኝ ነው። ይህ ሲሆን ውሃን ከብክለትም ከብክነትም መታደግ ይቻለላል። አነስተኛ ግድብ በቤታችን ሊኖረን በሚያስችል መልኩ ብንሰራ እኛም መጠጣት፣ ከብቶቻችንንም ማጠጣት እንዲሁም ለምርታማነት መጠቀም የሚያስችለን ነው። ይህ ብቻ በቂ ነው ማለት ሳይሆን ውሃ በሌለበት ወሳኝ ጊዜ እንድንጠቀም የሚያስችል ይሆናል። በቀጣዩ የዝናብ ወቅት ደግሞ እንዲሁ ውሃ በመያዝ ለሚያስፈልገን ማዋል እንችላለን።

በእርግጥ እንዲህ አይነቱን ስራ በትምህርት ቤቶች፣ በጤና ተቋማትም ጀምረናል። በዚህ ዓመት ከ120 በላይ ሳይቶች ተመርጠዋል። ቦረና እና ጎንደር ላይ የጀመርን ሲሆን፣ የቴክኖሎጂውን ውጤታማነት ማረጋገጥ ችለናል። በጣም ትርጉም ያለው ስራ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በቶሎ ወደየስፍራው ለማስገባት እየተሰራ ነው። ይህ ስራ ቀደም ሲል እንደነበረው አይነት የውሃ ማቆር ሳይሆን በቴክኖሎጂ የታገዘ እና አገልግሎቱም ሰፋ ያለ ነው። በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ለሙከራ ብለን የሰራናቸው በአሁኑ ወቅቱ ፋይዳቸው ላቅ ያለ ሆኖ አግኝተነዋል።

በኢነርጂው ዘርፍ ባዮጋዝ ከዚህ ቀደምም የነበረ ነው። ምናልበባት የአቅም ውስንነት ካልገደበን እና የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት ካለመቻላችን በስተቀር ለዘርፉ የሚሆን ግብዓት አለ። ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት የመብራት ታሪፍ በየጊዜው እየጨመረ መሆኑን ተከትሎ ሕዝቡም በዚያው ልክ ሮሮ እያሰማ ይገኛል። በከተማ ከየመጸዳጃ ቤቱ የሚወጡ ፍሳሾች ከገጠር ደግሞ ከየከብቱ የሚገኘው ለበባዮ ጋዝ ትልቅ ግብዓት ነው። የአደጉ አገራት በዚህ ቴክኖሎጂ መጠቀም ከጀመረሩ ዘመናት ተቆጥረዋል። በጥቅሉ ግን በኢነርጂ ዘርፍ የፖሊሲ ለውጥ ከማድረግ ጀምሮ ትልቅ ስራ እየሰራን ነው፤

ይሁንና ፖሊሲ መለወጥ ብቻ በራሱ ውጤት አይደለም። ዋናው ውጤት የሚባለው በዘርፉ ያለውን ኢንቨስትመንት መሬት ላይ ማውረድ ነው። ለምሳሌ ከመንግስታት ጋር የሚደረጉ የልማት ድጋፍና ትብብሮች በእነዚህ የኢነርጂ ዘርፍ ላይ እንዲያተኮሩ እንፈልጋለን።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይም ጭምር ትኩረት የሰጡት የኃይል ዘርፍ ላይ በጣም መስራት አለብን የሚል ነው፤ እሱ ላይ እስካልሰራን ድረስ ከችግራችን ልንላቀቅ አንችልም። የኃይል ዘርፉ ማደግ፣ መለወጥና ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እስካልተሰራ ድረስ ኢኮኖሚያችንን በምንፈለገው መልኩ ማሳደግም መለወጥም አንችልም።

በውሃው ዘርፍ ላይም እንዲሁ ነው። በውሃው ዘርፍ ላይ ለምሳሌ የውሃ ሀብት አስተዳደር ዘርፍ አለ፤ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ አለ፤ እንደሚታወቀው ደግሞ የውሃ ሀብት አስተዳደር በጣም ሰፊ ነው። የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽንም ጭምር አቅፎ ይይዘዋል። ስለዚህ ሁለቱ ዘርፎች ተናበውና ተቀናጅተው ነው እየሰሩ ያሉት። በአሁኑ ወቅት ፖሊሲያችንን ስንከልስ በዚህ አንግል ነው።

ከዓመታት በፊት አስርና ሃያ ሜትር ድረስ ተቆፍሮ በቀላሉ ውሃ ማግኘት ይቻል ነበር። አሁን አሁን ግን 150 ሜትር ርቀት ላይ ተቆፍሮ ውሃ ማግኘት አይቻልም። ስለዚህ ያለው አማራጭ የገጠር ውሃ አማራጮችን ማየት ነው። በተለይ ወንዞችን መመልከት ያስፈልጋል። በእርግጥ ደግሞ ወንዞችን ሙሉ በሙሉ ገድቦ ከታች ያለውን የኅብረተሰብ ክፍል ለግጭት ማነሳሳት ተገቢ አይደለም። ነገር ግን በፖሊሲያችን ላይ የተቀመጠው የመጠጥ ውሃ በመጀመሪያ የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጠው የአገልግሎት ዘርፍ እንደሆነ ነው። ከዚህ በዘለለ መስኖው፣ ኢንዱስትሪውና ሌላ ሌላው ይመጣል ማለት ነው። ይሁንና የሚቀረን ብዙ ስራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቀጣይ ስራ ምን ላይ ያተኮረ ነው? ከቀጣናው አገራት ጋርስ ያለው ትብብር ምን ይመልሳል?**

**አቶ አበራ፡-** በውሃው ዘርፍ ላይ የውሃ ሀብት አስተዳደርና የውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ አጠቃላይ እንደአገር ካለንበት ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ከሶማሌ እስከ ጋምቤላ፣ ከትግራይ እስከ ቤኒሻንጉል ያለውን ጽንፍ በአግባቡ አጥንቶ እና የሌሎች ሴክተሮችን የውሃ ጥያቄ ለምሳሌ የግብርና ሚኒሰቴር የውሃ ጥያቄ፣ የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የውሃ ጥያቄ እና የሌሎችም የውሃ ጥያቄዎች የሚያቀርቡ ሴክተሮች አሉ፤ ከዛ አኳያ የሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን ፖሊሲ ከሌሎች ሴክተሮች ፖሊስ ጋር የተጣጣመና የተናበበ ነው ወይ? በሚል ስራ እየተሰራ ነው።

አንዱ በቅርቡ በእቅድና ልማት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ውስጥ የሚመራ የ22ቱም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ውስጥ የልማት ፖሊሲ የማናበብ (አላይንመንት) ስራ ተሰርቷል። የትኛው ፖሊሲ ከየትኛው ፖሊሲ ጋር ይጣጣማል? ይገናኛል? ወይም ደግሞ ይጣረሳል? የሚለውን የማስታረቅና የማናበብ ስራዎች ተሰርተዋል። ይህ አንድ ትልቅ እርምጃ ነው ብዬ አስባለሁ፤ ፖሊሲና ስትራቴጂ በሌለበት ሌሎች ፕሮግራሞችን ማስፈጸም አይቻልም።

ለምሳሌ ኢትዮጵያ ለጅቡቲ ውሃ እያጠጣች ነው። ይህ የአገራት ትብብርን ምርጫ የሌለው ብቸኛ የጋራ ስራችን ነው ብለን ነው የምናምነው። እኛ ዘንድ ያሉ ውስንነቶችና ችግሮች በተለይ ያልመለስናቸው ጥያቄዎች እንዳሉ ሆነው፤ ነገር ግን የጂቡቲ ሕዝብ ወንድም የሆነ ጎረቤት ሕዝብ ነው። ጂቡቲ በኢትዮጵያ ድንበር ውስጥ 28 የውሃ ጉድጓዶች አሏቸው። ከ28ቱ 11ዱ ጉድጓዶች በአሁኑ ወቅት ውሃ ያመርታሉ። ቀሪዎቹ መጠባበቂያ ናቸው። እያንዳንዳቸው ጉድጓዶች በሜትር ፐርሰከንድ በሊትር ከ40 እና ከ50 በላይ ውሃ ይሰጣሉ። ይህ የከርሰ ምድር ውሃ ነው። ተገቢ ጥናት በጥንቃቄ የተሰራ ስራ ነው። እነርሱ ከ650 ሚሊዮን ዶላር በላይ ለዚህ ፕሮጀክት ወጪ አውጥተውበታል። ይህ ውሃ በጄኔሬተር እየተገፋ 350 ኪሎ ሜትር ርቀት የሚሄድ ነው። ውሃውን ወደጂቡቲ ለመግፋት በቀን በርካታ ሺ ሊትር ነዳጅ ይጠቀማሉ። ይህ የሚሆነው እስከተወሰነ ኪሎ ሜትር ሲሆን፣ ከተወሰነ በኋላ በራሱ ግፊት የሚሄድ ነው።

ወደ ሌሎቹ ስንመጣ ደግሞ ደቡብ ሱዳን ከቃሪያና ከሽንኩርት አቅም የሚያስገቡት ከዑጋንዳ ነው። ከዑጋንዳ ለማስገባት ዞሮ የሚገባው በኬንያ በኩል ነው። እኛ ግን ያለነው አፍንጫቸው ስር ነው። ለምንድን ነው ከደቡብ ሱዳን ጋር ፈጣን የሆነ ያጋራ የትብብር ስምምነት ተፈራርመን መሰረተ ልማቶችን ዘርግተን ነዳጃችንን ከደቡብ ሱዳን የማናስገባው? ምክንያቱም 300 እና 400 ኪሎ ሜትር የማይሞላ ርቀት ላይ ነው ያለነው፤ ጨክነን ያንን መዘርጋት ለምን አልቻልንም። በተለይ ደግሞ አጠቃላይ የገቢና ወጪ ምርታችን ጂቡቲ ላይ እንደመሆኑ ምን ያህል ማነቆ ውስጥ እንዳለን እናውቃለን። ያንን ሊተካ የሚችል አማራጭ እድሎችን ሊፈጥሩ የሚችሉ አቅሞች አሉ። ስለዚህ እዛ ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት ያስፈልጋል። በመሆኑም የብዝሃ ሴክተሮች ቅንጅታዊ አሰራር ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ በደንብ የተናበበ የተሰናሰለ የፖሊሲ ማዕቀፍ ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- ለሰጡን ማብራሪያ አመሰግናለሁ።**

**አቶ አበራ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።


# ማህደረ ጤና

## ከእለት ተዕለት አመጋገባችን ላይ የትኞቹን ዘር እናድርግ?

**እፀገነት አክሊሉ**

ምግብ በራሱ ለሰው ተፈጥሮ የማይስማማ ወይም የሚጎዳ ነው ብሎ መደምደም ከባድ ነው። ምክንያቱም ምግብ በራሱ ክፉ ስላልሆነ። ነገር ግን ምግቦች የሚዘጋጁበት መንገድ፣ የምንመገበው መጠንና ድግግሞሹ ከምግቦቹ የምናገኘውን ጠቀሜታ ከማሳጣት ጀምሮ ለከፋ የጤና ጉዳት እስከመዳረግ ሊያደርስ እንደሚችል የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ። እናም የሚዘወተሩ ምግቦች ምናልባትም በሰውነት ውስጥ ተገዳዳሪ ጠላትን እያዘጋጁ ሊሆን እንደሚችል ማወቅ ያስፈልጋል።

ለመሆኑ ባለሙያዎች ከዕለት ዕለት የምግብ ፍጆታችን 'ዞር' እንድናደርጋቸው የሚመክሩን ምግቦች የትኞቹ ናቸው? ለምን? የሚሉትን ደግሞ የተለያዩ ምንጮችን ተጠቅመን በዚህ ጽሁፍ ለመዳሰስ እንሞክራለን፡፡



### ቅባት ያላቸው ምግቦች

በአሜሪካ በዩኒቨርሲቲ ኦፍ ላስቬጋስ የምግብ ዝግጅት እና ስነ ምግብ ባለሙያዎች እንደሚሉት እንደ ጮማ ስጋ ያሉ ቅባት ያላቸው ምግቦችን ማዘውተር በሰውነት ውስጥ ከፍተኛ የፐሮቲን መጠን እንዲከማች ምክንያት ነው።

ይህ ሃሳብ ታዲያ ፐሮቲን ቢበዛ ምን ችግር አለው? የሚል ጥያቄ ሊያስከትል ይችላል። ባለሙያዎቹ ሲመልሱ ከቅባታማ ምግቦች የምናገኛቸው ፕሮቲኖች በሰውነት ውስጥ እየተበራከቱ ሲሄዱ በስርዓተ ምግብ ሂደት ከመወገድ ይልቅ ወደ ስብነት ይቀየራሉ። ይህም ለሪህ ወይም የሰውነት መገጣጠሚያ ህመም ከማጋለጥ ጀምሮ በኩላሊት ላይ ከፍተኛ ጫና በማድረስ ለዘላቂ የጤና ችግር ሊዳርግ ይችላል።

ለዚህም ነው የዓለም ጤና ድርጅት በቀን አንድ አዋቂ ሰው በእያንዳንዱ የሰውነት ክብደት መጠኑ ከ 0 ነጥብ 83 ግራም ያልበለጠ ፕሮቲን እንዲወስድ የሚመክረው። ለአብነት አንድ 60 ኪሎ ግራም የሚመዝን የ40 ዓመት ሰው በየቀኑ ከ50 ግራም ያልበለጠ ወይም በሳምንት ከ 0 ነጥብ 35 ኪሎ ግራም በላይ ፕሮቲን ባይወስድ መልካም ነው ይላሉ። ቅባታማ ምግቦችን ማዘውተር ሰውነት ከሚፈልገው በላይ ፕሮቲን ማስከተሉ አይቀርም።

ኢትዮጵያ ውስጥ አቅም ከፈቀደ በጣም ብዙ ዘይት፣ ቅቤ ጨምሮ ምግብን ማብሰል የተለመደ ነው። ነገር ግን ምግቡ ቅባት አዘል ባይሆን እንኳን ማንኛውንም ምግብ በዘይት ወይም በቅቤ ቅባታማ ማድረግ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝን ይሆናል።

ከመጠን ባለፈ ሁኔታ ቅባት የበዛባቸውን ምግቦች መጠቀም ከፍተኛ ስብና ከሚቃጠለው በላይ ኢነርጂ በሰውነት ውስጥ እንዲጠራቀም እና ጤናም እንዲታወክ ምክንያት ይሆናል።

ከዚህ አንጻር አጠቃላይ የዘይት፣ የቅባት አጠቃቀማችንን መፈተሽ ያስፈልገናል። የቅባት መጠንን መቀነስ ከተቻለ ደግሞ የቅባት አይነቶችን እና ምንጩን መምረጥ ተገቢ መሆኑን ባለሙያዎች ይመክራሉ።

### የገበታ ጨው

"የጨው ጨዋታ ምላስ ላይ ብቻ ነው" የሚሉ ባለሙያዎች ጨውን ብንተወውም ምንም ጉዳት እንደሌለው ይናገራሉ። በሰውነት ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ የጨው መኖር ለተለያዩ በሽታዎች የመጋለጥ ዕድልን ይጨምራል ይላሉ።

ጨው ሶዲየም የተባለ ማዕድን ይይዛል። ሶዲየም ደግሞ ሰውነት ውስጥ ሲበዛ ከፍተኛ መጠን ያለው ውሃ የደም ቧንቧዎች ውስጥ እንዲኖር ያደርጋል። በደም ቧንቧዎች ውስጥ ከፍተኛ ውሃ አለ ማለት ደግሞ መደበኛ ያልሆነ የደም ግፊት እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል ። የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት በጊዜ ሂደት ውስጥ ለደም ግፊት፣ ለስትሮክ፣ ለኩላሊት እና ለልብ ህመም መጋለጥን ሊያመጣ ይችላል። የዓለም ጤና ድርጅት አዋቂ ሰው በቀን ከአምስት ግራም ወይም ከአንድ የሻይ ማንኪያ ያልዘለለ የገበታ ጨው እንዳይጠቀም ይመክራል።

ከዚህ በተቃራኒ በበርካታ የኢትዮጵያ አካባቢዎች በምግብ ዝግጅት ውስጥ ጨው ከመጠን በላይ ጥቅም ላይ ይውላል፤ በአንድ ምግብ ውስጥ በተለያየ መንገድ በርካታ ጊዜ ጨው ይጨመራል። ጥቅም ላይ የሚውሉት ቅመሞች ካላቸው ጨው በተጨማሪ ሲበስሉም ጨው ይጨመርባቸዋል፤ ይህም በሰውነት ውስጥ የጨው ክምችትን ከፋ ያደርጋል። ባለሙያዎች ‹‹የጨው አጠቃቀማችንን መቀነስ ቢቻል የሀገሪቱ የበሽታ መጠን መቀነስ ይችላል›› የሚል እምነት ያላቸውም ለዚህ ነው፡፡

ጨው የሚጠቀሱለት የጤና ጥቅሞች ቢኖሩትም ከመጠኑ ሲያልፍ ከጥቅሙ ጉዳቱ እያመዘነ ይመጣል። ለዚህም ነው ባለሙያዎች ያልተገባ የጨው አጠቃቀምን አጥብቀው የሚኮንኑት።

### ስኳር እና ጣፋጭ ምግቦች

በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የምግብ ስርዓት እና ስነ ምግብ ተመራማሪዎች እንደሚሉት፣ ስኳርን አብዝቶ መውሰድ በሰውነት ውስጥ የኃይል ሰጪ ንጥረ ነገር ከመጠን እንዲያልፍ ያደርጋል። ኃይል ሰጪ ንጥረ ነገር ሲበዛ ደግሞ በርካታ መዘዞችን ይዞ ይመጣል። የመጀመሪያው የሰውነት ክብደት መጨመር ወይም ውፍረት ሲሆን ይህ ደግሞ በራሱ ለሌሎች በሽታዎች የመጋለጥ ዕድልን ከፍ ያደርጋል። ከምግብ ፍላጎት መቀነስ ጀምሮ ለልብ ችግር፣ ለስኳር ህመም እና ተያያዥ ጉዳቶች ሊዳርግም ይችላል።

ስኳር ግሉኮስ እና ፍሩክቶስ የተሰኙ ማዕድኖች ውህድ በመሆኑ ወደ ሰውነት ሲገባ ግሉኮሱ ወደተለያዩ ውስጣዊ ክፍሎች ይሰራጫል፣ ፍሩክቶስ ደግሞ በቀኝ የጉበት ክፍል በመከማቸት ለተለያዩ የጤና ጉዳቶች ይዳርጋል።

በተጨማሪም ኬክ፣ ከረሜላ፣ አይስክሬም እና የለስላሳ መጠጦች በከፍተኛ የስኳር መጠን ስለሚዘጋጁ እነሱን አዘውትሮ መጠቀም ስኳር ከመቃም ያልተናነሰ ተግባር በመሆኑ የሚያስከትለው ጉዳትና ችግርም በዛው ልክ ሰፋ ያለ ይሆናል ።

ይህም ማለት ግን ስኳር ለሰውነት አያስፈልግም ማለት አይደለም፡፡ ምግብ ወይም መጠጥ ውስጥ የሚጨመረውና የተጣራ ስኳርን ማዘውተር አይመከር እንጂ ከፍራፍሬዎች የሚገኘው ፍሩክቶስን የያዘ ስኳር ለጤና ጠቃሚ ብቻ ሳይሆን በሰውነት ዕድገት ውስጥ ወሳኝ ነው።

አንጎላችን 60 በመቶ ኃይሉን የሚጠቀመው ከስኳር በመሆኑ መጠቀም ያለብን፣ በአንዴ ለሰውነታችን ብዙ ስኳር የሚለቀውን የተጣራ ስኳርን ሳይሆን፣ ቀስ በቀስ ወደ ሰውነት የሚሰራጨውን እና ፍራፍሬን ከመሰሉ የምግብ አይነቶች የምናገኘውን ስኳር መሆኑን ባለሙያዎች አበክረው ይመክራሉ ።

### የፋብሪካ ምግቦች

ከበለጸጉት ሀገራት በተቃራኒ በኢትዮጵያ የታሸጉ ምግቦችን የማምረት እና የመጠቀም ባህሉ ዝቅተኛ በሚባል ደረጃ ያለ ቢሆንም በተለይ በከተሞች የእነዚህ ምግቦች ፍላጎት ቀስ በቀስ እያደገ ይመስላል። በከፍተኛ የዝግጅት ሂደት የሚያልፉ የታሸጉ ምግቦች ከፍተኛ ስኳር እና ጨው የመያዝ ዕድላቸው ሰፊ ነው።

በከፍተኛ የዝግጅት ሂደት ያለፉ ምግቦችን በተቻለ መጠን ብናስወግድ የተሻለ ስለመሆኑም የዘርፉ ባለሙያዎች ይመክራሉ። እነዚህ ምግቦች ሲዘጋጁ ተፈጥሮዊ ያልሆኑ ማቅለሚያዎች፣ ማጣፈጫዎች እና ማቆያዎችን ይይዛሉ። በመሆኑም አዘውትረን በተመገብናቸው ቁጥር በሆድ እና በአእምሮ መካከል ያለውን መስተጋብር ማወክ ይጀምራሉ ።

አዕምሮ የጥጋብን ወይም የረሃብን ስሜት የሚረዳበት ስርዓት ያለው ቢሆንም እነዚህን የፋብሪካ ምግቦች ማዘውተር ግን መስተጋብሩን የማዛባት እና ከሚገባው በላይ ደጋግሞ የመመገብ ፍላጎትን እንዲጨምር አንዳንድ ጊዜም ሱስ እስከመሆን ሊደርስ እንደሚችል ባለሙያዎች ያብራራሉ ።

በሌላ በኩል በፋብሪካ ሂደት ያለፉ ሆት ዶግ እና በተለያየ መልክ የሚዘጋጁ የቀይ ስጋ ውጤቶች ለካንሰር አጋላጭ ከመሆናቸውም በላይ በፋብሪካ ሂደት ሲያልፉ የነበራቸውን ተፈጥሯዊ ይዘት የመልቀቅ ዕድላቸው በጣም ከፍተኛ ነው። ሳይበላሹ የመቆየት ዕድሜያቸው እንዲጨምር ሲባል የሚገቡ ኬሚካሎች ደግሞ ጎጂነታቸው ከፍ ያለ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም ሰውነታችን እንደነዚህ አይነት ነገሮችን እንዲቀበል ሆኖ አልተሰራምና ።

የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ባለሙያዎችም ይህንን ሃሳብ መነሻ በማድረግ በኢትዮጵያ ያለው ሽሮን የመሰሉ የምግብ ዓይነቶችን ገዝቶ ቤት ውስጥ የማዘጋጀት ባህል እጅግ ሊበረታታ የሚገባው መሆኑን ይጠቅሳሉ። ይህ ልማድ በፋብሪካ ለሚዘጋጁ ምግቦች ቦታውን በፍጹም ሊለቅ እንደማይገባውም አጽንኦት በመስጠት ይመክራሉ።

### በዘይት የተጠበሱና ፈጣን ምግቦች

በዘይት የተጠበሰ ድንችን ወይም ችፕስ፣ ሳምቡሳና ጣፍጭ ብስኩቶችን ጨምሮ ሌሎች በዘይት ተዘጋጅተው በፍጥነት የሚደርሱ ምግቦች [fast food] መሸጥ በኢትዮጵያ በተለይም በከተሞች አካባቢ እየተበራከተ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ለበርካታ የጤና ችግሮች መንስዔ ወይም አባባሽ እየሆነ ስለምምጣቱ ባለሙያዎቹ ይናገራሉ። እንደነዚህ አይነት ምግቦች በተለይም ችፕስን የመሰሉ በዘይት የሚጠበሱ ምግቦች ያላቸው የስነ ምግብ ጠቀሜታ ዜሮ ሲሆን በተለይም አብዛኞቹ የሚጠበሱት በፓልም ዘይት መሆኑ ደግሞ የጤና ስጋትነታቸውን አባብሶታል ።

እንደ ባለሙያዎች ሀሳብ እነዚህ ምግቦች የበለጠ ጎጂ የሚሆኑት የሚጠበሱበት ዘይት ደጋግሞ ጥቅም ላይ ስለሚውልና በዚህም ምክንያት ምግቡ ዘይቱን በመምጠጥ ጎጂ ስብን እንዲያጠራቅም ይሆናል ፤ ይህ ጎጂ ስብ ካንሰርን ጨምሮ ለተለያዩ ድምጽ አልባ ገዳይ ህመሞች የማጋለጥ እድሉ ደግሞ እጥፍ ነው። ለጤናም አደገኛ ነው። ከተቻለ በዘይት የሚጠበሱ ምግቦችን ማስወገድ ይመከራል። አትክልትም ሊሆን ይችላል በዘይት የምንጠብሳቸው ነገሮች መቅረት መቻል አለባቸው፡፡

ለምን? የሚለውን ባለሙያዎች ሲያብራሩ በጣም የተጠበሰ ዘይት ከሰውነታችን ጋር ለመዋሃድ ይቸገራል። እየበረከተ ሲሄድ ደግሞ የደም ቧንቧ እና ሌሎች የጤና ችግርን ያስከትላል። ስለዚህ ዘይት ምግቡን ልናወጣ ስንል ብንጨምር እና ዘይት ዘይት የሚለውን ጣዕም ለማስቀረት ብቻ ቢበስል የተሻለ ስለመሆኑም ይናገራሉ።

በቅርቡ በዓለም ላይ በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፉ ያሉ ፈጣን ምግቦች አሳሳቢ እንደሆኑ እና ከልክ ላለፈ ውፍረት እና ተያያዥ ችግሮች እያጋለጡ ነው ሲል የዓለም ጤና ድርጅት አሳስቦ ነበር። እናም ፒዛ፣ በርገር፣ ችፕስ፣ የተጠበሰ ዶሮ እና መሰል ምግቦችን እንዲሁም በከፍተኛ ዘይት የሚጠበሱ ምግቦችን አለማዘውተር አሊያም ማስወገድን ባለሙያዎቹ ይመክራሉ።

### ታዲያ የትኞቹን ምግቦች እናዘውትር?

የስነ ምግብ ተመራማሪዎች የትኛውም ምግብ ብቻውን የተሟላ አይደለም ይላሉ። የተሟላ ንጥረ ነገርን ለማግኘት ግን ምግቦችን ማሰባጠርን ይመክራሉ። በጥቅሉ ግን አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ጥራጥሬዎችን፣ ለውዝን የመሰሉ የቅባት እህሎችን አዘውትሮ መመገብ ለጤናና ለሰውነት ዕድገት የተሻለ ጥቅም ያስገኛል።

ሆኖም ምግቦቹ የሚዘጋጁበት መንገድ ጠቀሜታቸውን ሊቀነስ ስለሚችል የአትክልት አበሳሰልን ምሳሌ በማድረግ ባለሙያዎቹ ያስረዳሉ።

በበርካታ የኢትዮጵያ አካባቢዎች አትክልቶችን ከመጠን በላይ ማብሰል የተለመደ ነው። ነገር ግን አትክልት በሚገባ በንጹህ ውሃ ማጠብ እንጂ ከመጠን ባለፈ ማብሰሉ ከምግቡ የምናገኘውን ንጥረ ነገር ሙሉ በሙሉ እንድናጣ ሊያደርግ ይችላል።

ባለሙያዎች ከገበታችን ማጣት የለበንም ከሚሉት የእህል ዘር አንዱ ደግሞ ቦሎቄ ነው። ቦሎቄን ማዘውተርን አጥብቀው ይመክራሉ። በተለያየ ቀለም የሚበቅለው ቦሎቄ እንደ ቀለሙ የተለያየ ጥቅም ሲኖረው በተለይም ከፍተኛ ፋይበር፣ ጤናማ ፕሮቲንና ስብ፣ በካርቦሃይድሬት እና መሰል ንጥረ ነገሮች የበለጸገ ስለመሆኑም ይመሰከሩለታል። ይህም ጤናማ የምግብ ፍላጎትን ለማዳበር ከማገዝ ጀምሮ የተለያዩ የጤና ጥቅሞችን ያስገኛል።

እኤአ በሚያዝያ 2020 የተከለሰው የዓለም ጤና ድርጅት የጤናማ ምግቦች ዝርዝር ለአዋቂዎች በባለሙያዎቹ የተጠቀሱትን ጨምሮ ያልተፈተጉ የሰብል ምርቶችን አካትቷል። ለአብነት በፋብሪካ ያላለፉ የበቆሎ፣ የአጃ፣ የስንዴ እና ቡናማ ሩዝን ከምግብ ዝርዝር ውስጥ ይኑር ብሏል።

ሁልጊዜም በዋና የምግብ ሰዓት ውስጥ አትክልቶችን ማካተት እንዲሁም እንደመክሰስ ሰዓት ላይ ደግሞ ፍራፍሬዎችን እና እንደ ሰላጣ ያሉ በጥሬ ሊበሉ የሚችሉ አትክልቶችን ማዘውተር ተገቢ ነው ሲል አስታውቋል። ቁልፉ ጉዳይ ግን አንድን ወይም ተመሳሳይ ምግብን ደጋግሞ መመገብ ቢያንስ የተሟላና ለሰውነት የሚያስፈልጉ ንጥረ ነገሮችን ከማግኘት ያራርቃል የሚለው ጉዳይ የባለሙያዎቹ ምክር ነው።

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## "የዘመናት የፊት እድፍ"

### የርዕሰ ጉዳያችን ማፍታቻ፤

የሰውን ልጅ የመደሰት፣ የማኩረፍ፣ የማዘን፣ የመከፋት፣ የመጠራጠር ወዘተ. ስሜቶች ለመረዳት ፊትን መመልከት ብቻ ይበቃል። "የልብን ምሥጢር ከፊት ላይ ማንበብ ይቻላል" የሚለው ብሂል ተዘውትሮ መነገሩም ይህንነው ሃሳብ ለማጽናት ይመስላል። ከተትረፈረፈ ግብዣ ይልቅ ለእንግዳ ክብሩ "ከፍትፍቱ ፊቱ" እንዲሉ "የፊት ፈገግታ" ምን ያህል ተመራጭ እንደሆነም ማከል ይቻላል።

"ፊቱን አዙሮ ሄደ" ሲባል ተከፍቶና ተቀይሞ ተመለሰ ማለት እንደሆነ ለቋንቋው ተናጋሪ እንግዳ አባባል አይሆንም። "ፊቱን አጠየመ፣ ፊቱን አጠቆረ" - ተከፋ፣ "ፊቱን አጠመመ" - የሚያስጸይፍ ነገር ስላየ ዘወር አለ፣ "ፊቱን ያዘ" - አፈረ፣ "ፊቱ ተፍለቀለቀ" - ከመጠን በላይ ተደሰተ፣ "ፊት አሳየ" - አቀረበ፤ ወደደ፣ "ኮሶ ፊት" - ኮስታራ፤ የጨፈገገው፣ "ፊተ ሰልካካ" - ቆንጆ፣ "ፊቱ ተኮፈሰ" - አኮረፈ፣ ተጸረረ ወዘተ. የመሳሰሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች "ፊት" ምን ያህል በርካታ መልእክቶች እንደተዋቀሩበት የሚያረጋግጡ ናቸው።

"ፊት" በውክልና የሚቆመው ለሰብዓዊ ፍጡር ብቻ ሳይሆን "የሰማዩ ፊት ጠቁሯል" እየተባለም "ለዶፍ ዝናብ" ጠቋሚነት አገልግሎት ላይ ይውላል። "ደስ ያለው ልብ ፊትን ያበራል" (ምሳሌ 15፡3) የሚለው የጠቢቡ አገላለጽም ትርጉሙ ላቅ ያለ ነው። "ፊት አውራሪ (ፊታውራሪ)" የሚለው ወታደራዊ ማዕረግም ከበድ ያለ ሥልጣን የተወከለበት ነው። ብዙ ሰዎች (በተለይም ከተሜ ቀመሶቹ) ማለዳ ወደ መደበኛ የሥራ ገበታቸው ከመሰማራታቸው አስቀድሞ በመስታወት ፊት ቆመው "በፊታቸው" ውክልና ራስን ማስገምገም የተለመደ የዕለት ተዕለት ክስተት ነው። "የፊት እድፍ በመስታወት፤ የኃጢያት እድፍ በክህነት" የሚለው ንስሃንና ይቅር መባልን የሚያበረታታው "ሃይማኖት ነክ" ብሂልም በክርስትና አማንያን ዘንድ ትርጉሙ ላቅ ያለ ነው።

ልብ ብለን ብናስተውል እያንዳንዱ ዘመን በራሱ ፊት ላይ የሚነበብ ታሪክ አለው። አንዳንዱ ዘመን በፈካ ፊቱ ላይ ልቡናውና አእምሮው የፈካ ትውልድ አስተናግዶ ያልፋል፡፡ ይህን መሰሉ ትውልድ የዘመንን ወንዝ የሚሻገረው ለራሱ ኖሮ ብቻ ሳይሆን ለተከታዩ ትውልድም ደማቅ አሻራ በማኖር ነው። አንዳንድ ዘመን ደግሞ እንደተጨፈገገ ተከስቶ ጠልሽቶ ሲያሽልብ በታሪካችን ውስጥ ደጋግመን የምናነበው እውነታ ነው። የዘመን ፊት የሚገመገመው በዕለት ኑሮ ብቻ ሳይሆን በታሪክ ብያኔ ጭምር ነው የሚባለውም ስለዚሁ ሳይሆን ይቀራል።

ደግሞም አለ አንዳንድ ዘመን ፊቱ እንደተሸፈነ መጥቶ "ምን ተሠራበት" ተብሎ ቢጠየቅ "ምንም" እየተባለ የሚመሸበት። ሆደ ባሻ ዘመንም አለ "እምባው" እንጂ ሣቁ ሳይሰማ የሚያልፍ። ነፍሰ ሔሩ መምህራችን ደበበ ሰይፉ ይህንን መሰሉን "አሻራ ቢስ" በራሪ ዘመን የመሰለው በሚከተሉት ጥቂት ስንኞች ወካይነት ነው። ነበርን እያስታወሱ ዛሬን መገምገም ያለና የሚኖር የሰው ልጆች ሁሉ ጠባይና ባህርይ ስለሆነ ስለምን ተብሎ አይጠየቅም።

**ጊዜ በረርክ በረርክ፣**
**ጊዜ በረርክ በረርክ፣**
**ግና ምን አተረፍክ፣**
**ግና ምን አጎደልክ?**
**ሞትን አላሸነፍክ፣**
**ሕይወትን አልገደልክ።**

በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ ዛሬም ድረስ ነግሠው ያሉት እኛ ሹሩቤያሙ የቀዳሚ ዘመናቱ ታላቅ መሪ እንደተናገሩት አስመስሎ የጻፈልን የተወዳጁ ባለቅኔችንን ጥቂት ግጥሞች እንደ መንደርደሪያ በመዋስ የዘመናችንን የፊት እድፍ "በመስታወት ፊት በሚደረግ የአፍታ ቆይታ" ያህል በፍጥነት ጠቅሰን እንለፍ።

**"ያለፈ ጥረታችንን፣ ሳስታምመው ትዝ ሲለኝ፣**
**ከሞከርነው ነገር ይልቅ ያልሞከርነው ነው እሚቆጨኝ።**
**ታዲያ እንግዲህ አንቺ ኢትዮጵያ፣ እኛስ ልጆችሽ ምንድነን፣**
**አመንኩሽ ማለት የማንችል ፍቅራችን የሚያስነውረን።**
**ዕዳችን የሚያፎክረን፣**
**ግፋችን የሚያስከብረን፣**
**ቅንነትየሚያሳፍረን ቂማችን የሚያስደስተን፣**
**እኮ ምንድን ነን? ምንድን ነን?**
**አሜከላ የሚያብብብን፣**
**ፍግ የሚለመልምብን።**
**ከአረም ጋር ያፈራን ጊንጦች፣ ከእንክርዳድ ያልተለየን ዘር፣**
**ግርዱ ከምርቱ ተማጥቆ፣ ከቶ ያልተበራየን መከር፣**
**ምንድን ነን? እኮ ምንድነን?**

እንደ እውነቱ ከሆነ ገጣሚያኑ ብቻ ሳይሆኑ እኛ ራሳችን የራሳችንን ዘመን ኑሮ ወደ ግጥም ብንለውጠው በመጻኢው ትውልድ የሚጠቀስ ፈለግ ትተን ለማለፍ አይቸግርም።

### የዘመናችን የፊት እድፍ፤

ዛሬ የደረስንበት የጊዜያችን የፊት እድፍ በዛሬ ጀንበር የተደፈደፈብን ብቻ ሳይሆን ከትናንት ታሪካችን የወረስነው ጭቅቅት ጭምር ነው። ገፊቱ እያንገሸገሸን ያለውና በኢትዮጵያችን ላይ የተላከከው የዛሬው ወሰክ (ቆሻሻ) መሰረቱን ጠለቅ ብለን እንፈትሽ ብንል የምንደርሰው የትናንቱ ዘመን ጥሎብን ባለፈው የከፋ ማዲያት ላይ ሊሆን ይችላል።

እየገፈገፍን ያለነው ሁለንተናዊው የዛሬ ብሔራዊ ዕዳችን የትናንቱ ዘመን ታቅፎና ፈልፍሎ ያሸጋገረልን ውላጅ እንጂ ዛሬ ላይ እያጨድን ያለነው የመከራችን አዝመራ ያፈራውን ምርት ብቻ አይደለም። ልባሙና ስደተኛው ገጣሚያችን ክፍሌ አቦቸር (ሻለቃ) "የትናንቱን ዘመን የፊት እድፍ ተግተንና ጨክነን" ይሉኝታ ሳይቆጣጠረን አብሰን ብናልፍ ኖሮ የዛሬው መከራችን ይቀልልን እንደነበር የተቀኘው እንዲህ በማለት ነበር።

**"ሀ" ሲባል "ሀ" ቢባል፤ ጅምሩ ቀድሞ ቢዳሰስ፣**
**ቀድሞ! ቀድሞ ቢቀነጠስ፣**
**መፈልፈያው ቢደፈን፤ ሥሩ ማለዳ ቢበጠስ፣**
**የውስጥ ውስጡ የላይ ላዩ፣**
**ቃርሚያው በወጉ ቢነሳ፣**
**ባልኖረ ባልነበረ ነበር፤ የዛሬው ክምር አበሳ!**
**ይኼው ዛሬም እንዲሁ፣**
**ለቆየ ችግር "እርሾ" ሆኖ፣**
**እንደ "ጲላጦስ" አንጡኝ የሚል፣**
**የውስጡን በውስጡ ይዞ፣ ሲታዘን**
**ቀድሞ የሚስል፣**
**የችግሩ "ችግር" ይህ ነው።**
**ሽምቅታው ነው የገደለን፣**
**የሣመን ነው የነከሰን፤ የሣቀ ነው የገደለን።**

> **ይህን መሰሉ ትውልድ የዘመንን ወንዝ የሚሻገረው ለራሱ ኖሮ ብቻ ሳይሆን ለተከታዩ ትውልድም ደማቅ አሻራ በማኖር ነው**

ከላይ ማጣቀሻና የማዋዣ ስንኞችን የተዋስና ቸውን ባለቅኔዎቻችንን አመስግነን ዛሬያችንን ወደ መፈተሸ እናዝግም።

### እናስ ምን ይሁን? ከዜጎች የሚጠበቀውስ ምንድን ነው?

እርግጥ ነው ሀገሬን ያበለዛት የዛሬው ዘመን የፊት እድፍ በዓይነቱም ይሁን በመልኩ ውስብስብና ለመፍትሔውም አስቸጋሪ ሆኖብናል። ብዙ ዜጎች በስክነትና በማስተዋል የዘመኑን የፊት እድፍ በመደጋገፍ ለማጠብ ከመትጋት ይልቅ ይበልጥ ለከፉ ችግሮች ምክንያት ለመሆን ርብርብ ሲደረግ ይስተዋላል።

በችግሩ ላይ ዘምቶ ዘመኑንና ራስን ከእድፍ ከመጠበቅ ይልቅ የትናንትን ቆሻሻ "ከታሪክ ኮሲ" ላይ እየለቀሙ ካልኖሩበት ትውልድ ጋር ግብግብ በመፍጠር ይዋጣልን ብሎ መፎከር የተለመደ ክስተት ሆኗል። የትናንት ዘመን እድፍ በዛሬ ማጽጃ ሊነጻ የሚችለው በመነጋገርና በመግባባት እንጂ ነፍጥ ወልውሎ "ይዋጣልን" እያሉ መፎከሩ እንኳን ለዛሬው ትውልድ ቀርቶ ለትናንቶቹም "ዱር አደሮች" የበጀ እንዳልሆነ መረዳት አይከብድም።

በመጯጯኽና "በለው! ቁረጠው! ፍለጠው!" እየተባባልን በማሕበራዊ ሚዲያ ደን ውስጥ ተሸሽጎ መፋለሙ "በቡሃ ላይ ቆረቆር" ከማከል ውጭ ምንም ፋይዳ አይኖረውም። የብሔራዊ ችግራችን ሁነኛ መፍትሔ የትናንትን ችግር ከዛሬ ችግር ጋር እያጋቡ የከፋ ችግር እንዲፈለፈል ከማድረግ ውጭ ከቶ ምን የረባ ውጤትስ ሊገኝ ይችላል?

በሀገር ላይ የተደፈደፈው የዘመን ውርስ እድፍ ሊታጠብ የሚችለው በጠረጴዛ ዙሪያ የውይይትና የምክክር ወንበር ስቦ አድምጠኝ እኔም ላድምጥህ ሲባል ብቻ ነው። በሙሉ አቅሙ ሊንቀሳቀስ እየተሟሟቀና "ጉልበቴ በርታ! በርታ!" እያለ ባለው የብሔራዊ አካታች የምክክር ኮሚሽን ላይ ይህ ጸሐፊ ትልቅ ተስፋ አሳድሯል። ኮሚሽኑ የሀገራችንን ፊት ያጠየሙና ያቆሸሹ የውርስ ችግሮችና አዲስ በቀል እድፎችን ለማስወገድ ትልቅ ኃላፊነት እንዳለበትም ይረዳል።

የሀገሪቱ ችግሮች እንደ ንብርብር አለቶች ሲደራረቡ የመጡ ድድር እድፎች መሆናቸውን ቀድመን ካልተረዳን በስተቀር መፍትሔውን በቀላሉ ማግኘት ሊያዳግተን ይችል ይመስለናል።

ለምሳሌ፡- የዘር ማንዘር ቆጠራ ደዌ የተቆራኘንና የተጠናወተን በየትኛው ዘመንና ትውልድ ነበር? ያ "ተወቃሽ ትውልድ" ስለምን ነበር ለልክፍቱ ሊጋለጥ የቻለው? ይህ አንዱ የምክክር ኮሚሽኑ የእድፍ ማራገፊያ ርእስ ሊሆን ይችላል።

እንቀጥል፡- ስንት መከራ የተጫናት ሀገር በቋንቋ እንካ ሰላንትያ አታካራ ውስጥ ስለምን ልትዘፍቅ ቻለች? ከዚህ ላለመግባባት ካግባባን ክፉ እድፍ እንዴት መላቀቅ እንችላለን? ይኼኛው ችግራችንም በኮሚሽኑ ቅድሚያ ተሰጥቶት ቢስተናገድ እንጠላም።

እንሠልስ፡- "ይኑርልን ለክብራችን" እያልን የምንዘምርለት የሀገሪቱ ሕገ መንግሥት ዋነኛ የፊት እድፎች በየትኞቹ አናቅጽ ላይ የሚገኙት ናቸው? እናስ እድፎቹ እንዲወገዱና "የሕጎቹ አውራ" እንዲጸዳ መወያየት ያለብን እንዴትና በምን አኳኋን ነው? ሌላው ልንወያይበት የሚገባ መሰረታዊ ጉዳይ ይመስለናል።

በሀገሬ ፊት ላይ የተደፈደፈውን የዛሬውን ብሔራዊ እድፍ በአጭር ቋንቋ እንግለጸው ካልን በደል የውበት ማበልጸጊያ ሜክአፕ ይሆን ይመስል የትናንትን ቂም በሌላ በደል በመኳል ለማሽነፍ መትጋታችን ያመጣቸው መዘዞች እንዴት ሊወገዱ ይችላሉ? ሌላው የጋራ አጀንዳችን ቢሆን አንጠላም። ሊሆንም ግድ ይላል።

ጸሐፊ ተብዬዎች ምሬትን እያስተጋቡ እሪታ ካበዙ፣ ጥበብ በብሶት ተጸንሳ ብሶት ብቻ የምትወልድ ከሆነ፣ ምሁራን እየተንገፈገፉ መፍትሔውን ሳይሆን በእድፉ ጉዳዮች ላይ ብቻ እያላዘንን እንድንጮህ "ጃስ!" በማለት የሚያስደነብሩን ከሆነ፣ የፍትሕ ሥርዓቱ ኮምጥጦ የሚያኮመጥጠን ከሆነ፣ ፖለቲካው ቃዥቶ የሚያሯሩጠን ከሆነ፣ ሃይማኖቶቻችን ስክነትን ከመስበክ ይልቅ ወዮታ የሚበዛባቸው ከሆነ የሀገር እድፍ ተስፋን ያጨልም ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምንም ትሩፋት አይኖረውም።

ይህ ጸሐፊ የዛሬ ሠላሳ ስምንት ዓመት ይህንን አንጋፋ ጋዜጣ የተቀላቀለው "ሀ - በጽጌሬዳ ብእር" በሚል ርእስ በተጻፈ ሥነ ጽሑፋዊ ሂስ ነበር። ያ ዘመን እንኳንስ ስለ ጽጌሬዳ ሊጻፍ ቀርቶ ምድርና ሰማዩን የሞላው የጦርነት ዜና፣ የወጣቶች አፈሳና ዘርፈ ብዙ መከራ ፋታ የሚሰጥ አልነበረም። ጸሐፊው ለዚያ ክፉ ዘመን ተመጣጣኝ የብእር ምት ከመስጠት ይልቅ ተስፋ ማሳየቱ የተሻለ መስሎ ስለታየው እነሆ በእሾህ ለተከበበች ሀገር "ተስፋ አለሽ" ብሎ ማጽናናቱን በመምረጥ የድርሻውን ለመወጣት ሞከረ።

ዛሬም በዘመናት የንብርብሮሽ የሀገራችን ፊት በእድፍ ገርጥቶና ቅስሟ ተሰብሮ አንገት የደፋች ቢመስልም በርግጥም ተስፋ አላት። የውጭ ወደረኞቿ ስም በማጥፋት ቢዘባበቱባትም፣ የውስጥ ችግሮቻችን የተወሳሰቡ ቢመስሉም ለበጎነት ከበረታንና ተስፋችንን የማንጥል ከሆነ ያለ ምንም ጥርጥር ነጋችን የተዋበ፣ የደደረው እድፍም ለቆ የሀገሬ የፊት ማዲያት መፈወሱ አይቀርም።

ሰላም ለሕዝባችን፤ ለዜጎችም በጎ ፈቃድ።

# ተናጋሪው ዶሴ

## እኩለ ሌሊት

**ምሕረት ሞገስ**



የድሬዳዋ መልከመልካም፤ ቆንጆ ከመባልም በላይ ነች፡፡ የቀይ ዳማ ሆና፤ ፈገግ ስትል ሁለቱም ጉንጮቿ ይሰረጉዳሉ፡፡ አፍንጫዋ ሰልካካ ባይሆንም የደም ግባቷ ያየት ሁሉ እንዲመኛት ያስገድዳል፡፡ ከዘመዶቿ፣ ከጎረቤት እና ከጓደኞቿ ጋር ያላት ቅርበት በፍቅር የተሞላ፤ ሰላማዊ እና የሚያስቀና ዓይነት ነው፡፡

ወንዶችን እንደወንድሞቿ፤ ሴቶችን እንደእህቶቿ ስትቀርብ የማይወዳት እና አብሯት መዋል ማደር የማይፈልግ የለም፡፡ ብዙ ሰዎችን ለማስደሰት ትሞክራለች፡፡ በምንም መልኩ የምታቀርባቸው ሰዎች ጠላት ይሆኑብኛል ብላ አስባ አታውቅም፡፡ ከልቧ ሁሉንም ትወዳለች፤ እየተፍለቀለቀች ሁሉንም ለማስደሰት ትሞክራለች፡፡

ሴቶቹ በእርግጥም እንደእህት እንደአካባቢው ባህል አብረዋት እየበሉ፤ አብረዋት እየሳቁ እና እየተደሰቱ፤ ተሳስበው ይኖራሉ፡፡ ወንዶቹ ግን በተደጋጋሚ በወንድምነት አብረዋት ለመቆየት ይቸገራሉ፡፡ እርሷ የምትፈልገው ወንድምነትን ቢሆንም፤ መልኳ ፈገግታዋ ታክሎበት በፍቅር ይወድቃሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ብዙዎቹ በወንድምነት ሳይሆን የፆታ (የፍቅር...) ግንኙነት እንዲኖራቸው ሲፈልጉ ትሸሻቸዋለች፡፡ እርሷ ተዝናንታ ተደስታ ስትኖር፤ ከወንዶች ጋር የሚኖራት ግንኙነት ከወንድማዊነት የዘለለ እንዳይሆን ከፍተኛ ጥንቃቄ ታደርጋለች፡፡

አምሽታ መዝናናት ልማዷ ነው፡፡ ከሴትም ሆነ ከወንድ ጓደኞቿ ጋር ዘና ማለት መለያዋ ነው። ዘና ማለት የምትወደው ግን በእህትነት እና በወንድምነት ግንኙነት እየተሳሳቁ ከመጨዋወት የዘለለ አይደለም። ማክበር እና መከባበር መለያዋ ነው። ነገር ግን ደግሞ በተቃራኒው የድሬዳዋዋን ቆንጆ የአካባቢው ወንዶች ሊረዷት አልቻሉም፡፡ ዙሪያዋን ያንዣብባሉ። አንዳንዶቹ ፍላጎት እንደሌላት እያወቁ አልፎ አልፎ ሊያስገድዷት ይሞክራሉ፡፡ ለማስገደድ ሲሞክሩ እርሷም የዋዛ ባለመሆኗ ባላት አቅም ተከላክላ አስገድደው የፍቅር ግንኙነት ለመፍጠር ከሚጥሩ ወንዶች ጋር ያላትን ጓደኝነት ሙሉ ለሙሉ ታቋርጣለች። ቤቷ አታስገባቸውም፡፡ መንገድ ላይ ስታገኛቸው አታስጠጋቸውም፡፡ አንዳንዶቹ ገብቷቸው፤ተረድተዋት ይተዋታል፡፡ ሌሎች ደግሞ በተቃራኒው ጥቃት በመፈፀም እያስፈራሩ አስገድደው አብረዋት ለመቆየት ያስባሉ፡፡

### ሃኪም ጣሰው

ሃኪም ጣሰው ጀማል ጎልማሳ ነው፡፡ ሥራውን በአግበቡ ይሠራል፡፡ ሞያው የተከበረ ነውና ሁሉም ያከብረዋል፡፡ ከዚህችው የድሬዳዋ ቆንጆ ጋር የፍቅር ግንኙነት መመስረት ፈልጓል፡፡ ሆኖም ፈቃደኛ አልሆነችለትም፡፡ ጠዋት እና ማታ በቤቷ አካባቢ እያንዣበበ ስትገባ ስትወጣ ያያታል፡፡ ፍዝዝ ብሎ ቢመለከታትም፤ ነገሬ ብላ ፊት አልሰጠችውም፡፡ ቢያፈጥባትም፤ ፊቷን አዙራ አይኗን ገልጣ ለማየት ፍቃደኛ አልነበረችም፡፡ ሊያባብላት ቢሞክርም አልፈቀደችውምና እምቢ አለችው፡፡

እርሱ እየለመናት እምቢ ስትለው ሰው ላከባት። ለሰዎቹም ፍቃደኛ አልሆነችም፡፡ መልሷ ‹‹ከማንም ጋር ምንም ዓይነት የፍቅር ግንኙነት ውስጥ መግባት አልፈልግም፡፡›› የሚል ነበር፡፡ ሃኪም ጣሰው እምቢ ማለቷን ተከትሎ ሊተዋት አልቻለም፡፡ ጭራሽ ፍቅሩ ጨመረበት፡፡ በስጦታም በመለማመጥም ለማሳመን የቻለውን ሁሉ አደረገ፡፡ ነገር ግን ምላሽ ማግኘት አልቻለም፡፡

ሥራውን መሥራት ተሳነው፤ የቀንና የሌሊት ህልሙ ሆነች፡፡ በተቃራኒው እርሷ ግን ሃኪሙን ጭራሽ አታስታውሰውም፡፡ እንደለመደባት እየሳቀች እየተደሰተች ኑሮዋን ቀጥላለች፡፡ ሃኪሙ በበኩሉ ቢያንስ ሰውነቷን መንካት ከሆነለት ደግሞ ሌሎችም የሚፈልጋቸውን ተግባሮች ለመፈፀም መመኘቱን ቀጠለ፡፡ በማባባል ባይሆንለት በግድም ቢሆን ተግባሩን ለመፈፀም ማውጠንጠን ጀመረ፡፡

የመውጫ እና የመግቢያ ሰዓቷን መከታተል ጀመረ፡፡ በተለይ ስታመሽ በተደጋጋሚ ያያታል፡፡ እንዳታመልጠው ሊጨብጣት፤ በቤቷ እንዳትከለል ብብቱ ስር ከቷት ሊያድር ወደደ፡፡ ይህንን ህልሙን እውን ለማድረግ ቀን መጠበቅ ጀመረ፡፡ እርሷ ግን ጭራሽ እንደሚከታተላት ስታውቅ ጭራሽ ትጠላው ጀመረ፡፡

### መስከረም አንድ

ቀኑ የዓመቱ መጀመሪያ መስከረም 1 ነበር፡፡ የድሬዳዋ ቆንጆ የአንድ ክፍሏን መስኮት ስትከፍት የጠዋቱ የፀሃይ ብርሃን ልቧን በሃሴት ሞላው። ለወትሮም ሞቅ ደመቅ የምትለው ድሬዳዋ በዛ በበዓል ቀን የበለጠ ተሟሙቃለች፡፡ ከአልጋው ወርዳ የለሊት ልብሷን አውልቃ በግርጌ የተቀመጠውን ድሪያዋን ለበሰች። ፊቷን ታጥባ ኩሏን ከተኳለች በኋላ ከቤት ወጣች፡፡ እጣኗን እና ቡናዋን ገዝታ ወደ ቤቷ ተመለሰች፡፡

የበዓል ወጥ መስራት ጀመረች፡፡ ወጧን ሠርታ ስትጨርስ ጉዝጓዟን አሰናዳች፡፡ ቤቷን ሞቅ አድርጋ ጎረቤቶቿን ለመጥራት ቡና መቁላት ጀመረች። ቀን ከጎረቤቶቿ ጋር ማታ ደግሞ ከጓደኞቿ ጋር ለማመሻሸት አስባለችና በጊዜ የሚበሳሰለውን ከማበሳሰል አልፋ፤ በጠዋት የምትጠራቸውን ጎረቤቶቿን ጠራራች። አብረው እየተጎራረሱ በልተው፤ የሚጠጣውን ጠጥተው ሁሉም ወደየቤቱ ሲሔድ፤ እርሷ ደክሟታልና አይኗን የቤቷ ጣራ ላይ ሰክታ ካፈጠጠች በኋላ መልሳ በጎኗ ጋደም አለች፡፡

የድሬዳዋዋ ቆንጆ ቢደክማትም በዓል በመሆኑ ደስ ብሏታል፡፡ ለብሳ ለመዝናናት ከመውጣቷ በፊት ለመተኛት አሰበች፡፡ ጋደም ብላ ብዙም ሳትቆይ የጓደኞቿ የሥልክ ጥሪ ሸለብ ካደረጋት እንቅልፍ በድንገት አባነናት፡፡ አመሻሽ ላይ ለመገናኘት ተቀጣጥረው እንቅልፏን ተኛች፡፡

### እኩለ ሌሊት

ሃኪም ጣሰው ጀማል በድሬዳዋዋ ቆንጆ ቤት አካባቢ እያንዣበበ ነው፡፡ እርሷ በበኩሏ አጭር ቀሚስ፤ ረዥም ተረከዝ ያለው ጫማ አጥልቃ እና ፀጉሯን በረዥሙ ለቃ ከቤቷ ወጥታ በስልክ ጠርታ ያስመጣችው ባጃጅ ውስጥ ገብታ ወደ ጓደኞቿ ሔደች። ሃኪም ጣሰው በባጃጁ ውስጥ የሄደችውን ቆንጆ በአይኑ ሸኝቷት ወደ ቤቱ ገባ፡፡ በየአንድ ሰዓት ልዩነት እየወጣ ቢያያትም አልተመለሰችም፡፡

ቤቷ ሔዶ አንኳኳ ፤ከውስጥ መልስ አላገኘም። የቤቷ አንፖል አልበራም፡፡ መቅናት ጀመረ፡፡ ንዴት ይተናነቀው ያዘ፡፡ ጃኬት ደርቦ ቢላዋ ይዞ መንገድ መግቢያ ላይ ቆሞ መጠበቅ ጀመረ፡፡ ሰዎች ሲመጡበት ወደ ጨለማው ገባ ብሎ ቢላዋውን ጃኬቱ ሥር ከቶ ዚፑን ዘጋ፡፡ እጁን ኪሱ ውስጥ ከቶ መጠበቁን ቀጠለ። የድሬዳዋዋ ቆንጆ ወደ ቤቷ አልተመለሰችም፡፡

ወጣ ብለው የነበሩ ጎረቤቶቿ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ሃኪም ጣሰውን ቆሞ ማየታቸው ጥርጣሬ አሳድሮባቸዋል፡፡ ሃኪሙን ወጣ ብለው በድጋሚ ሲመለከቱት ወደ ቤቱ አልገባም፡፡ አንዳች ነገር አስቦ ሊሆን እንደሚችል ጠርጥረዋል፡፡ ሰዓቱ እየገፋ እኩለ ለሊት ሆነ፡፡

### ከመዝናናት መልስ

መሽታ ቤት ስትዝናና የቆየችው የድሬዳዋ ቆንጆ እንደልማዷ ለጓደኞቿ ወደ ቤቷ መሔድ እንደምትፈልግ ነገረቻቸው፡፡ እንሸኝሽ ብለው ተከተሏት፡፡ ከሩቅ ቆንጆዋን የያዘ ባጃጅ እየመጣ መሆኑን የጠረጠረው ሃኪም ጣሰው ወደ ጥግ በመጠጋት ራሱን ጨለማ ውስጥ ከቶ ላለመታየት ሞከረ፡፡ ሸኚዎቿ ልብ አላሉትም፡፡ እርሷም አላየችውም፡፡ እርሷን እና ሸኚ ጓደኞቿን ይዞ የነበረው ባጃጅ እርሷን አውርዶ በፍጥነት ከአካባቢው ሲርቅ ሃኪም ጣሰው ቆንጆዋን ተከተላት፡፡

የድሬዳዋዋ ቆንጆ ብዙም በእግሯ ሳትራመድ ከጀርባዋ በጠንካራ እጅ አፏና አፍንጫዋ ታፈነ። በእጇ ለማስለቀቅ ብትሞክርም አልቻለችም። ምራቋ አነቃት። እንደምንም እየተንፈራፈረች እጇን እያወራጨች ጠንካራውን እጅ ከአፍንጫዋ እና ከአፏ ለማስለቀቅ ሞከረች፡፡ ቢላዋውን ወደ አንገቷ ሲያስጠጋው አይኗ ፈጠጠ፡፡ በድንጋጤ ከመንቀጥቀጥ ይልቅ ድርቅ አለች።

ሃኪም ጣሰው ይወዳታልና ሳሳላት፤ መጨከን አልቻለም፡፡ ይልቁኑ ቢላዋውን ጥሎ፤ አፍና አፍንጫዋን ያፈነበትን እጁን አንስቶ አጭሩን ቀሚሷን ሲገልብ እየተንቀጠቀጠች ኡኡታዋን አቀለጠችው። ከየአቅጣጫው ጎረቤቶቿ በራቸውን እየከፈቱ ሲወጡ፤ ሃኪም ጣሰው እግሬ አውጪኝ ብሎ ፈረጠጠ፡ ፡ ቆንጆዋ ግን በድንጋጤ እየተንቀጠቀጠች ግድግዳ ተደግፋ ተቀመጠች፡፡ ሰዎች ተሰበሰቡ። የሆነውን ሲጠይቋት በሚንቀጠቀጥ ድምፅ ከሞት ማምለጧን እና ሃኪም ጣሰው ሊደፍራት ሲሞክር እንደነበር ተናገረች፡፡ የአካባቢው ወጣቶች ሃኪሙን ለማግኘት ሮጡ፡፡ ነገር ግን ሊያገኙት አልቻሉም፡፡ ፖሊስ ጣቢያ ሔደው አመለከቱ፡፡

### የፖሊስ ምርመራ

በማግስቱ ማለትም መስከረም 2 ፖሊስ የተፈፀመውን ወንጀል በተመለከተ የደረሰውን ጥቆማ ተከትሎ የቆንጆዋን ቃል ተቀበለ፡፡ ሃኪም ጣሰው ለቀናት ከመሰወር አልፎ ከተማዋን ለቆ ለመውጣት ቢያስብም እንዳሰበው አልሆነም፡፡ ብዙ ቀናቶች ሳይቆጠሩ ያለበት ታወቀ፡፡ ፖሊስ እና የአካባቢው ሕብረተሰብ በመረባረቡ ብዙም ሳይቆይ ቆንጆዋን ልጅ እጁ ለማስገባትም ሆነ አቅፎ ለማደር፤ እንዲሁም የፈፀመውን ወሲባዊ ጥቃት ተከትሎ ከሚመጣበት ተጠያቂነት ለማምለጥ ያደረገው ሙከራ ሁሉም ሳይሳካለት ቀረ፡፡

ህብረተሰቡ ከፖሊስ ጋር በመተባበር ብርቱ ክትትል በማድረጉ ሃኪም ጣሰው ጀማል በቁጥጥር ስር ለማዋል ቻለ፡፡ በድሬዳዋ ከተማ ቀበሌ ዜሮ ሶስት ልዩ ስሙ ዲፖ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ከለሊቱ ሰባት ሰዓት የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ሊፈፅም የነበረ ግለሰብ በቁጥጥር ውሏል በሚል ፖሊስ የምርመራ መዝገብ አሰናዳ፡፡

የድርጊቱን ሁኔታ ከሳሽ የድሬዳዋ ቆንጆ አስረዳች።ተከሳሽ ሃኪም ጣሰው ጀማል ቢላዋ ይዞ ተዝናንታ ወደ ቤቷ ስትገባ በጨለማ ተሸሽጎ የያዘውን ቢላዋ ወደ አንገቷ አስጠግቶ የአስገድዶ መድፈር ሙከራ ሊያደርግ መሞከሩን ገለፀች፡፡ ፖሊስም ድርጊቱን ተጠርጣሪው ስለመፈፀሙ አረጋገጠ፡፡

### ውሳኔ

ፖሊስ እና አቃቤ ህግ በጋራ ያጣሩትን የምርመራ መዝገብ ለድሬዳዋ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቀረቡ፡፡ ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን መረጃ ተመርኩዞ፤ የግራ ቀኙን ክርክር ከተከታተለ በኋላ መስከረም 23 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተከሳሽ ጣሰው ጀማል ጥፋተኛ ነው ሲል ብይን ሰጠበት፡፡ በመጨረሻም የድሬዳዋ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰባት ዓመት ከ3 ወር እስራት ወሰነበት፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## አለመታመም ጤነኛ አያስብልም!

**ቦጋለ አበበ**

ትናንት ከጎናችን የነበሩ ብዙ ሰዎች ዛሬ እንደዋዛ ተለይተውናል። ጠዋት በሰላም በጤና አብረውን ሲሰሩ፣ሲጫወቱ ወዘተ የነበሩ በርካቶችን ከሰአት በኋላ እንደ ጤዛ ያጣንበት አጋጣሚ ቤቱ ይቁጠረው። ማታ ደህና እደር ተባብለውና ነገ ለመገናኘት ቀጠሮ ይዘው የተለያዩትን ወዳጅ ህይወት ማለፍ ጠዋት የተረዱ ጥቂት አይደሉም። ብዙዎቻችን እንዲህ አይነት አስደንጋጭ ነገሮች ሲገጥሙን የምንደርስበት ድምዳሜ ይለያያል። አንዳንዶቻችን እንደ ፈጣሪ ቁጣ ልንቆጥረው እንችላለን። ሌሎች ደግሞ ሌላም ሌላም ነገር ሊያስቡ ይችላሉ።

የህክምና ባለሙያዎች ብዙ ጊዜ የሚሉት ነገር አለ፤ ‹‹አለመታመም ጤነኛ መሆን ማለት አይደለም።›› እውነት ነው። ትናንት አንድም የጤና እክል ያላየንባቸው ሰዎች ዛሬ ህይወታቸው አልፎ ስናይ ጤነኞች ነበሩ ብለን መደምደም በራሱ ጤናማ አይደለም። ብዙዎቻችን አሁን ላይ ሙሉ ጤንነት ላይ እንደሆንን ሊሰማን ይችላል፣ ነገር ግን ጤነኞች ነን ምንም የጤና እክል የለብንም ማለት አይደለም። ይህን ደግሞ ሳይንሱም ቢሆን እንደሚደግፈው አይጠፋንም።

ብዙዎቻችን ወደ ሕክምና ማእከላት የምንሄደው ሕመም ሲሰማን ወይም አንዳች የጤና እክል ሲገጥመን ነው። ይህም መሆኑ አንዳንድ ሕመሞች በጊዜ ሳይደረስባቸው ይቀራል። ከዛም በላይ በቶሎ መሻሻል እንዳይኖር ሊያደርግና ከፍተኛ ወጪንም ሊያስወጣ ይችላል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የብዙዎችን ሕይወት እየቀጠፈ የሚገኘውና እጅግ አሳሳቢ የሆነው የኩላሊት ሕመም ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል፡፡ ሃኪሞች እንደሚናገሩት የሰው ልጆች ኩላሊት ሁለቱም ተዳክሞ ሃያ አምስት በመቶ እስኪቀር ድረስ አንድም ምልክት ላይታይ ይችላል፡፡ ድንገት ግን እዚያ ደረጃ ላይ በደረሰ ሰዓት ህይወት ለመንጠቅ ጊዜ ላይፈጅበት ይችላል፡፡ ለዚህም ነው ብዙዎች የዚህ ህመም ተጠቂ መሆናቸውን ባወቁ በቀናት ልዩነት አይሆኑ ሆነው ከአልጋ ቁራኛነት እስከ ህይወት ማጣት የሚደርሱት፣ ህመሙ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ከደረሰ በኋላ ያለ የሌለ ሃብታቸውን አሟጠው ከፍተኛ የህክምና ወጪ በማውጣት ለመዳን ሲጥሩ የሚታዩት፡፡ እንዲህ አይነት የጤና ችግሮች አሳሳቢ ደረጃ ላይ ከመድረሳቸው አስቀድሞ በየጊዜው በሚደረግ የጤና ምርመራ መታወቅ ቢችሉ ህይወትን እስከ ማጣት የሚያደርሰውን አደጋ በብዙ እጥፍ መቀነስ ይቻል ነበር፡፡

ይህን ለመከላከል እንዲቻል የጤና ባለሙያ ዎች የሚመክሩት ዓመታዊ የሆነ የጤና ምርመራ ማድረግን ነው። ይህም ከስር ከስር ሰዎች የጤናቸውን ሁኔታ እንዲከታተሉና በቶሎ እርምጃ እንዲወስዱ ያስችላቸዋል ተብሎ ይታመናል። ይህ ተደጋግሞ የሚነገረንና የምናውቀው ጉዳይ ቢሆንም ግን ተግባር ላይ የለንበትም። ግንዛቤውና መረጃው ቢኖረንም ባህሉን አላዳበርነውም፡፡

መደበኛ የጤና ምርመራ በምን ያህል ጊዜ ልዩነት መካሄድ አለበት ወይም ቢካሄድ ጥሩ ነው የሚለው ላይ የጤና ባለሙያዎች በተለያየ ጊዜ የተለያየ አስተያየት ሲሰጡ ይደመጣል። በትንሹ በዓመት አንድ ጊዜ ጠቅላላ የጤና ምርመራ ማድረግ እንደሚመከር ግን በርካቶቹ ይመክራሉ።

ዓመታዊ የጤና ምርመራ ማድረግ እንደ ካንሰር እና አንዳንድ በቅድመ ጥንቃቄ ልንከላከላቸው የምንችላቸውን ሕመሞች ለመቆጣጠር ያግዛል። ዓመታዊ የጤና ምርመራ ማድረግ እንደ ቅድመ መከላከል ይቆጠራልም ይባላል። በዚህም ተከታታይነት ያለው ምርመራ ስለሚደረግ፣ ብሎም የቤተሰብ የጤና ታሪክ፣ የግል የአኗኗር ሁኔታና የመሰለው ስለሚነሳ፣ ከጤና ጋር በተገናኘ ያሉ ስጋቶች አብረው ሊነሱ ይችላሉ። ከዚህና ከሚደረጉ ምርመራዎች በመነሳትም የጤና ባለሙያዎች በቀላሉ ሊደርሱ ይችላሉ የሚባሉ የጤና እክሎችን ቀድመው መከላከል የሚያስችሉ ዘዴዎችን ተግባራዊ ያደርጋሉ። ከዛም ባለፈ አንድ ሰው ተላላፊ ላልሆኑ (በዘር ሊተላለፉ ለሚችሉ) በሽታዎች ያለውን የተጋላጭት ስጋት ለመለየት ያስችላል። ይህም ምልክቶች በብዛትና በስፋት ሳይታዩ አስቀድሞ በሽታው በቶሎ እንዲለይ እና ሕክምና በቶሎ እንዲሰጥ ያስችላል። ይህም በሽታው ሊያደርስ የሚችለውን የከፋ ጉዳት በከፍተኛ መጠን ለመቀነስ የሚያግዝ ነው።

ከዚሁ ሳይርቅ፤ የተገኘ ወይም ምልክት የታየበት በሽታ ላይ ፈጣንና ተከታታይ የሆነ የጤና ክብካቤ እርምጃና የሕክምና መፍትሔ ለመስጠት ይጠቅማል። በቶሎ መደበኛ ሕክምና ጀምሮ ወደ ቀደመ ጤንነት ለመመለስም በእጅጉ ይረዳል። ‹ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ› እንዲሉ፤ ወቅትን ጠብቆ የጤና ምርመራ ማድረግ የግል ለውጥን ለመከታተልና ጤናማ የሆነ የአኗኗር መንገድን ለመከተል ትልቅ ሚና አለው። ለምሳሌ ጤናማ አመጋገብን በተመለከተ ከጤና ባለሙያ ተገቢውን ምክር ለማግኘት ብሎም ቀድሞ በማንኛውም አጋጣሚ የተደረገ ምርመራንና የምርመራ ውጤት ያለበትን ሁኔታ ለመከታተል ያግዛል። መድኃኒት እየወሰደ ያለ ወይም ቀደም ብሎ መድኃኒት የወሰደ ሰውም ጤናው ያለበትን ደረጃና ለውጡን ለመከታተል ያስችለዋል።

ከዚህም ሁሉ በላይ ደግሞ ስጋትን ይቀንሳል። ራሴን፣ ወገቤን፣ ጎኔን ወዘተ ያመኛል የሚልና መሰል የተለያዩ ምልክቶችን የሚያይ ሰው፣ የሕመሙ ምክንያት ምን ሊሆን እንደሚችል በመገመት ከመጨነቅ፤ ጥርጣሬዎችን ለማጥፋት እንዲህ ያለው የጤና ምርመራ ክትትል ትክክለኛውን የጤናውን ሁኔታ እንዲረዳ ያስችለዋል።

ይህንን እና መሰል ዓመታዊ የጤና ምርመራ ለማድረግ የገንዘብ አቅም አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡ በትንሽ ገንዘብ ጤና ጣቢያ ሄዶ ሙሉ ምርመራ ማድረግ ይቻላል፡፡ ገንዘብ ይጠይቃል ቢባል እንኳን በኋላ ሕመም ሰውነት ላይ ሲሠለጥን ለመታከምና ለመዳን ከሚያስፈልገው ወጪ አንጻር ግን አነስተኛ ነው። ስለዚህም ለቅድመ ጥንቃቄ የሚያግዝ በመሆኑ በቅናሽ ዋጋ ምርመራ አገልግሎት በሚሰጥባቸው የጤና ጣቢያዎችና የሕክምና ማእከላት በተቻለ አቅም አገልግሎቱን ለማግኘት ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነውና እናስብበት፡፡

# ዓስም አቀፍ

## የአውሮፓ ህብረት የዩክሬን ስንዴ ወደአምስት የህብረቱ ሀገራት እንዳይገባ አገደ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የአውሮፓ ህብረት የዩክሬን ስንዴ እና ሌሎች የጥራጥሬ ምርቶች ፖላንድን ጨምሮ ወደ አምስት ሀገራት እንዳይገባ እገዳ ጥሏል።

የዩክሬን ስንዴ እና ሌሎች ጥራጥሬ ምርቶች በርካሽ ዋጋ ወደ ተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት መግባቱን ተከትሎ ነበር ተቃውሞ የተሰማበት። በተለይም የፖላንድ፣ ሮማኒያ፣ ቡልጋሪያ፣ ሀንጋሪ እና ስሎቬኪያ ገበሬዎች በዩክሬን ስንዴ ምክንያት የምርቶቻቸው ዋጋ ቀንሶብናል በሚል በተቃውሞ ላይ ነበሩ።

የአውሮፓ ህብረትም ከገበሬዎቹ የቀረበውን ተቃውሞ ምክንያት በማድረግ የዩክሬን ስንዴ እና ሌሎች የጥራጥሬ ምርቶች እንዳይገቡ እገዳ አስተላልፏል ሲል ዩሮ ኒውስ ዘግቧል። የአውሮፓ ህብረት እገዳም እስከ ቀጣዩ መስከረም ወር ድረስ ይቆያል የተባለ ሲሆን፤ ኪቭ ምርቶቿን ተቃውሞ በተነሳባቸው አምስት ሀገራት ላይ ከማጓጓዝ ውጪ መሸጥ አትችልም ተብሏል።

ዩክሬን እስካሁን በጉዳዩ ዙሪያ ምላሽ ያልሰጠች ሲሆን፤ በተመድ እና ቱርክ አደራዳሪነት የግብርና ምርቶቿን በጥቁር ባህር በኩል ለዓለም ገበያ በማቅረብ ላይ ትገኛለች ሲል የዘገበው አልዓይን ኒውስ ነው።




## ቨርጅን ጋላክቲክ ለጉብኝት ወደጠፈር የሚደረግ በረራ ሊጀምር ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በጠፈር ቱሪዝም ላይ የተሰማራው የእውቁ ባለሃብት ሰር ሪቻርድ ብራንሰን ቨርጅን ጋላክቲክ ኩባንያ ከሁለት ሳምንታት በኋላ ለጉብኝት የሚደረገውን የመጀመሪያውን የጠፈር በረራ እንደሚጀምር አስታወቀ።

ኩባንያው ጋላክቲክ 01 ሲል የጠራውን በረራ ከሰኔ 20 እስከ 23 2015 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ለማድረግ መወሰኑን ገልጿል። ይህን ውጥን ይፋ ሲያደርግ የቨርጅን ጋላክቲክ የገበያ ድርሻው 40 በመቶ ተመንድጓል። ባለፈው ወር የዩኬው ባለሀብት ሪቻርድ ብራንሰን ቨርጅን ኦረቢት የተባለ ሌላ ኩባንያ ተልዕኮዎቹ ከተጨናገፉ ከወራት በኋላ ተዘግቷል።

ቨርጅን ጋላክቲክ ኩባንያ በመጀመሪያ በረራ ሳይንሳዊ ጥናት የማድረግ ተልዕኮ አለው። በዚህ በረራ የሚካተቱት የቡድን አባላት ከጣልያን አየር ኃይልና ከጣልያን ብሄራዊ ጥናት ማዕከል የሚመጡ ተጓዦች ሲሆኑ ‘ማይክሮግራቪቲን’ ያጠናሉ ተብሏል።

ኩባንያው ከዚህ የመጀመሪያ ጉዞ በኋላ ቀጣዩ በረራ ሃምሌ ላይ የሚደረግ ሲሆን፤ ከዚያም በኋላ በየወሩ በረራ እንደሚደረግ ይጠበቃል። ይህ የጠፈር በረራ 19 ዓመታትን ላስቆጠረውና በቴክኒክ ችግሮች እንዲሁም ተከታታይ አደጋዎች ላጋጠሙት ቨርጅን ጋላክቲክ ጉልህ ለውጥ ይሆናል።

ባለፈው ወር የኩባንያው ‘ዩኒቲ’ ተብሎ የተጠራ የሮኬት አውሮፕላን ከሁለት ዓመታት በኋላ ወደ ስራ ተመልሷል። ሁለት ፓይለቶችን እና አራት ተሳፋሪዎችን ይዞ የነበረው ሮኬት ከአሜሪካዋ ኒው ሜክሲኮ በርሃ ተወንጨፎ ተመልሷል። ይህ በረራ ለረጅም ጊዜ ሲጠበቅ የነበረው የንግድ አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት የተደረገ ሙከራ ነው።

ቨርጅን ጋላክቲክ እስካሁን ከምድር 80 ኪሎ ሜትር ከፍ ብለው መብረር ለሚፈልጉ ከ800 በላይ ሰዎች ትኬት ሸጧል። በዚህ በረራ የሚካተቱ ተጓዦች ምድርን ከላይ ሆነው የሚመለከቱ ሲሆን፤ ለጥቂት ደቂቃዎች የመሬት ስበት በሌለበት ቦታ ደርሰው ስሜቱን ይጋራሉ። ይህ ጉዞ በአንድ ሰው 450 ሺህ የአሜሪካ ዶላር ይከፈልበታል።

ቨርጅን ጋላክቲክ የጠረፍ ቱሪዝም ላይ ቢያተኩርም የሰር ሪቻርድ ኩባንያ በቨርጅን ኦርቢት አማካኝነት የሳተላይት ሮኬት የማስወንጨፍ እቅድም ነበረው። ሆኖም ቨርጅን ኦርቢት ባለፈው ወር ባጋጠመው የተልዕኮ መጨናገፍ ምክንያት ተዘግቷል። ይህም በዩኬ የጠፈር ዳሰሳ ትልቅ ለውጥ ሆኗል። በዚህ ዓመት መግቢያ ላይ ኩባንያው ሳተላይት እንደሚያመጥቅ ሲጠበቅ የነበረ ቢሆንም የገንዘብ አቅሙን ለማሳደግ ስራዎቹን አቁሞ ቆይቷል።

ሰር ሪቻርድ ባለፈው ወር ለቢቢሲ በሰጠው ቃለ መጠይቅ በግሉ የ1.9 ቢሊዮን ዶላር ኪሳራ እንደገጠመው ገልጿል። ባለሀብቱ የዚህ ኪሳራ መነሻ በኮቪድ 19 የእንቅስቃሴ ገደብ ምክንያት የአየር መንገድና የመዝናኛ ንግዶቹ ያጋጠማቸው ኪሳራ እንደሆነ



አመላክቷል።

“ሁሉንም ነገር እናጣለን ብዬ ያሰብኩበትም ጊዜ ነበር” ሲልም አክሏል። ሆኖም ሰውዬው ቢሊየነር ሆኖ መቆየት ችሏል። ባለፈው ዕሁድ የወጣው የታይምስ ባለጸጎች ዝርዝር ሰር ሪቻርድ ብራንሰን 2 ነጥብ 9 ቢሊዮን ዶላር የተጣራ ሀብት አለው ሲል የዘገበው ቢቢሲ አማርኛ ነው።

ማህበራዊ

# መጋቢ አዕምሮ

## ህይወት ቀያሪ የጠዋት ፅባዮች

አስናቀ ፀጋዬ



‹‹ዛሬ ደግሞ ተጫጭኖኛል፤ እንቅልፍ እንቅልፍ ብሎኛል›› እያሉ እንዲሁ ግዜያቸውን በከንቱ የሚያሳልፉ ብዙዎች ናቸው:: እነዚህ ሰዎች በጠዋት መነሳት አይሆንላቸውም:: ማልደው ባለመነሳታቸው ስራቸውን በሰአቱና በአግባቡ አይከውኑም:: ይነጫነጫሉ:: ስልቹ ናቸው። ድብርትም ያጠቃቸዋል:: በህይወቱ ስኬት እንዲመጣ የሚያስብ ሰው ግን እነዚህን ነገሮች ማስወገድ የግድ ይለዋል:: ሰው በእያንዳነዱ ቀን የሚኖረው ብርታት ተጠራቅሞ ነው የሚፈለገውን ነገር ማሳካት የሚቻለው:: ቀንን የሚወስነው ደግሞ የጠዋት ክንውን ነው::

ፈረንጆች ‹‹first impression is last impression›› ይላሉ:: ‹‹ጅማሬህ ፍፃሜህን ይወስነዋል›› እንደማለት ነው:: ለመሆኑ ቀናችን ላይ ባለስልጣን የሆነው የጠዋት ልምዳችን ምን መምሰል አለበት? የተሳካና የሚያስደስት ጠዋት ቢኖረን በቀን ውስጥ ከሚሰሙን መጥፎ ስሜቶች ውስጥ አብዛኛዎቹን የመቀነስ እድል ይኖረናል::

በጠዋት ተነስተን ማንኛውንም ነገር ማከናወን ሞት መስሎ የሚታየን ብዙ ሰዎች ልንኖር እንችላለን። ግን አንድ ሰአት ቀድመን ተነስተን ያለንን አንድ ህይወት ማሳማር መቻል በራሱ ትልቅ ስኬት ነው:: በማለዳ ተነስተን ማድረግ ያለብንና ለህይወታችን እጅግ ጠቃሚ የሆኑ አስር ፀባዮች የሚከተሉት ሲሆኑ ቀጥሎ ከሚዘረዘሩት አስር ፀባዮች ውስጥ ስንቶቹ የእናንተ ፀባይ እንደሆኑ ልትለዩ ትችላላችሁ። የወደዳችሁትን ደግሞ መርጣችሁ ፀባያችሁ ታደርጉታላችሁ።

### 1ኛ. ቀደም ብሎ መነሳት

ማልዶ መነሳት የብዙ ስኬታማ ሰዎች ፀባይ ነው:: ከሞቀ እንቅልፋችን ለመነሳት ያለውን ትግል ለማሸነፍ አላርማችንን ሞልተን እንተኛለን። ሆኖም አላርሙ በጮኸ ቁጥር ስንቴ ነው ተነስተን አጥፍተን የምንተኛው? የመነሳት ጉጉት እንዲኖርህ የሚያደርግ አላማና አስተሳሰብ ከሌለህ አእምሮህን አሳምኖ መንቃት የማይታሰብ ነው:: ከዚህ በፊት እኮ የምትወደውንና የምታከብረውን ሰው ቀጥረህ በጠዋት ተነስተህ አግኝተኸው ታውቃለህ:: አንዳንዴ ወሳኝ ጉዳይ ሲኖርህም በጠዋት ተነስተህ ታውቃለህ:: ትልቁ ችግር ወጥነት ባለው መልኩ በየቀኑ በጠዋት አትነሳም የሚለው ነው።

ስለዚህ ሁልግዜም አይምሮህን የሚያባንነው ጉዳይ ቢኖር ትነሳለህ ማለት ነው:: ለዛም ነው የሚያባንንና በጠዋት የሚያስነሳ ዓላማ እንዲሁም የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅድ የሚያስፈልግህ። ለምሳሌ የሚጮኸውን አላርም በመጠኑ ብታርቀው በጠዋት ለመንቃት በመጠኑ ይረዳሃል። ምክንያቱም አላርሙ ሲጮህ በጠዋት ተነስተህ ለማጥፋት የምታደርገው እንቅስቃሴ ሰውነትህን ስለሚያነቃቃው በዛው እንድትነቃ ሊያደርግህ ይችላል::

### 2ኛ. ብርሃን ማግኘት

ብርሃን የመነቃቃት ስሜትን ስለሚፈጥር በጠዋት እንደተነሳን መስኮት የመክፈትና ብርሃን ወደመኝታ ቤታችን የማስገባት ልምድ ሊኖርን ይገባል:: ብርሃንን መመልከት ስንል ግን ቀጥታ ፀሃይን ማየት ማለት አይደለም። ነገር ግን መስኮታችንን ከፍተን የምናገኘው ወይ ደግሞ መንገድ ላይ ስንሄድ የምናየውን ብርሃን ማለት ነው።አንዳንድ ጊዜ ቤት ውስጥ ስንውል በቂ ብርሃን ላናገኝ እንችላለን:: ስልክ ወይም ኮምፒዩተር ላይ ግዜያችንን እናጠፋለን:: ቆይተን ከአልጋችን ተነስተን የሚኖረን ስሜት ግን የመደበር ስሜት ነው። ምንአልባት ግን ከሰአት ያንን በቂ ብርሃን ካገኘን እንነቃለን:: ችግሩ ግን ሰውነታችን ይህን ኡደት ተከትሎ ሲሄድ ማታ በጊዜ ለመተኛት ይቸግረናል:: ምክንያቱም በቂ ብርሃን በሰአቱ ስላላገኘንና ኡደቱን ስላዛባነው የመተኛትና የመንቃት ሰአታችንም አብሮ ይዛባል። ስለዚህ ጠዋት እንደተነሳን በቂ ብርሃን ማግኘት ተአምረኛ የሆነውን ሰውነታችንን የመንቃት ሂደቱን ያስተካክለዋል።አርፈደን ተነስተን የቤትን ብርሃን ዘግተን ከዋልን ግን የድብርት ስሜቶች እኛ ጋር ተሰባስበው መኖር ይጀምራሉ:: ለነገሮች ፍላጎት እንድናጣ፤ አንዳንዴም ህይወት ጣዕም እንዳይሰጠን ያደርገናል:: ተፈጥሮ በፀሃይ በኩል የምትሰጠንን ጥቅም ማባከን የለብንም:: የጠዋት ብርሃን ያስፈልገናል::

### 3ኛ. ራስን ለማንቃት መሞከር

ሁሉም ሰው ከእንቅልፉ ከነቃ በኋላ ራሱን ለማንቃት የሚያደርገው የተለያዩ ልማዶች ይኖሩታል:: ለምሳሌ ስመጥሩ ባለፀጋ ኤሎን መስክ ‹‹ህይወቴን የቀየረው አንድ ልምድ ቢኖር በጠዋት እየተነሳሁ የምወስደው ቀዝቃዛ ሻወር ነው›› ይለናል። እነ ኦፕራ ዊንፍሬይና ሌሎችም ታላላቅና ዝነኛ መንፈሳዊ ሰዎች ደግሞ ‹‹በጠዋት ተነስቼ በህይወቴ የተደረጉልኝን አምስት ነገሮችን ፅፌ ሳመሰግን ቀኔ እጅጉን ብሩህ ይሆናል›› ይሉናል::

በጠዋት ከተነሳን በኋላ ቀን ላይ እሚሰማን አይነት ንቃት አይኖረንም:: ለጥቂት ጊዜ እንቅልፍ እንቅልፍ ይለናል:: እንደተነሳን ያለውን የእንቅልፍ ስሜት ለማጥፋት የሚረዳን የሰውነት እንቅስቃሴ ነው:: የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ስናደርግ የልብ ምታችንና የሰውነት የደም ዝውውራችን ጨምሮ ሰውነታችን ይበልጥ እንዲነቃቃ ያደርገዋል:: ቀዝቃዛ ሻወር መውሰድም ሰውነትን ለማነቃቃት ይረዳል::

### 4ኛ. በቀን ውስጥ የሚደረጉ ነገሮችን ዝርዝር ማውጣት

በማንኛውም እንቅስቃሴያችን ውስጥ መዳረሻችንን ማወቅ አለብን:: ወዴት እንደሚወስድ የማታውቀው ታክሲ ውስጥ ዘው ብለህ አትገባም:: በቀን ውስጥ የምናደርገውን ማንኛውንም ነገር ጠዋት ማወቅ አለብን:: ይህ ማለት የቀኑን አላማችንን ጠዋት አውቀን መነሳት ማለት ነው:: ይህን ዝርዝር ስናወጣ የቀን መነቃቃት ራሱ ይጨምርልናል::

ታዲያ እነዚህ ዝርዝሮች ላይ የምናስቀምጣቸው ተግባሮች ልምድ ልናደርጋቸው የምንችላቸው መሆን አለባቸው:: ለምሳሌ አንድ ፀሃፊ ተነስቶ ዛሬ ጥሩ ፅሁፍ እጽፋለሁ ካለ ግልፅ አይደለም:: በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ሁለት ገፅ እጽፋለሁ ቢል ግን ለመተግበር ቀላል ይሆንለታል:: ልክ እንደዚህ በየትኛው የስራ ዘርፍ ላይ ብትሆን ማድረግ የምትፈልገውን ነገር ለመተግበር በሚመች መልኩ አስቀምጠው። በተለይ ግልፅና አጠር አድርገህ ከፃፍከው ማታ ላይ እንዳሳካኸውና እንዳላሳካኸው ለመመዘን ይረዳሃል::

### 5ኛ. ከራስ ጋር ንግግርና ምስላዊ እይታ

በጠዋት ተነስተን ለራሳችን የምንነግራቸው ነገሮች ውሏችን ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ አላቸው:: ነጋዴው ዛሬ ሁለት መቶ ብር እሰራለሁ፣ መፅሐፍ አንባቢው ዛሬ ስልሳ ገፅ አነባለሁ ሊል ይችላል። ለራሳችን ደጋግመን የምንነግረው ነገር በውሏችን ውስጥ መከወኑ የማይቀር ነው:: ስለዚህ አወንታዊ የሆኑትንና ዛሬ አደርጋለሁ የሚሉ ማረጋገጫዎችን ለራሳችን እንሰጣለን::

እነዚህን እቅዶች አሉታዊ በሆኑ መንገዶች መግለፅ ግን ተገቢ አይደለም:: ለምሳሌ ‹‹ዛሬ አላረፍድም›› ብንል ሃሳባችን ትክክል ነው:: ነገር ግን አላደርግም ከሚለው ሃሳብ ይልቅ አደርጋለው ወደሚለው ብናመዝን ለአእምሮ ያለው አወንታዊ ጫና ከፍተኛ ይሆናል:: ሌላው ጥሩ ልማድ የሚባለው ደግሞ አደርጋለሁ የምንላቸውን ነገሮች በአእምሯችን መሳል ነው:: እነዚህን ስእሎች በአእምሯችን ውስጥ ስንፈጥር ‹‹visualization›› ይሰኛል::

በርካታ እውቅ ተመራማሪዎች ሊሰሩ ያሰቡትን የፈጠራ ውጤት በጭንቅላታቸው ውስጥ በማመላለስ እያዩት ካሰቡበት ይደርሳሉ:: እኛም ጠዋት ከተነሳን በኋላ የምናደርገውን ነገር ማወቅ ብቻ ሳይሆን በምስል አእምሯችን ውስጥ ማመላለስ አለብን:: ምክንያቱም ምስሎችን አእምሯችን ውስጥ መፍጠር ከቻልን መሬት ላይ ማውረዱ ከባድ አይሆንም::

### 6ኛ. አመስጋኝ መሆን

ገና እንደተነሳን ‹‹ደሞ ነጋ ወደዛ ስራ፣ ወደዛ አስቀያሚ ትምህርት ልሄድ ነው›› እያልን እያማረርን ከእንቅልፋችን እንነሳ ይሆናል:: እዚህ ጋር ግን አንድ ነገር አስታውሱ! ስራ የሌለው፣ ትንሽ እንኳን ገቢ የሌለው፣ ከሰው የሚጠብቅ፣ ኑሮ የመረረው በሚሊዮኖች የሚቆጠር ሰው ሞልቷል:: በጦርነት፣ በችግርና በድህነት ምክንያት ሳይማር ቤቱ የቀረ በሚሊዮን የሚቀጠር ህዝብ እንዳለም አትዘንጋ::

በመንገድ ስታልፍ እኮ ‹‹ምን አለ እንደዚህ ሰውዬ የምሰራው፤ የምማረው ነገር ብትሰጠኝ›› እያለ ፈጣሪውን የሚጠይቅ ብዙ ሰው ነው:: ቀድሞውኑ ለመንቃት መቻል በራሱ ትልቅ ማመስገኛ ነው። መንቃት ማለት አይንን መግለጥ ብቻ አይደለም። አይናችንን በገለጥንበት ቅፅበት ሰውነታችን እጅግ ብዙ ስራዎችን ያከናውናል:: ይህንን ሁሉ በተሳካ ሁኔታ አልፎ መነሳትን አለማመስገን አይቻልም:: ስለዚህ በተሰጠህና ባለህ ነገር አመስጋኝ ሁን::

### 7ኛ.ዝምታ

በጠዋት ቀድመን ስንነቃ ከሚን ጫጫው፤ ከሚተራመሰው ዓለም ነፃ የሆነ የራሳችን ጊዜ ይኖረናል። በቀን ውስጥ ልናገኘው የማንችለው የራስ ጊዜ እናገኛለን:: የሰው ልጅ ለማንኛውም ውሳኔ ቅድሚያ ከራሱ ጋር ማውራት አለበት:: ለዚህ ደግሞ ዝም ያለና የተረጋጋ ግዜ ያስፈልጋል። አትርሳ! ህይወት በውሳኔ የተሞላች ነች:: ያንተን ውሳኔ የሚጠብቁ ብዙ ጉዳዮች አሉ:: ስለዚህ ሁሌም ጠዋት ስትነቃ በዝምታ ውስጥ ሆነህ ከዚህ የጫጫታ ዓለም ርቀህ ማሰብ መቻል አለብህ::

### 8ኛ. የኔ ከምንላቸው ሰዎች ጋር ማውራት

ቢያንስ ለአስር ደቂቃ ከራስህ ጋር ከተነጋገርክ በኋላ ከምትወዳቸው ሰዎች ጋር ደግሞ መገናኘት አለብህ። የሰው ልጅ ብቻውን እንዲኖር አልተፈጠረም:: ለዚህ ነው በሌሎች መፈለግንና መወደድን የምንፈልገው። ታዲያ ይህንን ስሜት ስናገኘው አእምሯችንና ሰውነታችን ይነቃቃል።ደስተኛ ይሆናል:: ጠዋት መጀመሪያ ላይ ለዛ የኔ ለምንለው ሰው ጊዜ መስጠት፣ ፍቅር መለገስ አብሮ ማሳለፍ እንዲሁም የምንወዳቸውን ሰዎች ማቀፍ በራሱ በሰውነታችን ውስጥ ያለውን የሚያነቃቃ ኬሚካል መጠኑ ይጨምራል:: ያለንን እምነትና ግንኙነትንም ያጠናክራል::

### 9ኛ. አልጋ ማንጠፍ

አልጋ ማንጠፍ በቀላሉ የማይታይ ቀናችን ላይ ትልቅ ተፅእኖ የሚፈጥር ዲስፕሊን ነው። የቀኑ ስኬትህን አንድ ብለህ የምትጀምርበት መነቃቂያህ ነው:: አልጋህን ራስህ ስታነጥፍና ሌላ ሰው ሲያነጥፍልህ የሚሰማህ ስሜት የተለያየ ነው:: በአንተ ምክንያት አንድ የተዝረከረከ ነገር መስተካከሉን ስታይ የስኬታማነት ስሜት ይሰማሃል። ይሄ ስሜት በቀን ውስጥ ልትሰራቸው ላሰብካቸው ሌሎች ተግባሮች በደምብ አድርጎ የሚገፋህ መንደርደሪያ ይሆንሃል::

### 10ኛ. ማንበብ

ጠዋት ባለን ንቃተ ህሊና ብዙ ነገሮችን ወደአእምሯችን የማስገባት አቅም አለን:: በዚህ ሰአት ቢያንስ አንድ ለስራችንና ለህይወታችን ወይ ደግሞ ለደስታችን፣ ለጤናችንና ለመንፈሳዊ ህይወታችን ጠቃሚ የሆነ አንድ ነገር ብናውቅ ከጊዜ በኋላ ያለን አስተሳሰብና የእውቀት ደረጃ እየተለወጠና እያደገ ይሄዳል:: ጠዋት ተነስተህ የምታነበው ነገር ቶሎ ይገባሃል:: በቋሚነት ሁሌም ካደረከው ደግሞ ይህ ፀባይ ካስተሳሰብህ ጀምሮ እውቀትህንና ገቢህን እስከመጨረሻው ይቀይረዋል::

ከላይ የተዘረዘሩት አስሩ ፀባዮች ፍላጎቱ እስካለን ድረስ በቀላሉ ልንተገብራቸው የምንችላቸው ናቸው:: ምን አልባት ‹‹ይህን ሁሉ ለማድረግ እንዴት ጊዜ ሊበቃን ይችላል›› ትሉ ይሆናል:: ሁለት ሦስቱን ፀባዮች በየቀኑ መርጠው ለጥቂት ደቂቃዎች በመከወን ጀምሩ። ተአምራዊ ለውጥ ያያሉ:: ሰላም!!

# የኢትዮጵያን ማርና ሰም አቀነባብሮ በውጭ ሀገራት መደርደሪያ ላይ ያስቀመጠው ባለሀብት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የግብርና ምርቶችን በጥሬያቸው ወደ ውጭ ገበያ ከመላክ ይልቅ እሴት ጨምሮ መላክ የተሻለ ኢኮኖሚን መገንባት እንደሚያስችል ይታመናል፡፡ መንግሥት በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ አካባቢዎች የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮችን የሚገነባውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ እሴት ሳይጨመርባቸው ወደ ውጭ ገበያ የሚላኩ እንደ ቡና፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ማርና ሌሎችም የግብርና ምርቶች አሁን ላይ እሴት ተጨምሮባቸው ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ መቅረብ ጀምረዋል፡፡ በዚህም ሀገር ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ታገኛለች፤ ተጨማሪ የስራ እድልም ይፈጠራል፡፡

ኢትዮጵያ የተገነቡ የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር፣ የአርሶ አደሩ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥና የሥራ ዕድል እንዲፈጠር በማድረግ አይነተኛ ሚና እየተጫወቱ ሲሆን፤ በተለይም ከተለያዩ የዓለም አገራት የተወጣጡ ኢንቨስተሮች ወደ ሀገሪቱ ገብተው መሥራት የሚችሉበትን ሰፊ ዕድልም እየፈጠሩ ይገኛሉ፤ ከውጭ ኢንቨስተሮች በተጨማሪም የአገር ውስጥ አምራቾች በተለያዩ ዘርፎች መሰማራት እንዲችሉ በር ከፍቷል፡፡

በአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው እሴት የተጨመረባቸውን የግብርና ምርቶች በማምረት ሥራ ላይ ከተሰማሩ የአገር ውስጥ አምራቾች መካከልም በቡልቡላ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የሚገኘው "ያናቢ ሸካ ኖርዲክ ማር" አንዱ ነው፡፡

‹‹ያናቢ ሸካ ኖርዲክ ማር ምርቱን ለባለንብረቱ የሰጠና ማር ያናቢው ነው›› በማለት ስለ መጠሪያ ስሙ ያብራራልን የኩባንያው መስራችና ባለቤት አቶ ቢንያም ቡልቻ ነው፡፡ አቶ ቢንያም፤ በሺዎች ከሚቆጠሩ አርሶ አደሮች ምርቱን ሰብስቦ የተጣራና ደረጃውን የጠበቀ ምርት ለውጭ ገበያ እያቀረበ እንደሚገኝ ይናገራል፡፡ ያናቢ ባህላዊ የንብ ማነብ አሰራርን አዋጭ ወደሆነው ዘመናዊ የንብ እርባታ ለመቀየር እየተንቀሳቀሰ ያለ የንግድ ድርጅት መሆኑን ጠቅሶም፤ ድርጅቱ በአገር ውስጥ በዘመናዊ የማር ማዘጋጀት አሰራር የሚመረተውን ተጨማሪ የማርና የሰም አቅርቦት ዓለም አቀፍ የገበያ ፍላጎትን በሚያሟላ መልኩ እንደሚያቀርብ ይገልፃል፡፡

ኩባንያው የማርና የሰም ምርቶችን በማቀነባበር፣ በማሸግና ወደ ውጭ ገበያ በመላክ ቀዳሚ እንደሆነ ያነሳው አቶ ቢንያም፤ ወደ ዘርፉ ከመግባቱ አስቀድሞ በስደት መቆየቱንና በሌሎች የሥራ ዘርፎች ተሰማርቶ እንደነበር አጫውቶናል፡፡ አዲስ አበባ ከተማ መርካቶ ተወልዶ ያደገው አቶ ቢንያም፤ በስደት ከሀገር የወጣው ገና በጠዋቱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ባጠናቀቀ ማግስት እንደነበር ያስታውሳል፡፡ የስደት ቤቱም ኖርዌይ ነበረች፡፡ በዚያም ከመማር በተጨማሪ ዝቅተኛ ከተባለ ሥራ ጀምሮ የግል ሥራዎችንም ሠርቷል፡፡

ለአስራ አምስት ዓመታት በስደት ከቆየባት አገረ ኖርዌ በመመለስ ብትን ጨርቆች፣ መኪኖችና ሌሎች ቁሳቁስን ከውጭ ሀገር በማስመጣት ሥራ ላይ ተሰማርቶ ቆይቷል። በተሰማራበት የንግድ ስራ ዘርፍ የሚፈጠር የሥራ ዕድል እና በአገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ አነስተኛ መሆኑን በማመን ወደ ማር ሥራ መግባቱን አቶ ቢኒያም ይገልፃል። ይሁን እንጂ ወደ አገር ውስጥ ያስመጣቸው ከነበሩ ምርቶች መካከል ጨርቃ ጨርቆችን አሁንም ድረስ እያስገባ ይገኛል፡፡

የተለያዩ ምርቶችን ወደ አገር ውስጥ ከማስገባት ባለፈ የኢትዮጵያ የሆኑ ምርቶችን ወደ ውጭ አገር ለመላክ ያሰበው አቶ ቢንያም፤ ንግዱን ሰፋ አድርጎ ለመሥራት በኢትዮጵያ የተገነቡ የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ምርጫው አድርጓል፡፡ የኢትዮጵያ ማር በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲቀርብ ለማስቻልም በኦሮሚያ ክልል በሚገኘው ቡልቡላ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የማርና የሰም ምርትን በማቀነባበር ለውጭ ገበያ እያቀረበ ይገኛል፡፡

"ያናቢ ሸካ ኖርዲክ ማር" ወደ ሥራ በገባበት ወቅት በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተመርቆ ወደ ሥራ መግባቱን ያስታወሰው አቶ ቢንያም፤ ኩባንያው ብዙ ተስፋ የተጣለበት መሆኑንም ይገልጻል። የአገሪቱን ኢኮኖሚ በማሳደግና አገርን በማስተዋወቅ ረገድ አበርክቶው የጎላ እንደሆነ ይናገራል፡፡ ዘርፉ በርካታ አርሶ አደሮችን ማሳተፍ የሚችል መሆኑን ገልጾ፣ በሥራ ዕድል ፈጠራም በርካታ ዜጎችን ማሳተፍ እንደሚያስችል አመላክቷል፡፡



**አቶ ቢንያም ቡልቻ፣**

የተጣራ የኢትዮጵያ ማር ለምን በውጭ አገራት መደርደሪያ ላይ አይታይም በሚል መነሻ ወደ ሥራው የገባ መሆኑን ያነሳው አቶ ቢንያም፤ የኢትዮጵያ ማር ሳይጣራና ሳይዘጋጅ ከነሰፈፉ ለውጭ ገበያ ይቀርብ እንደነበርም ነው የሚገልጸው፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ማሩ ለብቻ ተጣርቶ እንዲሁም ሰፈፉ ለብቻው ተዘጋጅቶ ለውጭ ገበያ እየቀረበ መሆኑን ተናግሯል፡፡ በዚህም አገር የምታገኘው የውጭ ምንዛሪ በእጥፍ እየጨመረ እንደሚመጣ ነው ያመለከተው፡፡

‹‹የኢትዮጵያ ማር ተጣርቶ ደረጃውን በጠበቀ መንገድ በጥሩ ዋጋ መሸጥ እንዲችልና በውጭ አገራት መደርደሪያ ላይ እንዲቀመጥ ማድረግ የቻልንበት የመጀመሪያው ምክንያት ከልብ የመነጨ ፍላጎት ነው›› የሚለው አቶ ቢንያም፤ ያለው አቅም ምን ያህል እንደሆነ፣ በአገር ውስጥ እንዲሁም በውጭ ያለው ፍላጎት ምን እንደሚመስል የምርቱ ባለቤት ከሆነው አርሶ አደር ጋር በማጥናት በመለየት ወደ ስራ መግባቱን ይናገራል። ከዚህ መነሻ አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሶ በቁርጠኝነት ወደ ስራው መግባቱን ይገልፃል። ምንም ነገር ቢሆን ከልብ በመነጨ ፍላጎት ለመሥራት ከታቀደ መሥራት እንደሚቻልም ነው ያስገነዘበው።

በሥራ አጋጣሚ ወደ ውጭ አገር በሄደበት ወቅት የኢትዮጵያ ማር በትንሽ ገንዘብ በበርሜል ተደርጎ ሳይጣራ ለውጭ ገበያ ሲሸጥ የሚያውቀው አቶ ቢንያም፤ በተመሳሳይ ደግሞ ይህንኑ ማር ነጮቹ አጣርተው በውድ ዋጋ በመሸጥ ተጠቃሚ ሲሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይህም ዛሬ ላይ ማርን በማቀነባበር ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ ያነሳሳው ሌላ ምክንያት መሆኑን አጫውቶናል፡፡ ወደ ሥራው ከመግባቱ አስቀድሞ ምዕራባውያኑ ማርን እንዴት እንደሚያጣሩትና ምን የተለየ ነገር እንደሚጨምሩበት አጥንቷል፡፡ በጥናቱም ማሩን በሚገባ የሚያጣራ ማሽን የግድ መሆኑን በመረዳት ዘመናዊ ማሽን በመትከል እንደ ሌሎቹ ሁሉ የተጣራ ማር አዘጋጅቶ ወደ ውጭ ገበያ እያቀረበ ይገኛል፡፡

በአሁኑ ወቅት በአነስተኛ ዋጋ ለውጭ ገበያ የሚቀርበውን የማር ምርት በማስቀረት የተጣራ ማር በተሻለ ዋጋ ለተለያዩ የዓለም አገራት እያቀረበ ያለው አቶ ቢንያም፤ የገበያ መዳረሻዎቹም ጃፓንን ጨምሮ አውሮፓና አሜሪካ ድረስ እንደሚዘልቅ ይጠቁማል፡፡ ያናቢ ሸካ ኖርዲክ ማር በአጭር ጊዜ ውስጥ ገበያ ውስጥ ገብቶ ተወዳዳሪ መሆን ችሏል፡፡

በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ አካባቢዎች ማሩን ሰብስቦ ለውጭ ገበያ የሚቀርበውን ማርና ሰም በቡልቡላ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ እንደሚያዘጋጅ የጠቀሰው አቶ ቢንያም፤ ከሁሉም የአገሪቱ ክፍል የማር ምርቱን ያገኛል፡፡ ለአብነትም ጉጂ፣ ኖኖ፣ ኢሊባቦር፣ ማሻ፣ ሸካ፣ ቦንጋ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍልም እንዲሁም ሰቆጣ፣ አዊና በሌሎች ማር ካለባቸው አካባቢዎች ሁሉ በማሰባሰብ ተፈጥሯዊነቱን ጠብቆ ማጥራት እንዲሁም ውስጡ ያለውን ሰምና ባክቴሪያዎች ዘመናዊ ማሽኖችን በመጠቀም በመለየት ንጹህና በውጭው ዓለም የሚፈለገውን ማር እያመረተ እንደሆነ አስረድቷል፡፡

ምዕራባውያኑ የሚከተሉትን ደረጃ በማሟላት አስፈላጊ ማሽኖችን በመጠቀም ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የማር ምርት ለውጭ ገበያ እያቀረበ መሆኑን የገለጸው አቶ ቢንያም፤ ከማሩ በተጨማሪ ኢትዮጵያ ውስጥ በተለምዶ ሰፈፍ ተብሎ የሚወጣውን ተረፈ ምርት አዘጋጅተውና አቀነባብረው ለውጭ ገበያ እየላኩ እንደሆነ ይገልጻል፡፡

ሰሙም በስፋት እንደሚፈለግ ይናገራል፡፡ "ሰም በራሱ አንድ ዘርፍ ነው" የሚለው አቶ ቢንያም፤ ሰሙ ተጣርቶ ለውጭ ገበያ እንደሚቀርበ የተለያዩ የዓለም አገራትም ለበርካታ ግልጋሎት እያዋሉት እንደሆነ አጫውቶናል። ለአብነትም ለመድሃኒትነት፣ ለፊት ማስክ፣ ለቅባትና ለሌሎች ጉዳዮች ጭምር ነጮቹ እንደሚገለገሉበት አስታውቋል፡፡

ለአውሮፓ ሀገሮች፣ አሜሪካና ጃፓን ማርና ሰሙን በስፋት ተደራሽ እያደረገ እንደሆነ የጠቀሰው አቶ ቢንያም፤ ሌሎች አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን እያገኘ መሆኑንም ነው ያመላከተው፡፡ ከእነዚህም መካከል በአውሮፓ አዳዲስ አገራትና በመካከለኛው ምስራቅም ተፈላጊ እየሆነ ስለመምጣቱም ተናግሯል። ለዚህም የገበያ ማፈላለግ ሥራ በስፋት ሠርተዋል፡፡ እየሰፋ ለመጣው ገበያ በቂ ምርት ማቅረብ እንዲቻልም ከአርሶ አደሩ ጋር በቅርበት እየሰራ መሆኑን የገለጸው አቶ ቢንያም፤ በተለይም አርሶ አደሩ ዘመናዊ ቀፎ እንዲያገኝና በብዛት እንዲያመርት ከውጭ ድርጅቶች ጋር እየሠራ እንደሆነ ጠቅሟል፡፡

በሺዎች ከሚቆጠሩ አርሶ አደሮች ጋር እንደሚሰራ የገለጸው አቶ ቢንያም፤ ያናቢ ሸካ ኖርዲክ ማር የሚያገኘው በህብረት ሥራ ዩኒየኖች አማካኝነት እንደሆነ ይጠቅሳል፡፡ በየአካባቢው በሚገኙ የህብረት ሥራ ማህበር ዩኒየኖች አማካኝነት እያንዳንዱን አርሶ አደር በመደገፍና በመከታተል እንዲሁም ስልጠና በመስጠት ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር እየተደረገ መሆኑንም ይገልጻል።

አቶ ቢኒያም እንዳብራራው፤ ከእያንዳንዱ አርሶ አደር ማሩን መልቀም የማይቻል በመሆኑ በዩኒየኖች አማካኝነት ማሩ ይሰበሰባል፡፡ በአሁኑ ወቅት ያናቢ ሸካ ኖርዲክ ማር ዘጠኝ ከሚደርሱ ዩኒየኖች ጋር ስምምነት ፈጽሞ ማር እየገዛ ይገኛል፡፡ ከስምምነት ውጭም ከተለያዩ ዩኒየኖች ማር ይረከባል፡፡ በእያንዳንዱ ዩኒየን ውስጥም ከ500 እስከ 700 የሚደርሱ አባላት በመኖራቸው በአጠቃላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በሺዎች ከሚቆጠሩ አርሶ አደሮች ጋር እየሰራ ነው፡፡

ማር አምርተው የሚያቀርቡ በሺዎች የሚቆጠሩ አርሶ አደሮችን ጨምሮ በቡልቡላ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ 60 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር የቻለው አቶ ቢንያም፤ በድምሩ በሺዎች ለሚቆጠሩ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር እንደተቻለም ነው ያጫወተን፡፡

ኩባንያው ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ ማር የሚያመርተው አርሶ አደር ውጤታማ መሆን እንዲችል ዘመናዊ ቀፎና ስልጠና በመስጠት ከሚያደርገው ድጋፍና ክትትል በተጨማሪ ከውጭ ድርጅቶች ጋር በመሆን በተለያዩ አካባቢዎች ለሚገኙ ወጣቶች ዘመናዊ ቀፎዎችን ለመስጠት እንቅስቃሴ እያደረገ ነው፡፡ ሁለት ባህላዊ የንብ ቀፎ ላለው አንድ ወጣት ሁለት ዘመናዊ የንብ ቀፎ ጨምሮ በመስጠት የበለጠ ማምረት እንዲችል ያደረጋል፤ በዚህም ከ500 እስከ 1000 የሚደርሱ ወጣቶች ተጠቃሚ እንደሚሆኑ አጫውቶናል፡፡

በኢትዮጵያ መልከዓ ምድር አበቦችና ንቦቹን ጨምሮ ምቹ የሆነ አየር በመኖሩ ማር ላይ ብዙ ብንሠራ ውጤታማ መሆን እንችላለን የሚለው አቶ ቢንያም፤ በተፈጥሮ ከታደልነው ጸጋ በተጨማሪ ማርን ከመብላት ባለፈ እንዴት ማልማት እንደሚገባ ጠንቅቆ የሚያውቅ ሕዝብ ስለመኖሩም ተናግሯል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ማር መብላቱንም ማምረቱንም ለሚያውቀው ማህበረሰብ ዘመናዊ ቀፎዎችን በማቅረብ በብዛት ማምረት የሚቻልበትን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር አገሪቷ ከዘርፉ የበለጠ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችል ጠቁሟል፡፡

ኢትዮጵያ መቶ ሺ ቶን ማር የማምረት አቅም እንዳላት የጠቀሰው አቶ ቢንያም፤ ያናቢ ሸካ ኖርዲክ ማር በሰዓት 1ሺ250 ኪሎ ግራም የማምረት አቅም እንዳለው ነው የጠቀሰው፡፡ በቀጣይም ሥራውን በማስፋት በምስራቅ አፍሪካ የማርና ፍራፍሬ ምርቶችን በማቀነባበር፣ በማሸግና ከአገር ውስጥ ባለፈ ኤክስፖርት በማድረግ የቀዳሚነት ስፍራን ለመያዝ ማቀዱን ጠቁሟል፡፡

በቡልቡላ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ያለበት አካባቢ ተጨማሪ ምርት ለማምረት የሚያስችል ምቹ ስፍራ መሆኑንም አቶ ቢንያም ይናገራል፡፡ ሌሎች ምርቶችን ይዞ ወደ ገበያው እየመጣ እንደሆነም ነው አቶ ቢንያም የገለጸው፡፡ በዋናነት ማርና ሰም እያመረተ ለውጭ ገበያ የሚቀርበው ያናቢ ሸካ ኖርዲክ ማር፤ በአካባቢው በስፋት የሚመረተውን ፍራፍሬ በማቀነባበር ተጨማሪ ዘርፍ ላይም መግባቱን አቶ ቢንያም ይጠቁማል፡፡

እሱ እንዳለው፤ በአካባቢው በስፋት የሚገኙትን ፓፓያ፣ ስትሮበሪና ሌሎች ፍራፍሬዎች ከአርሶ አደሩ በመሰብሰብ እሴት በመጨመር አዘጋጅቶና አሽጎ ለገበያ የማቅረብ ሥራው ተጀምሯል፡፡ አሁን ላይ ያለው ዕቅድም ለአገር ውስጥ ገበያ ማቅረብ ሲሆን፣ በቀጣይ ሁለትና ሶስት ዓመታት ከአገር ውስጥ ባለፈ ለጎረቤት አገራት የማቅረብ አላማን አንግቦ እየሰራ መሆኑን አቶ ቢኒያም ይናገራል። ምርቱ በስፋት ልጆች የሚጠቀሙበት ሲሆን፤ በቀላሉ ዳቦ ላይ ተቀብቶ የሚበላ የተዘጋጀ ፍራፍሬ እንደሆነ በማስረዳት፤ በአገር ውስጥ ገበያ የሚገኙት ተመሳሳይ ምርቶች 90 በመቶ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ መሆናቸውን አቶ ቢንያም አመላክቷል፡፡

ከፍራፍሬው በተጨማሪም ዳቦ ላይ የሚቀባ ቸኮሌት እያዘጋጀ ለገበያ እያቀረበ እንደሆነም ይገልጻል፡፡ እነዚህን ምርቶች ከውጭ የሚመጡ ምርቶችን መተካት እንደሚችሉ ጠቅሶ፣ የሚሰጡት ጠቀሜታ ዘርፈ ብዙ እንደሆነ ነው የሚናገረው፡፡ በተለይም የውጭ ምንዛሪን በማስቀረት እንዲሁም የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድ የሚኖረው አበርክቶ ጉልህ መሆኑን ይገልጻል፡፡

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የኮርፖሬት አደረጃጀትን ለሀገር ውስጥ ተቋራጮች

**መላኩ ኤሮሴ**

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን እየፈተኑ ካሉ ችግሮች አንዱ የሀገር ውስጥ ተቋራጮች የመወዳደር አቅም ውስንነት ነው፡፡ የሀገር ውስጥ ተቋራጮች የአቅም ውስንነት ፕሮጀክቶች በታሰበላቸው ጊዜ እንዳይጠናቀቁ ከሚያደርጉ ተግዳሮቶች አንዱ ከመሆኑም ባሻገር፣ ሀገሪቱ አላስፈላጊ ወጪ ውስጥ እንድትገባም ምክንያት ሲሆን ይስተዋለል፡፡ ዘርፉን አሁን ካለበት ችግር ለማላቀቅና አቅም ያላቸው ኩባንያዎችን ለመፍጠር የኮርፖሬት ባህል መፍጠር አንዱ አማራጭ እንደሆነ ታምኖበት እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡

የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር በቀጣይ ሊያዘጋጀው ላቀደው አዲስ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ሰነድ ግብዓት ለማሰባሰብ ከዘርፉና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርቡ በመከረበት መድረክ ላይ እንደተገለጸው፤ ውጭ ሄዶ ተወዳድሮ መስራት የሚችል እና በሀገር ውስጥ ባሉ ችግሮች ሸብረክ ሳይል መቆየት የሚችል ኩባንያ ለማፍራት በመጀመሪያ በሀገር ውስጥ የኮርፖሬት ባህል/ ኮርፖሬት ካልቸር/ እንዲገነባ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በመድረኩ ላይ ጥናታዊ ጽሁፍ ያቀረቡት ኢንጂነር መሰረት ለመች እንደሚሉት፤ የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች የአቅም ውስንነት ያለባቸው በመሆናቸው አብዛኞቹን ሜጋ ፕሮጀክቶችን ግንባታ እያከናወኑ ያሉት የውጭ ሀገር ኩባንያዎች ናቸው፡፡ የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ራሳቸውን ተወዳዳሪና ብቁ አላደረጉም፡፡ በገንዘብና በሌሎች አቅሞችም ብቁ አይደሉም፡፡

የውጭ ኩባንያዎች አንዱ የአቅም ምንጭ ደግሞ በኮርፖሬት ደረጃ መወዳደራቸው ነው፡፡ የቻይና የኮንስትራክሽን ተቋራጮች በኢትዮጵያ ውስጥ ሜጋ ፕሮጀክቶችን እየገነቡ ያሉት በኮርፖሬት ደረጃ ተወዳድረው በማሸነፍ ነው፡፡ በተለይም እንደ ቻይና ኮሚዩኒኬሽንስ ኮንስትራክሽን ካምፓኒ (CCCC) ያሉ ኮርፖሬቶች ናቸው ፕሮጀክቶችን እየገነቡ ያሉት፡፡

‹‹ተቋራጮች ኮርፖሬት ሲሆኑ ብዙ ጥቅም ያገኛሉ። የፋይናንስ እና የቴክኒክ አቅማቸውን በአንድ ላይ በማድረግ ሜጋ ፕሮጀክቶችን ይይዛሉ፤ ስኬታማ በሆነ መንገድም ገንብተው ያስረክባሉ፤ ተወዳዳሪነታቸው ከፍ ይላል፤ ለተለያዩ ስራዎች የሚያስፈልገውን ነገርም በቀላሉ ያገኛሉ፡፡ ምክንያቱም ኮርፖሬት ሲሆኑ ለሜጋ ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን በቀላሉ ያሟላሉ›› ሲሉ ኢንጂነር መሰረት ያብራራሉ፡፡

ለዚህም ነው የሀገር ውስጥ ተቋራጮች ወደ ኮርፖሬት እንዲያድጉ ጥረት እየተደረገ ያለው ያሉት ኢንጂነር መሰረት፤ ‹‹የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ወደ ኮርፖሬት አድገው የግንባታ ድርጅቶችን መያዝ ቢችሉ፣ ሀገሪቱ በከፍተኛ ሁኔታ ተጠቃሚ እንደምትሆንም አብራርተዋል፡፡ መንግስት ለውጭ ኩባንያዎች የሚያወጣውን ወጪ ማዳን ይቻላል። በዚህም በሀገሪቱ ውስጥ ካለው የምንዛሬ እጥረት አንጻር በሀገሪቱ ላይ ያለውን ጫና ይቀንሳል›› በማለት ያስረዳሉ፡፡

እንደ ኢንጂነር መሰረት ማብራሪያ፤ ኩባንያ ዎች በኮርፖሬት መደራጀት ቢችሉ የውጭ ምንዛሬ ከማዳን አልፎ ለሀገሪቱ ተጨማሪ ምንዛሬም ያስገኛል። ኩባንያዎቹ በውጭ ሀገራት የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን ተወዳድረው በማሸነፍ ለሀገር የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኙ ይችላሉ፡፡ ለዚህም ነው ደረጃ አንድ እና ደረጃ ሁለት የሆኑ ኩባንያዎች በጥምረት እንዲደራጁ ጥረት እየተደረገ ያለው፡፡

አንድ የማድረጉ ስራ በፈቃድ ላይ የተመሰረተ እንደሚሆን ያብራሩት ኢንጂነር መሰረት፤ ለሀገር ካለው ፋይዳ አንጻር በኮርፖሬሽን ለሚደራጁት የተለያዩ ማበረታቻዎች እንደሚቀርቡም ተናግ ረዋል። ‹‹ለኮርፖሬቶቹ እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል የተለያዩ ድጋፎች ይሰጣል፡፡ የሁሉም ዘርፍ ተቋማት



የቤት ስራውን ወስደው እንዲሰሩ ይደረጋል›› ብለዋል፡፡

አብዛኞቹ ኩባንያዎች በኮርፖሬት ጉዳይ ደስተኛ መሆናቸውን ያብራሩት ኢንጂነር መሰረት፤ ከእያንዳንዱ ባለድርሻ አካል ጋር በመሆን ወደ ኮርፖሬት የማሳደግ ስራ እንደሚሰራም ነው ያመለከቱት፡፡ የኮንስትራክሽን ፖሊሲ ሲዘጋጅም ተቋራጮቹን ወደ ኮርፖሬት የማሳደግ ጉዳይ አንዱ የትኩረት አቅጣጫ እንደሚሆን አመልክተዋል፡፡

የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ወንድሙ ሴታ በበኩላቸው፤ ‹‹በዚች ሀገር ውስጥ የኮርፖሬት ባህል እንዲገነባ ማድረግ ያስፈልጋል። የኮርፖሬት ባህል ማለት አምስት ስድስት ኩባንያዎችን መጨፍለቅ አይደለም፤ ብቻውንም ቢሆን በሚገባ የተዋቀረ የኮርፖሬት የአሰራር ሥርዓት ያለው ተቋራጭ እንዲኖር ማድረግ ከተቻለ ጠንካራ ተቋም ማግኘት ተችሏል ማለት ነው ሲሉ ያብራራሉ። የተቋራጮችን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ እኛ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት እንቀርጻለን፤ በዚህም መስፈርቶችን በማዘጋጀት ኩባንያዎችን በማብቃት ትልልቅ ኩባንያዎችን እንፈጥራለን›› ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የኮንስትራክሽን ኢንዱ ስትሪው የተለየ አሰራር ይፈልጋል፤ የቻይና ኩባንያ እዚህ አገር ለመስራት ድንገት አልመጣም፤ የአገሪቱ መንግስት ኩባንያው ወጥቶ ሰርቶ ገንዘብ እንዲያመጣ ይደግፈዋል። ‹‹ከዚህ አንጻር የኛ አገር መንግስት ተቋራጮች ወጥተው እንዲሰሩ ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል። በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ላይ የሚመጣው ተወዳዳሪነት የሚባክነውን ሀብት ከመቀነስ ባሻገር የሚመደበውን ሀብት በውጤታማ መልኩ ስራ ላይ ማዋል የሚቻልበትን ከባቢ ይፈጥራል።››ብለዋል፡፡ ይህን ተወዳዳሪነት ከፈጠርን በኋላ ይህን ለውጥ የሚሸከም አዲስ ስትራቴጂ መንደፍ ያስፈልጋል›› ሲሉም ሚኒስትር ዴኤታው ገልጸዋል፡፡

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አብቦ የነበረባቸውን የቀደሙትን ዓመታትም አስታውሰው፣ ‹‹በዚያን ወቅት ላይ ያንን እድገት የሚጠብቅ ተግባር አልሰራንም፤ ቁጥር አበዛን፤ ተወዳዳሪነት ላይ ግን እዚህ ግባ የሚባል ተቋራጭ ሳናገኝ ቀረን ሲሉ ገልጸዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው እንዳሉትም፤ ከዚህ አንጻር አዲስ ለውጥ መፍጠር ይገባል፤ ያለውን የገበያ እድል ማስፋት፤ አዳዲስ የገበያ እድሎችን መፍጠር ያስፈልጋል። የዛሬ ሰባት ዓመት መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ እንደርሳለን ስንል መንገዱ ኮንስትራክሽን ነው፡፡ ኮንስትራክሽን የሚፈጥረው እሴት፣ ለውጥና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ነው መካከለኛ ገቢ ላይ የሚያደርሰው።

ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ዘጋን ማለት መንገዱን ዘጋን ማለት ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ በየዓመቱ በኮንስትራክሽን ዘርፉ ያለው ኢንቨስትመንት እየጨመረ ነው፤ ከመጨመርም አልፎ ጥሩ ጥሩ ግንባታዎችም አሉ ያሉት ኢንጂነር ወንድሙ፣ ‹‹ሁሉም ሊባሉ በሚችል መልኩ ሜጋ ፕሮጀክቶች ናቸው። የስራ ተቋራጮቻችንን የባለሙያዎቻችንን የአማካሪዎቻችንን ተወዳዳሪነት ካላሳደግን በስተቀር እነዚህ ሜጋ ፕሮጀክቶች መቶ በመቶ ለውጭ ተቋራጮች ሊሰጡ ይችላሉ›› ሲሉ አስገንዝበዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን ሁሉም አገሮች ያደጉበት መንገድ በውጭ ኩባንያዎች ተሳትፎ መሆኑን ነው። የውጭ ኩባንያዎች ተሳትፎ ግን የአጭር ጊዜ መሆን አለበት። በእነሱ ተሳትፎ ፕሮጀክቶች እየተሰሩ ቴክኖሎጂ እየተሸጋገረ እውቀት እየተቀሰመ ከዚያም የአገር ውስጥ ተቋራጭነት አቅም እያደገ መምጣት አለበት። የአገር ውስጥ ተቋራጮች ከውጭዎቹ ጋር ያላቸው ትስስር እንዲጠናከር ማድረግ ላይ መሰራት ይኖርበታል። እስከ አሁን ያንን ጠንክረን አልሰራንበትም ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፣ በዚህ የተነሳም በሚባለው ደረጃ ቱሩፋቱን ማግኘት አልተቻለም ይላሉ፡፡

የኮንስትራክሽን ማኔጅመነት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ታምራት ሙሉ በቅርቡ በአዳማ በተካሄደ የዘርፉ መድረክ ላይ ለሀገር ውስጥ ተቋራጮች ግሎባል ተወዳዳሪነት መሰረት የሚጥሉ ስራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የ30 አመት ሮድ ማፕ አለው፤ የአስር አመት እቅድ ወጥቶም እየተሰራም ይገኛል፡፡ በአስር አመቱ እቅድም ካለው የዘርፉ ገበያ የሀገር ውስጥ ተቋራጮች 75 በመቶ እንዲሁም የምስራቅ አፍሪካን/ ሰብ ሪጅን/ 25 በመቶ ድርሻ እንዲይዙ ታቅዶ፤ ይህ ይቻላል ወይ ሲሉ ዋና ዳይሬክተሩ ጠይቀው አዎን ይቻላል፤ የቻይና ተሞክሮ ይህን ያመለክታል ሲሉ ያብራራሉ፡፡

የሀገር ውስጥ ተቋራጮች እንዴት ይበረታቱ፣ እንዴት ተወዳዳሪ እናድርጋቸው ሲሉም ጠይቀው፣ ዓለም የሚጠቀምባቸውን ቴክኖሎጂዎች እንዲ ጠቀሙ ማድረግ ላይ እየተሰራ መሆኑንም ነው ዋና ዳይሬክተሩ ያመለከቱት፡፡ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች እየተሰጡ፣ የሀገር ውስጥ ኩባንያዎችን የሚያበረታታ አዲስ የግዥ መመሪያ እየተዘጋጀ፣ ተኪ ምርቶችን የሚያመርቱን ከማበረታታት አኳያም እየተሰራ መሆኑን አብራርተዋል፡፡ በሀገሪቱ ቀደም ሲል ተቋራጭ ሌባ ተደርጎ ይቆጠር ነበር፤ አሁን የልማት አጋር ተደርጓል፤ ተቋራጭም አማካሪም የሀገር ሀብት ናቸው፡፡ ይህ ሳይሆን በመቅረቱ የሀገር ሀብቶችን አጥተናል፤ ያን መመለስ አለብን ያሉት አቶ ታምራት፣ የሀገር ውስጥ ተቋራጮች በተዳከሙ ቁጥር በውጭዎቹ ስር እንወድቃለን ሲሉ አስገንዝበዋል፡፡

ተቋራጮች በቀጣይ በቆይታቸው ሳይሆን በብቃታቸው ልክ ብቻ የሚያድጉበት ሁኔታ እንዲኖርም ይሰራል ብለዋል፡፡ የአቅም ግንባታ በመንግስት በኩል እንደሚደረግ ጠቅሰው፣ መንግስት በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ተደጋጋሚ ስልጠናዎችን እንደሚሰጠም ጠቅሰው፣ ተቋራጮችም በተደራጀ አግባብ ሲቀርቡ እንደሚደገፉም አስታውቀዋል፡፡

የባዛልት ኮንስትራክሽን ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ብሩክ ነጋሽ እንደሚሉት፤ የተቋራጮች አቅም ማነስ ተቋራጮችንም ሆነ ሀገሪቱን ይጎዳል፡፡ የተቋራጮች ፍላጎትን መሰረት በማድረግ ተቀራራቢ አቅም ያላቸው ኩባንያዎች በአንድ ላይ በመሆን ወደ ኮርፖሬት እንዲያድጉ ቢደረግ የዘርፉን ችግር ለመቅረፍ እገዛ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ይሁን እንጂ የኮንስትራክሽን ተቋራጮችን ወደ ኮርፖሬት የማሳደጉ አካሄድ ሌሎች ዘርፎችን ወደ ኮርፖሬት ለማሳደግ ከሚደረገው አካሄድ እና አሰራር የተለየ ሊሆን እንደሚገባም ይጠቁማሉ። ለአብነት ያህል እንደ ባንኮች እና ኢንሹራንሶች ያሉ የፋይናንስ ዘርፎች ተቋማትን ወደ ኮርፖሬት ለማሳደግ ከሚካሄደው የተለየ አካሄድ መከተል ያስፈልጋል፡፡ እንደ ባንኮች እና ኢንሹራንሶች ያሉትን ኩባንያዎች አይነት ኮርፖሬሽንን በመመስረቻ መንገድ ተቋራጮችን ኮርፖሬት ለማድረግ የሚደረገው ጥረት የሚፈለገውን ውጤት ላያፈራ ይችላል ይላሉ፡፡

የኮንስትራክሽን ዘርፍ ከፍተኛ ሀብት ያለበት ነው ይላሉ፡፡ አንዳንዶቹ የኮንስትራክሽን ተቋራጮች ከፍተኛ ሀብት ሲኖራቸው ሌሎቹ ደግሞ ብዙም ሀብት ላይኖራቸው ይችላል፡፡ ብዙ ሀብት ያለው እና ሀብት የሌለው አንድ ላይ ኮርፖሬት ይሁን ሲባል ሀብት ያለው ሊጎዳ ይችላል ሲሉም ያብራራሉ፡፡

እንደ አቶ ብሩክ ማብራሪያ፤ ተቋራጮችን ወደ ኮርፖሬት በማሳደግ ሂደት ውስጥ የኮንስትራክሽን ስራ ከሌሎች ስራዎች ጋር ያለው ልዩነት ከግምት ሊገባ ይገባዋል፡፡ የኮንስትራክሽን ስራ ብዙ ጥረት ይጠይቃል፡፡ ቀንና ሌሊት የሚሰራበት ነው፡፡ ትልቅ መሰጠትን ይጠይቃል፡፡ ሰዎች ተሰጥተው ካልሰሩ በኮንስትራክሽን ዘርፍ ስኬታማ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡

እንደ ፋይናንስ ዘርፍ ስርዓት በመዘርጋት ብቻ የሚመራ አይደለም፡፡ ከስርዓት ባሻገር ብዙ ድካምን ይጠይቃል፡፡ አቀበት ቁልቁለት መውረድና መውጣት፤ አቧራና ጭቃ ውስጥ መሄድን ይፈልጋል። አንዳንዱ ሳይሰራ የቅንጦት ሕይወት የሚኖር የኮንስትራክሽን ኩባንያ ባለቤት አለ፡፡ ሌላኛው ደግሞ ወርዶ ራሱ የሚሰራ የኩባንያ ባለቤት አለ፡፡ ከዛ አንጻር በመሃል መጓተት ሊኖር ይችላል፡፡

አቶ ብሩክ ወደ ኮርፖሬት ሲመጣ የሰዎች መሰጠት ሊቀንስ ይችላል የሚል ስጋት አላቸው። መሰጠት ከቀነሰ ደግሞ ዘርፉን ወደፊት ሊወስድ ይችላል ተብሎ የታሰበው ኮርፖሬት ዘርፉን ጭራሽ ወደኋላ ሊጎትት ይችላል ሲሉ ያመለክታሉ፡፡

ወደ ኮርፖሬት ማደግ በራሱ ስኬታማ ሊያደርግ እንደማይችል የሚያነሱት አቶ ብሩክ፤ ከዚህ ቀደም በክልል እና በፌዴራል ደረጃ ኮርፖሬት የሆኑት ውጤታማ ናቸው ወይ የሚለውን ማየትም ያስፈልጋል ነው የሚሉት፡፡ በፌዴራል እና በክልሎች የተቋቋሙት የኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽኖች ውጤታማ ሊሆኑ አልቻሉም የሚል መከራከሪያም ያቀርባሉ፡፡

የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች ችግር ግን የአቅም ማነስ ብቻ እንዳልሆነም አቶ ብሩክ የጠቆሙት። ገበያ አለመኖር፣ የግብዓት አቅርቦት አለመኖር፣ ኤልሲ ማግኘት ከባድ ነው ሲሉ ያብራራሉ፡፡ ከውጭ የሚመጡ ግብዓቶችን ማግኘት ከባድ መሆኑንም ጠቅሰው፣ ከውጭ ሀገራት የሚገቡ የግብዓት ችግሮች መኖራቸውም ኮርፖሬት የሆኑትንም እየፈተኑ መሆናቸውን ይጠቁማሉ፡፡ ከላይ የተጠቀሱ ችግሮች ሳይፈቱ ኮርፖሬቶችን በመፍጠር ብቻ የዘርፉ ችግር ሊፈታ አይችልም ይላሉ፡፡

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ኮርፖሬት የማድረግ ስራ ከመሰራቱ በፊት የስራ ባህልንም መቀየር ያስፈልጋል፡፡ በኢትዮጵያ አብሮ ተደጋግፎ የመስራት ልምድ አነስተኛ ነው፡፡ ተደጋግፎ ከመስራት ይልቅ አንዱ ሌላውን ጠልፎ ለመጣል ጥረት ሲያደርግ ነው የሚታየው፡፡ ይህንን የስራ ባህል በመሰረቱ ለመቀየር የሚያስችሉ ስራዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሱዳናውያን በመነጋገር ከችግሮቻቸው በላይ መሆናቸውን ማሳየት ይጠበቅባቸዋል

አፍሪካውያን ችግሮቻቸውን በራሳቸው የመፍታት አቅሙ ብቻ ሳይሆን፤ ለዚህ የሚሆን ሰፊ ማህበራዊ፣ ባህላዊና መንፈሳዊ እሴቶች ያሏቸው ሕዝቦች ናቸው። ይሁን እንጂ ይህንን አቅማቸውን ተጠቅመው ከግጭት ነፃ የሆነች አህጉር መመስረት ያልቻሉት በአብዛኛው የውጭ ጣልቃ ገብነቶች ፈተና ስለሆኑባቸው እንደሆነም ይታመናል።

ለዚህ ደግሞ በነጻነት ዋዜማቸው አፍሪካውያን ስለነገዎቻቸው ተስፋ አድርገው ያለሟቸውንና ከነጻነት ማግስት ጀምሮ እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ ለመኖር የተገደዱባቸውን አመታት መመልከት ተገቢ ነው። እነዚህ አመታት ለአህጉሪቱ ሕዝቦች የቱን ያህል የምጥ አመታት እንደሆኑ ነጋሪ የሚያስፈልጋቸው አይደሉም።

ከስድስት አስርት ዓመታት በሚበልጡ በነዚህ ጊዜያት የአህጉሪቱ ሕዝቦች በተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ምስቅልቅሎች ውስጥ ለማለፍ ተገደዋል። በዚህም ሰላምና መረጋጋት አጥተው፤ ለአስከፊ እልቂቶች፣ ስደትና ስነልቦናዊ ቀውሶች ተዳርገዋል።

የቀደሙት አህጉሪቱ የነጻነት አባቶች ለአህጉሪቱ ሕዝቦች ተስፋ ያደረጓቸው ነገዎች፤ እንዲሁም ነገዎቹ የተሸከሟቸው ህልሞቻቸው፣ የቅዥት ያህል ተለውጠው ህልመኞቹን ሳይቀር በልተው አህጉሪቱ የግጭትና የሁከት፤ የተስፋ መቁረጥና የቁዘማ ምድር እንድትሆን ተደርጋለች።

እነሱ ብቻ ሳይሆኑ ከነሱም በኋላ የተነሱ ስለ አህጉሪቱ ሕዝቦች ነገዎች ብሩህ ህልም የነበራቸው አፍሪካውያን ተስፈኞች በአንድም ይሁን በሌላ ከተስፋቸው ተፋተው ባልተገባ መልኩ ለሞት እና ለስደት ተዳርገዋል። ፍጻሜያቸውም ለሌሎች እንደ ማስፈራሪያ ማስጠንቀቂያ ተደርጎ ተገምዶም ታይቷል።

በዚህ የአፍሪካውያን የስድስት አስርት አመታት የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ምስቅልቅሎሽ፤ ከዚህ በመነጩ የግጭት፣ የእልቂት፣ የስደት፣ የረሀብና የእርዛት ትርክቶች በስተጀርባ የውጭ ጣልቃ ገብነቶች ሰፊ ወስን ስፍራ እንደሚይዙ፤ የአፍሪካ ችግሮችም አልፋና ኦሜጋ እንደሆኑ ተጨባጭ እውነታዎች የሚያረጋግጡት ጉዳይ ነው።

ይሄም የነፃነት ትግሉና ትግሉ የወለደው አህጉራዊ መነቃቃት በቅኝ ገዥዎች መንደር የፈጠረው መደናገጥ፤ አፍሪካውያን የነጻነት አባቶች የትናንት ህልሞች እውን እንዳይሆኑ ፈተና የመሆኑን ያህል፤ ያው ስጋት እስከዛሬ ድረስ አፍሪካውያን ብሩህ ነገዎቻቸውን ሰርተው እንዳይኖሯቸው ተግዳሮት እንደሆነ ነው።

ኢትዮጵያም እንደ አገር የቅኝ ግዛት ሰለባ ባትሆንም፤ እንደ የትኛውም አፍሪካዊ አገር የዚሁ የውጭ ጣልቃ ገብነት ሰለባ ስለመሆኗ ባለፉት ስድስት አስር ዓመታት የመጣችባቸው ውጣ ውረዶች፤ ሞት እና ስደት፤ ረሀብና እርዛት የበዙባቸው ጉዞዎቿ ተጨባጭ መገለጫዎች ናቸው።

በቅርቡ እንኳን በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የተካሄደው ጦርነት እና ጦርነቱ በሁለንተናዊ መልኩ በአገሪቱ ላይ እያስከተለ ያለው ተጽእኖ ስንመለከት፤ አፍሪካውያን ብሩህ ነገዎቻቸውን ለመስራት ቁርጠኛ ሆነው መንቀሳቀስ ሲጀምሩ የቱን ያህል የውጭ ጣልቃ ገብነቶች ዋነኛ ፈተና እንደሚሆኑባቸው ያመላከተ ነው።

ከዚህ ዘመናት ካስቆጠረ ተጨባጭ ችግር በመነሳት ኢትዮጵያ "ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ" በሚል የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት የሄደችበት መንገድ፤ የውጭ ጣልቃ ገብነትን በመቀነስ ችግሩን በውይይትና በሰላም ስምምነት ለመፍታት አስችሏታል፡፡

ይህ ተጨባጭ ተሞክሮም አፍሪካውያን ፖለቲከኞች አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነቶችን መከላከል ከቻሉ ችግሮቻቸውን መፍታት የሚያስችል በቂ አቅም እንዳላቸው ያሳየ፤ ከዚህም በላይ የትኛውንም አይነት የውጭ ጣልቃ ገብነት የሕዝቦቻቸውን ብሩህ ነገዎች ከማጨለም ባለፈ ምን አይነት ፋይዳ እንደሌላቸው ያመላከተ ነው።

በግጭት ውስጥ ያሉ የሱዳን ኃይሎችም ይህንን ከስድስት አስርት ዓመታት በላይ አፍሪካውያንን ዋጋ እያስከፈለ ያለ ችግር በአግባቡ በመረዳት፤ በውጭ ጣልቃ ገብነቶች የሱዳንን ሕዝብ ከቀደመው ዘመን የከፋ ዋጋ እንዳይከፍል በኃላፊነት መንፈስ ሊንቀሳቀሱ ይገባል።

በተለይም ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ በሚለው መርህ ኢጋድ የአካባቢው አገራትን በማስተባበር በሱዳን ላለው ችግር ዘላቂ መፍትሄ ለማፈላለግ በአዲስ አበባ ሊያካሄድ ቀነ ቀጠሮ ለያዘለት የሰላም ውይይት፣ ተደራዳሪ ኃይሎች እራሳቸውን በተገቢው መንገድ በማዘጋጀት በእርግጥም ሱዳናውያን እንደ አንድ የአህጉሪቱ ሕዝቦች የራሳቸውን ችግር በራሳቸው መፍታት እንደሚችሉ በተጨባጭ ማሳየት ይጠበቅባቸዋል።

**አዲስ ዘመን**
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## አገርን በምክክር የመታደግ ሂደት

ጌቱሰማኒ ዘ-ማርያም

አገራችን ባለፉት ዓመታት ጥሩ ሁኔታ ላይ አልነበረችም፡፡ አዛም እዚህም ሁከትና ብጥብጥ እየተከሰተ ሕዝቡ ቁም ስቅሉን ሲያይ ኖሯል፡፡ በተለይ ከወደ ሰሜኑ የአገራችን ክፍል ከተቀሰቀሰው ጦርነት ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የአገራችን ክልሎች አውዳሚ ግጭቶች ተከስተዋል፡፡ ሁከትና ብጥብጦችም እየተባባሱ መጥተው፤ሰላማዊው ሕዝብም በዚሁ ምክንያት አላስፈላጊ መስዕዋትነት ሲከፍል ቆይቷል፡፡

ሰላም መደፍረሱ ሕገ ወጥነት እንዲበረታታ መንገድ ከፍቷል፡፡ ሙስና እንዲነግስና የቆዩ የአብሮ መኖር መስተጋብራችን እየተሸረሸረ እንዲመጣም አድርጓል፡፡ እንዲሁም ራሳችን መግዛት የሚያስችሉንን የኃይማኖቶቻችን እሴቶች ዋጋ እንዲያጡ አድርጓል። የትራንስፖርት እንቅስቃሴን አስተጓጉሎ የከፋና ጥግ የደረሰ የሕብረተሰብ ምሬት የሚሰማበት የኑሮ ውድነትና የዋጋ ንረትን ፈጥሯል፡፡ እነዚህ ሁሉ ችግሮቻችን በውጭ ግንኙነታችን ላይም መልካም ያልሆነ የግንኙነት ጥላ አጥልተው ቆይተዋል፡፡ የውጭ ጣልቃ ገብነትን በመጋበዝ የራሳችንን ችግር ራሳችን እንዳንፈታ ከባድ ጫና ፈጥረውብንም ከርመዋል፡፡ በንግድ ግንኙነትና በአንዳንድ የኢኮኖሚ ሁኔታዎቻችን ላይም ማዕቀብ ከማስጣል አልፈው ኃያላን ነን ከሚሉ በተለይም ከምዕራባዊያኑ አገራት ሉዓላዊነታችንን በብርቱ የሚፈታተን ማስፈራሪያና ዛቻ እንዲሰነዘርብን አድርገዋል፡፡ በተለይ ከአሜሪካ በግልጽ ብሔርንተ ጉዳይ እኔ ነኝ የሚያገባኝ፤ እኔን ስሙኝ የሚል ዓይነት ግልጽ ጣልቃ ገብነትን በትዕግስት አስተናግደናል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሰላም በመውረዱ ከሕ.ወ.ሓ.ት ጋር ስምምነት ላይ በመድረስ እነዚህን ሁሉ ችግሮቻችንን መፍታት የሚያስችለን መደላደል ፈጥረናል፡፡ የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከመደላደሎቹ አንዱ እንዲሆንም አድርገናል፡፡ ኮሚሽኑ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ከላይ የተዘረዘሩትን ዋና ዋና ችግሮች ጨምሮ ሌሎች እስከ ታች የወረዱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንዲሁም ስነ ልቦናዊ ችግሮቻችንን ለመፍታት የሚያስችል እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል፡፡ የዚህ ይህንን ዓይነቱን የእንቅስቃሴ ሂደቱን ለማሳለጥ በተቋቋመው በአማካሪ ኮሚቴ አዝዞ እያከናወነ የሚገኘው አገራዊ የምክክር ኮሚሽን ዋና ዓላማው ከላይ የተዘረዘሩትንና ሌሎቹን ችግሮቻችንን በመፍታት አገራዊ መግባባት መፍጠር ነው፡፡ በተጨማሪም አገራዊ መግባባት ሲፈጠር አገርና ሕዝብ ሰላም የመሆኑ ጉዳይ እሙን እንደመሆኑ አገርን ሰላም ለማድረግ፤ በፊት የነበሩ የተወሳሰቡ ሂደቶችን፤የተሳሳቱ ታሪኮችን የሚያጠራበትም ሂደት አለው፡፡

በነገራችን ላይ በዚህ ሂደት ተሳታፊዎችን የመለየቱ ተግባር የሚጀመረው በጋምቤላ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና ሀረሪ ክልሎች እንዲሁም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የአጀንዳ ማሰባሰብ እና ተሳታፊዎችን የመለየት ስራ የሚያከናውነው፤ በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በሚከፍታቸው ቅርንጫፎች መሆኑ ደግሞ ሥራውን የበለጠ የተቀና እንደሚያደርገው ይታሰባል። ከዩኒቨርሲቲ በተጨማሪ ኮሚሽን ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤቶችን የሚከፍትበት ሁኔታ መኖሩ ሂደቱን የበለጠ ያፋጥነዋል፡፡ በሲቪክ ማህበራትና በሌሎች ተቋማት የአጀንዳ ማሰባሰብ እና ተሳታፊዎችን የመለየት ስራ መሥራት ማስቡም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ ይሄን ተንተርሰው ነው በአራቱ ክልሎች እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ባሉ ሁሉም ወረዳዎች ውስጥ የሚገኙ "የተለዩ የህብረተሰብ ክፍሎች" "ይወክሉኛል" የሚሏቸውን ተሳታፊዎች ይመርጣሉ፡፡ እንደ አገር በጥቅሉ ከ700 ሺህ በላይ ሕዝብ ቀጥተኛ ተሳታፊ ይሆናል ተብሎም ታስቧል፡፡ ተወካይ ያስመርጣሉ ተብለው የተለዩ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችም የተካተቱ ሲሆን ሴቶችና ወጣቶች ዋናዎቹ የአስመራጭ ወገን ተዋናዮች ናቸው፡፡ በተጨማሪም የመንግስት ሰራተኞች፣ መምህራን እና የማህበረሰብ መሪዎች እንደሚገኙበት ከኮሚቴው በወጣ መግለጫ ማድመጣችን ይታወሳል፡፡ እንደኮሚሽኑ መግለጫ፣ የተገለሉ ህብረተሰብ ክፍሎችን ማሳተፉ የኮሚሽኑን ፍትሃዊነትና የሚያመላክት ከመሆኑም በላይ በአገራችው ጉዳይ ተገለለው በቆዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ የተለየ በጎ ስሜት ይፈጥራል ተብሎ ይታሰባል፡፡ እንደዚሁም አድሮች እና የንግድ ማህበረሰብም በአስመራጭነት የተካተቱበት ሁኔታ አለ። ከነዚህም ባሻገር በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ተፈናቃዮችም፤ "በባለድርሻ አካልነት" እንደሚቆጠሩ ሲነገር ተደምጧል፡፡ በአጠቃላይ ከተሳትፎ አንፃር ሁሉንም ዓይነት የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚያሳትፍ መሆኑ ነው እየተነገረለት የሚገኘው፡፡

እነዚህ አስመራጭ የማህበረሰብ ክፍሎች እያንዳንዳቸው በየወረዳቸው 50 ተወካዮችን እንደሚመርጡም ተጠቅሷል፡፡ የመረጧቸውንም ለለያ ወደ የዞን ማዕከላት እንደሚልኩ ተመላክቷል። ወደ ዞን ከመጡት የእያንዳንዱ የማህበረሰብ ክፍል ተወካዮች ውስጥ ሁለት ሰዎች የሚመረጡበትም ሂደት አለ፡፡ እነዚህ ሁለት ሰዎች በክልል ደረጃ በሚካሄደው አጀንዳ የማሰባሰብ ስራ ይሳተፋሉ ተብሎ ይታሰባል። በክልል ደረጃ የሚሰበሰቡት ተወካዮች፤ በየወከሉት ህብረተሰብ ክፍል ተከፋፍለው "ኮከስ" ይፈጥራሉ፡፡ ኮከሶቹ በፊናቸው "የወከልነው የህብረተሰብ ክፍል ዋነኛ ጉዳዮች እነዚህ ናቸው" ሲሉም የለዩዋቸውን አጀንዳዎች ለኮሚሽኑ የሚያቀርቡበት የአሰራር ሂደት እንዳለ ተነግሯል፡፡

በእያንዳንዱ ወረዳ አንድ አባል ይሄንኑ ሂደት የሚታዘብበት ሁኔታ በኮሚሽኑ በኩል ተመቻችቷል፡፡ ሂደቱን ከሚታዘቡ ተባባሪ አካላት ውስጥ፤ የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ምክር ቤት፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት እና የመምህራን ማህበር ይጠቀሳሉ። የአካባቢው "የዓውድ ጎሳ መሪዎች"፡ ሀገር አቀፍ የእድሮች ማህበራት ጥምረት እና የኃይማኖት ተቋማት ጉባኤም ተካትተዋል፡፡ የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች እና የወረዳ አስተዳደር ተወካዮችም ሂደቱን በመታዘብ ይሳተፋሉ፡፡

ለኮሚሽኑ ከሚቀርቡት አጀንዳዎች ከላይ በመግቢያችን የዘረዘርናቸውና ባለፉት ጥቂት ዓመታት ተከታትለው ሲገጥሙን የነበሩ ችግሮች ጎልተው ይነሳሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ ጦርነቱም ሆነ በተለያዩ አካባቢዎች ሲከሰቱ የነበሩትና አሁንም ያልቆሙት ግጭቶች ትልቅ ቦታ የተሰጠው አጀንዳ ሆኖ ይቀርባል ተብሎ ይገመታል፡፡

ወንድማማችነት ይንገስልን፤ የአብሮነታችን መስተጋብር ወደነበረበት ስርዓት ይመለስልን፤ የተሸረሸረው የየዕምነቱና ኃይማኖቱ እሴቶቻችን ዋጋ ኖሯቸው ችግሮቻችንን ለመፍታት ይበቁ እንጂ የግጭትና ሁከት መነሻ እንዳይሆኑ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራበት የሚለውም ትኩረት ተሰጥቶት የሚነሳ አጀንዳ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ሕገ ወጥነት ይቁም፤ ሕግ ይከበርልን እና ሰላም ይስፈንልን የሚለውም ትልቅ ቦታ ተሰጥቶት የሚነሳ አጀንዳ እንደሚሆንም ይገመታል፡፡

የዋጋ ንረት አባዜ ይታይ፤ የኑሮ ውድነት ጫና ይቅለል ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚፈጠረው ችግር ሁሉ ሊፈታበት የሚችል መፍትሄ ይዘየድ የሚለውም ሕዝባዊ አጀንዳ ሆኖ የሚነሳበት ሰፊ ዕድል ይኖራል ተብሎ ይታመናል፡፡ ለቀጣይ ትውልድ በምን መልኩ ትተላለፍና የወደፊት ዕጣ ፈንታዋ ምን ይሁን የሚለው የአገረ ኢትዮጵያ ጉዳይ ከትክክለኛ የታሪክ ትርክት ጋር ተጣምሮ የሚገነባበት ጥያቄ ቁልፍ አጀንዳ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

አሁን ላይ የምክክር ኮሚሽኑ ወደ ተሳታፊዎች መረጣ ገብቷል፡፡ በመሆኑም አገርን የመታደጉ ሰፊ ዕድልም ከ700 ሺህ በላይ ተሳታፊዎች እንደዚሁም ቀጥተኛ ያልሆነ ተዘዋዋሪ ተሳትፎ ባላቸው ሌሎች ታዛቢዎች፤ በአጠቃላይ በአገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ እጅ ላይ ነው ያለው ማለት ይቻላል፡፡ ተግባሩ ለስኬት ሲበቃ የኮሚሽኑ አስተዋጽኦ ቀላል አይሆንም፡፡ አሁን ላይ እንደ አገር እያጋጠሙ ያሉ ፈተናዎችን በአስተማማኝ ሁኔታ እንድንሻገር ይረዳል፡፡ ለመሻገር መርዳት ሳይሆን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያሻግራል፡፡ የነገ ተስፋችንንም ብሩህ ያደርግልናል፡፡ የአገረ መንግስቱን ግንባታ ጥሩ መሰረት ላይ በማሳረፍም አገሪቱን ከመፍረስ አደጋ፤ ሕዝቧን ከስደት፤ ከረሀብ፤ ከርዛትና ከግጭትና ሁከት ይታደጋል ተብሎ ይጠበቃል!

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## ከትናንትናው እውነታ ...

መልካምሥራ አፈወርቅ



### እንደመነሻ ...

ዛሬም በርካታ የማንነት ፈተናዎች ከታለፉበት፣ ብዙ የህይወት እጥፋቶች ከተዘረጉበት፣ አሰልቺ የኑሮ ውጣወረዶች ከሚተረኩበት ሰፊ ግቢ ውስጥ እገኛለሁ። አሁንም እንደዋዛ ያለፉ የማይመስሉ ፣ አስደናቂ ታሪኮችን እየሰማሁ ነው::

በትናንቱ የህይወት መንገድ እንደጥላ እልፍ ብለው ከሄዱት እውነታዎች መሀል በርካቶቹን በአግርሞት አደመጥኩ:: እነዚህ ታሪኮች የዕንባና ሳግ ስሜት ይዘዋል :: ለእያንዳንዱ ባለታሪክ ያልደበዘዙ ማህተሞች ሆነው ጊዜያትን ቆጥረዋል :: ከማንነታቸው ተዋህደው፣ ከሀዘን ደስታቸው ተቀድተው ዛሬን ደርሰዋልና በአይረሴ ትዝታዎች ሁሌም ይተረካሉ::

እነዚህ ሀቆች ትናንትን አልፈው ለዛሬ መታወሳቸው በምክንያት ሆኗል :: ‹‹ነበር›› ሲሉ ለማውሳት፣ ‹‹አልፏል›› ብሎ ለመንገር የመልካም ሰዎች ጥረትና ስብዕና ታክሎበታል:: በሰፊው የሚሰጡ እጆች ፣ ቸርነት አርፎበታል:: ትናንትን አልፎ ዛሬን ለማንጋት፣ ትጋት ከቅንነት፣ ቅንነት፣ ከበጎፈቃድ ተሳስሮ ‹‹ሰው›› ይሉት ማንነት ተገንብቷል ::

ይህ ሁሉ የሆነው ግን መንገዶች ሁሉ አልጋ በአልጋ ሆነው አልነበረም:: ያለፈን ታሪክ ለመቀየር፣ ጨለማውን በጸሀይ ለመተካት ብዙ ጋሬጣዎች፣ በርካታ ሻካራማ መንገዶች ታልፈዋል::

ዛሬ በሙዳይ በጎ አድራጎት ቅጥር ግቢ በርካቶች በሰላማዊ ዕንቅልፍ እፎይታን ተችረዋል:: አሁን ያለፈ ህይወታቸው የማንነታቸው ታሪክ ሆኖ ተሰናብቷል:: ዛሬን በአዲስ ትንፋሽ በተቀበሉት አዲስ ዓለም ስለነገ መንገዳቸው ይወጥናሉ :: ስለመጪው ህይወታቸው ያስባሉ:: ትናንትና በራሱ ታሪክ ሆኖ ቢሸኝም ፣ የማንነታቸው እውነታ ግን ‹‹ነበር›› ተብሎ እንዲህ ይተረካል::

### እንግዳዋ...

አንድ ማለዳ የሙዳይን ቅጥር ግቢ አልፋ የገባችው ሴት ከቢሮው ደርሳ በሩን በዝግታ አንኳኳች:: ሴትዮዋ ብቻዋን አልነበረችም:: በቅርብ የተወለደ ጨቅላ አዝላለች። የጀርባዋን ልጅ በአንድ እጇ እየመታች አጥብቃ የያዘቻትን ትንሽዬ ህጻን እየጎተተች ወደውስጥ አለፈች:: ለወይዘሮ ሙዳይ እሷን መሰል እንግዶች ማግኘት ብርቅ አይደለም:: በየቀኑ በርካቶችን እየተቀበለች ማስተናገድ ልምዷ ነው::

እንግዳዋና ሙዳይ ጭውውት ይዘዋል:: ሙዳይ ጥያቄዋን አውቃ ፍላጎቷን ልትሞላ ቃል ገብታለች:: ሴትዬዋ በትዳር አብሯት የቆየው ባሏ ትቷት ከጠፋ ቆይቷል:: በአራስ ጎኗ ልጆቿን ማሳደግ፣ ራሷን መምራት ቢሳናት አገሯ ልትገባ ወስናለች::

ውሳኔዋ ግን እንዳሰበችው አልሆነም:: አቅም ቢያንሳት፣ እጅ ቢያጥራት መላ ዘዴውን ፈለገች :: ‹‹አያሳፍረኝም›› ካለችው ግቢ ደርሳ ማልዳ በሩን አንኳኳች:: ወይዘሮ ሙዳይ በሰማችው ታሪክ ከልብ አዝና ለመንገዷ ይበቃል ያለችውን ገንዘብ ቆጥራ ሰጠቻት::

እመጫቷ በተሰጣት ፣ በሆነላት ሁሉ ተደሰተች። ከታላቅ ምስጋና ጋርም ግቢውን ለቃ ወጣች:: አሁን አገሯ የሚያደርሳትን በቂ መሳፈሪያ ይዛለች:: የምትሄድበት ቦታ ተወልዳ ያደገችበት፣ ደግ ክፉ ያለፈችበት ቀዬ ነው:: የእሷ መሄድ አሁን ካለችበት በተሻለ ነገን እንደሚያሻግራት ታምናለች ::

ይህ በሆነ ማግስት እመጫቷ ልጇቿን ይዛ ወደ ትውልድ አገሯ አቀናች:: አገር ቤት የረገጠው እግሯ ቀድሞ ያመራው ወደ ቤተሰቦቿ ቤት ነበር:: እንደገባች ዘመዶቿን በአካል አገኘች:: በደስታ፣ በፈፈግታ የተቀበላት የለም:: በትናንት ማንነቷ የሚያውቋት ሁሉ ፊት አዞሩባት :: ሰርታ ትለወጣለች ያሏት ወጣት ሁለት ልጆች ይዛባቸው መምጣቷ አልተመቻቸውም::

ውሎ አድሮ የልጆቹ አባት ከጎኗ እንደሌለ ባወቁ ጊዜ ፊት እየነሱ አገለሏት :: እየደጋገሙም ልጆቿ ‹‹ዲቃላ›› መሆናቸውን ይነግሯት ያዙ:: ይህን ስታይ ከፋት፣ ሆድ ባሳት። በዘመድ መሀል ባዕድ መሆኗ ተሰማት :: በድንገት የሰው አገር ሰው የሆነች አስኪመስላት ተከዘች:: ተስፋ አልቆረጠችም። ነገሮች እንደሚቀየሩ ገምታ ቀናትን ቆጠረች:: አዲስ ለውጥ አልመጣም::

አባት አልባ ሁለት ህጻናት ያላት ሴት አሁን ተስፋ ቆርጣለች:: ከእንግዲህ ማንም ከጎኗ የለምና መወሰን ፣ መቁረጥ አለባት:: ከዚህ በኋላ በማይፈልጓት ሰዎች መሀል መኖር ህይወቷን ይፈትናል:: ቆም ብላ አሰበች:: መላልሳ ከራሷ መከረችና ከውሳኔ ደረሰች:: ወደመጣችበት ከመመለስ ሌላ ምርጫ አልነበራትም::

### የመልስ ጉዞ ...

እመጫቷ እንግዳ ዘመዶቿ ፊት ቢነሷት መኖር ተስኗታል:: ውላ አድራም ከራሷ መክራ ከውሳኔ ደርሳለች:: አሁን ያመጧት እግሮቿ መልሰው እየወሰዷት ነው:: አዲስ በባ ስትደርስ የተቀበላት አልነበረም:: ሁለት

ከትናንትናው ... ወደ ገጽ 17 ዞሯል

## ከአማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የሚጥል በሽታ (ኢፒሊፕሲ) ምንድነው ?

የሚጥል በሽታ (ኢፒሊፕሲ) በተለምዶ የሚጥል ህመም የሚባል ሲሆን በእኛ ማህበረሰብ ዘንድ ብዙም ትኩረት ያልተሰጠው ጉዳይ ነው። በዚህ ህመም የሚጠቁ ሰዎችም ትኩረት ያልተሰ ጣቸው እና መድሃኒት የለውም ተብሎ ስለሚታሰብ ራሳቸውን ስተው በሚወድቁበት ጊዜ ተገቢውን እርዳታ አያገኙም። በዚህም የተሳካ የማህበራዊ ግንኙነት ለማድረግ ይቸገራሉ።

የሚጥል በሽታ (ኢፒሊፕሲ) በአንጎል ነርቮች ላይ ተገቢ ባልሆነ እና በበዛ የኤሌክትሪክ ፍሰት ምክንያት የሚከሰት ነው። ምልክቶቹም በተለምዶ የሚታወቀው ራስን ስቶ በመውደቅ እና አንዳንድ ጊዜም ራስን ሳያስት እንዲሁም ሳይጥል በአንድ ጎን የሰውነት ክፍል ማንቀጥቀጥ ነው። በዛሬው እትማችን የሚጥል በሽታ (ኢፒሊፕሲ) ሊከሰቱ የሚችሉባቸውን መንገዶች፣ አይነት እና ሊያደርጓቸው የሚገቡ ጥንቃቄዎችን እንመለከታለን።

የሚጥል በሽታ በዘመናዊ የህክምና መንገድ ክትትል ማድረግ የሚቻል እና መዳን የሚችል ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰት ይችላል። ከወሊድ በፊት እና ከወሊድ በኋላ ህፃኑ/ህፃኗ ላይ የሚደርስ አደጋ ዋነኛ ምክንያት ሲሆን ከእናት ህመም እና አስቸጋሪ ምጥ ጋር ሊያያዝም ይችላል። ሌላው ደግሞ በህፃንነት ጊዜ የነበሩ ሀይለኛ የትኩሳት በሽታዎች ሲሆኑ ከዚህ ውጪ ከአንጎል ህመም ጋር በተያየዘ ደግሞ አንጎል ውስጥ በሚያድጉ እጢዎች ፣ የአንጎል ኢንፌክሽን ማለትም እንደማጅራት ገትር የአንጎል ወባ፣ አንጎልን እና ነርቭን የሚጎዱ ህመሞች ፣ በተለያየ አደጋ ጭንቅላት ሲመታ እና አንጎል ላይ አደጋ ሲደርስ ሊከሰት ይችላል::

ከዚህ በተጨማሪም በሰውነት ውስጥ የሚገኙ ሰውነትን የሚጠቅሙ ንጥረ ነገሮች በበቂ ሁኔታ አለመገኘት ለምሳሌ በደም ውስጥ የስኳር መጠን መቀነስ ሲሆን ለረጅም አመት አልኮል መጠቀም፣ የአካል በመርዝ መበከል፣ ራስን ለማጥፋት ተብለው በሚወሰዱ የተለያዩ መድኃኒቶች እና ከላይ የተጠቀሱት ለሚጥል በሽታ (ኢፒሊፕሲ) ሊያጋልጡ የሚችሉ ናቸው። በሽታው በአጠቃላይ የሚጥል በሽታ ተብሎ ይጠራ እንጂ የተለያየ አይነት የሚጥል በሽታ አይነቶች አሉ። ምልክቱ እና ሊደረግ የሚገባው ጥንቃቄም እንደዚሁ የተለያየ ነው::

**ግራንድ ማልሲዠር፡-** የሚጥል በሽታ አይነት ሲሆን በዚህ በሽታ የተጠቁ ሰዎች ከመውደቃቸው የተወሰኑ ደቂቃዎች በፊት የመረበሽ እና የፍርሀት ስሜት ይሰማቸዋል። በሚወድቁበት ጊዜም ማንቀጥቀጥ፣ ራስን እንደሳቱ መቆየት፣ የሰውነት መገታተር አረፋ መድፈቅና ሽንት መልቀቅ የሚታይባቸው ሲሆን ከነቁ በኋላም የመርሳት፣ ከባድ እንቅልፍ እና የራስ ምታት ስሜቶችን ያስተናግዳሉ::

በዚህ ህመም የተጠቁ ሰዎች ራሳቸውን ስተው በሚወድቁበት ጊዜ ህመምተኛውን ከውሃ ፣ እሳት ካለበት ቦታ እና ከመኪና መንገድ ማራቅ የሚገባ ሲሆን ከጭንቅላት ስር ለስላሳ ነገር በማድረግ ልብሶቹን ማላላት መነፅር ካለ ማውለቅ፣ ህመምተኛወን በአንድ ጎን ማስተኛት እና እስኪነቃ ድረስ ከህመምተኛው ጋር መቆየት ይገባል::

**ፔፕቲማል (አብሰንስ)፡-** ይሄ ሁለተኛው የሚጥል በሽታ አይነት ሲሆን በብዛት የሚፈጠረው በህፃናት ላይ ነው። ምልክቶቹ ከመፈጠራቸው በፊት ምንም ስሜት አይስማቸውም ነገር ግን በድንገት ንቃተ ህሊናን ማጣት፣ መንቀሳቀስ እና መናገር ማቆም፣ ወደ አንድ አቅጣጫ አይናቸውን ማዞር የአይን ሽፋሽፍት፣ የፊት ጡንቻ እና የጣት መንቀጥቀጥ ይታይባቸዋል፤ አንዳንድ ጊዜም ከንፈር መምጠጥ እና ማኘክ ይታይባቸዋል።

ከላይ የተጠቀሱት ምልክቶች የሚቆዩት በአብዛኛው ለ10 ሰከንድ ያህል ሲሆን በተደጋጋሚ ሊከሰትም ይችላል::

**ሲምፕል ፓርሻል ሲዠር፡-** ይህ የሚጥል በሽታ አይነት በተወሰነ የሰውነት ክፍል ላይ ብቻ የሚከሰት ሲሆን በሁለት ይከፈላል። **አንደኛው ሲምፕል ፓርሻል** የሚባል ሲሆን በአንድ ጎን እጅና እግርን የማንቀጥቀጥ ምልክት አለው። እራስን መሳትም ሆነ መሬት ላይ መውደቅ በዚህ የበሽታ አይነት ላይ አይከሰትም። ሁለተኛው ደግሞ ኮምሌክስ ፓርሻል ሲዠር ይባላል። ይህ በሽታ ያለባቸው ሰዎች ደግሞ ህመሙ ሲጀምራቸው አካባቢን በአግባቡ የመረዳት እና የመገንዘብ ችግር ፣ የእይታ መጭበርበር ከተፈጥሮ ውጭ የሆነ ሌላ ድምፅ የማስተናገድ ስሜት የሚያጋጥማቸው ሲሆን ከንፈር መምጠጥ ፣ መሳቅ፣ መሮጥ፣ መቆጣት እና ስሜታዊ መሆን የመሰሉ የባህሪ ለውጦች ይታይባቸዋል። ከነዚህ ምልክቶች በኋላም በአብዛኛው መርሳት ከባድ እንቅልፍ እና ራስ ምታትንም ያስተናግዳሉ።

**ስታተስ ኢፒሊፕቲክስ፡-** ይህ በተደጋጋሚ የሚከሰት የሚጥል የበሽታ አይነት ሲሆን ብዙ ጊዜ የሚከሰተው መድኃኒት በድንገት ማቋረጥ ወይም መመረዝ ምክንያት ነው። በፍጥነት ወደ ህክምና ተቋም ካልተወሰደና ተገቢውን የመድኃኒት እና ሌሎች እርዳታን ካላገኘ ሞትን ሊያስከትል ይችላል::

**ፌብራይል፡-** ይህ የበሽታ አይነት በአብዛኛው ከትኩሳት ጋር በተያያዙ በሽታዎች የሚመጣ ነው። በአብዛኛው በህፃናት ላይ ይከሰታል። ይህንን ህመም የሚያስከትሉ በሽታዎችም እንደ ጉንፋን፣ የጆሮ ኢንፌክሽን የመሳሰሉት ሲሆኑ በቀዝቃዛ ፎጣ ትኩሳቱን ለማብረድ መሞከር እና ህፃኑን/ህፃኗን ለምርመራ መውሰድ ተገቢ ነው። በዚህ ህመም የተጠቁ ሰዎች የአካል እና የአዕምሮ ጤንነትን መጠበቅ፣ በቂ እንቅልፍ መተኛት፣ ሱስ አስያዥ ንጥረ ነገሮችን አለመውሰድ እና ጭንቀትን ማራቅ ይገባቸዋል።

የሚጥል በሽታ ከጥቂት አመታት እስከ እድሜ ልክ ክትትል ሊያስፈልገው የሚችል የህመም አይነት በመሆኑ ህክምናው ከተጀመረ በኋላ ሐኪሙ አቁሙ እስካለ ድረስ ታካሚው መድኃኒቱን በታዘዘለት መጠን እና ሰዓት መውሰድ ይኖርበታል በሽታው መጣሉን ቢተውም እንኳን መድኃኒቱን ማቋረጥ አይገባም ፤ መድኃኒቱ ሙሉ ለሙሉ ከማለቁ በፊት ሌላ ማሳዘዝ እና ሩቅ መንገድ በሚጓዙበት ጊዜ መድኃኒቱን ይዞ መሄድ ያስፈልጋል።

በዚህ በሽታ የተያዙ ሰዎች በአካባቢያችን ወይም በቤተሰባችን አባል የሚገኙ ከሆነ ደግሞ ትኩረት በመስጠት መድኃኒታቸውን እንዲወስዱ ከማስታወስ ባሻገር በሚወድቁበት ጊዜ ተለምዶአዊ የሆነውን አፍንጫቸው ላይ ክብሪት ማሽተት፣ የሚያንቀጠቅጣቸውን ለማስቆም መሞከር፣ የሚጠጣ ነገር መስጠት ወይም አፋቸውን ውስጥ ሌላ ነገር ለማስገባት መሞከር አይገባም።

# እንዲህም ይኖራል

## ከትናንትናው ...

**ከ16ኛው ገጽ የዞረ**

ህጻናት ልጇቿን ይዛ መንከራተት ጀመረች፡፡ እነሱን እያሉ በሰራተኝነት የሚቀጥራት እንደማይኖር ታውቃለች። ጥቂት ቆይታ ግን በራሷ ወሰነች፡፡ ከነ ልጆቿ ያለምንም ደሞዝ ከሚያሰሯት ሰዎች ዘንድ ተቀጠረች፡፡ አሁን ለእመጫቷ ህይወት በመጠኑ የቀለለ መስሏል፡፡ ጉልበቷን እየከፈለች የዕለት ጉርስ ታገኛለች፡፡ ስራ መግባቷ ጎዳና ከመውደቅ. የሰው እጅ ከማየት አድኗታል፡፡

ዓመታት ያለ ደሞዝ ክፍያ ቀጠሉ፡፡ እናት ሁለት ልጆቿ እያደጉላት ነው፡፡ እሷ በምትከፍለው የላብ ዋጋ እነሱ በልተው ከቤት ውለው አድረዋል፡፡ ያለአባት ያለማንም እገዛ የሚኖሩት ህጻናት ከእናታቸው ውጭ ሌላ ዓለም አያውቁም፡፡ ህይወትና ተስፋቸው እሷና እሷ ብቻ ነች፡፡

እናት ወር ሙሉ ሰርታ ደሞዝ ይሉትን አትጠብቅም። እንደሌሎች ያማራትን መግዛት፣ ያሻትን ማድረግ አትሞክርም ፡፡ የእሷ ክፍያ የልጆቿ መኖር ፣ የወር ደሞዟም ከቤት ውሎ ማደር ነው፡፡

### አጋጣሚው...

ከቀናት በአንዱ በአሰሪዎቿ ቤት እንዲህ ሆነ ፡፡ ትልቋ ልጅ በድንገት ቤት የነበረን መስታወት ሰበረች። ይህን ያዩ ባለቤቶች በእጅጉ ተቆጡ፡፡ ድርጊቱ የሆነው በአንዷት ትንሽ ልጅ እጅ ቢሆንም «ይቅር» ማለትን አልወደዱም።ቁጣና ተግሳጽ ያልበቃቸው ሰዎች አስቸኳይ ርምጃ ወሰዱ። ዓመታትን ያለክፍያ አብራቸው የዘለቀችው ሰራተኛ ልጆቿን ይዛ እንድትወጣ ወሰኑባት፡፡

ይህ አይነቱ ድንገቴ ጉዳይ ለልጆቹ እናት አስደንጋጭ ነበር፡፡ በዓመታት ቆይታዋ የቋጠረችው ገንዘብ፣ ለእኔ የምትለው ጥሪት የለም፡፡ ቤቱን ለቃ ስትወጣ በእጇ የነበሩት ሁለት ልጆቿ ብቻ ናቸው፡፡ ዛሬም ትጠጋበት ትጠይቀው ወዳጅ ዘመድ አታገኝም፡፡

አሁንም እንደቀድሞው ምርጫ ይሉት የላትም ፡፡ እንዲያም ሆኖ በዝምታ አልቆየችም፡፡ ልጇቿን እንደያዘች በቤት ሰራተኝነት ያለደሞዝ ለመቀጠር ተማጸነች፡፡ ይህን ማሰቧ ብቻውን መፍትሄ አልሆነም፡፡ እሷን እንጂ ልጆቿን ያልፈለጉ ቀጣሪዎች ዕድል ነፈጓት፡፡ «እንቅጠራት» ያሉ ጥቂቶች ደግሞ ቅድመ ሁኔታ አስቀመጡ፡፡ ተያዥ የሚሆናት ዋስ እንድታመጣ አጥብቀው ጠየቁ ፡፡

ይህን ማድረግ ያልቻለችው እናት ዳግም በሀሳብ ተዋጠች፡፡ እንዳሰበችው ዕቅድ፣ ውጥኗ አልተሳካም፡፡ በተስፋ መቁረጥ ተመላለሰች፡፡ ያልሰመረው ሙከራዋ እንደጅምሩ አልቀጠለም፡፡ ውሎ አድሮ የመጀመሪያ ማረፊያዋ ከጎዳና ዳር ሆነ ፡፡

### ሕይወት በጎዳና ...

አሁን እናትና ልጆች ከቤት ወደ ጎዳና ወጥተዋል፡፡ ይህ ቦታ ለነዚህ ነፍሶች አዲስ ዓለም ነው፡፡ በዚህ ስፍራ ኑሮ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ቀኑ በጭንቅ ያልፋል። ጨለማው ይዞት የሚመጣው ጣጣ ለሴት ልጅ ይከብዳል ፡፡ እናት ልጆቿን ታቅፋ ቀናትን በጎዳና ላይ ገፋች፡፡

ለዕለት ጉርስ እጇን መዘርጋት ስትጀምር ልጆቿን ያዩ የእጃቸውን ይጥሉላት ያዙ፡፡ በሌላ ወገን ጎዳና መምጣቷን ያስተዋሉ አንዳንዶች በትኩረት ዓይን ጣሉባት፡፡ ልጆች ብትይዝም ወንዶቹ ሊምሯት አልፈለጉም ፡፡ ሊተናኮሏት፣ ሊደፍሯት ቀን አስልተው ማድባት ያዙ፡፡

አንድ ሌሊት ሴትነቷን ያሰቡ ጥቂት ወንዶች ጨለማውን ተተግነው ወደእሷ ተጠጉ፡፡ ሁኔታቸው የገባት እናት ልጆቿን እንደያዘች ልትታገላቸው ሞከረች፡፡ ይህ ሙከራዋ ድርጊቱን አስቁሞ በአካሏ ጉዳት አስከተለ ።፡ አንድ እጇ ክፉኛ ተሰበረ፡፡

ከዚህ ምሽት በኋላ የእናትና ልጆች የጎዳና ዓለም ስጋት ገባው ፡፡ የምሽቱን ችግር ለመከላከል ቀኑን በመኝታ የምታልፈው ሴት ሌሊቱን ያለዕንቅልፍ ማደር ልምዷ ሆነ፡፡ ለእሷ የቀንና ሌቱ መለዋወጥ ለምና እንዳታድር ምክንያት ፈጠረ፡፡ አሁን ልጆቿ ሊራቡ እሷም ልትቸገር ነው ፡፡

ይህ ሲገባት ዕቅዷን ቀየረች፡፡ ለሌቱን ከቤተክርስቲያን እያደረች ቀኑን ለዕለት እንጀራዋ አዋለች ፡፡ በዚህ መንገድ ብዙ አልቀጠለችም፡፡ ቤተክርስቲያን ማደሯ ሲታወቅ በግቢው ድርሽ እንዳትል ታገደች፡፡ አሁንም እናት ስለልጆቿ መኖር አርቃ አሰበች፡፡ ከእንግዲህ ተስፋ የምትለው ምርጫ ተሟጧል፡፡

### ‹‹እሰሩኝ...››

አስቸጋሪው እውነታ ከሌለው ጥግ አደረሳት፡፡ ለህይወቷ መላ ያጣችው ሴት ከፖሊስ ጣቢያ ደርሳ ‹‹በቃ ! እሰሩኝ›› ስትል እጇን ሰጠች፡፡ ሁኔታዋ ያሳዘናቸው ፖሊሶች አልጨከኑም ፡፡ ቀን ስትለምን ውላ ማታ ከእስረኞች ጋር እንድታድር ፈቀዱላት፡፡

ይህ ዕድል ግን ብዙ አልቀጠለም፡፡ ለአዳር መመላለሷን ያልወደዱት ሌሎች ፖሊሶች ‹‹ሁለተኛ እንዳትመጪ›› ሲሉ ከለከሏት፡፡ መፍትሄ ያጣችው እናት ዳግመኛ ሀዘን ዋጣት ፡፡ ከእንግዲህ ደፍራ ጎዳና መመለስ አትችልም፡፡ ይህን ልሞክር ብትል በእሷና በልጆቿ ያለፈው ክፉ ታሪክ ይደገማል፡፡

ከጣቢያው በተባረረች ማግስት ከስፍራው አልራቀችም፡፡ ከእይታ ሳትወጣ ከፖሊስ ጣቢያው ፊት ለፊት ከሚገኝ ስፍራ ማረፊያዋን አደረገች፡፡ እንዲህ መሆኑ ቢያንስ ከጥቃት እንደሚታደጋት አምናለች፡፡ እናት አሁንም ከነበረችበት ህይወት አልወጣችም፡፡ በቀን ውሎዋ ከልመና ተቀምጣ ለአዳር ልጆቿን ይዛ ትመጣለች፡፡

አሁንም እየተጨነቀች፣ እየተከዘች ብዙ አሰበች። መስራት የለመዱ እጇቿ ለልመና መዘርጋታቸው አብዝቶ ይቆጫታል፡፡ ይህ የሆነው ስለልጆቿ መሆኑን ታውቃለች። ለእነሱ መኖር ያልከፈለችው ዋጋ የለም፡፡ በዚህ ዕውነት የእናትነት ፍቅሯ አስገድዷት ብዙ ሆናለች፡፡

ይህን እያሰበች ዓይምሮዋ ርቆ ተጓዘ፡፡ ከዓመታት በፊት በሙዳይ በጎአድራጎት ግቢ የተዘረጉላትን ቸር እጆች አስታወሰቻቸው፡፡ ልቦናዋ መላልሶ ያለፈውን እውነት አስታወሳት፡፡ አንዳች ሀይል ስፍራው እንድትደርስ ሹክ ሲል ተሰማት፡፡ ካለችበት ተነስታ በፍጥነት ወደስፍራው ተጓዘች፡፡

### በሩ ሲከፈት...

የጎዳናዋ ሴት ግቢውን አልፋ የቢሮውን በር በዝግታ አንኳኳች፡፡ ከበሩ ጀርባ ያለ የሴት ድምጽ ‹‹ይግቡ›› ሲል ተሰማት፡፡ ይህን ድምጽ ከዚህ በፊት ታውቃዋለች። አላንገራገረችም በሩን በፍጥነት ከፍታ ፊት ለፊት ከምታያት ወይዘሮ ጋር ተፋጠጠች፡፡

በእንግድነት ከበሩ የቆመችው ሴት ከወይዘሮ ሙዳይ ጋር ማውራት ይዛለች፡፡ እዚህ ስፍራ የመጣችው ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት አራስ ልጇን አዝላ ትልቋን ልጅ እየጎተተች ነበር ፡፡ የዛኔ የተቀበላት መልካም ፊት ዛሬም አልተለወጠም። አሁንም የሚያደምጡ ጆሮዎች ፣ በጥልቅ የሚያስተውሉ ዓይኖች ከእሷ ጋር ሆነዋል፡፡

የልጆቹ እናት የነበረውን አስታውሳ ከእሷ ከተለየች የሆነባትን ታሪክ ሁሉ አወጋች፡፡ ሙዳይ በሰማችው አሳዛኝ ጉዳይ ሁሉ አዝና ሊደረግላት የምትሻውን ጠየቀቻት ፡፡ ሁለቱ ሴቶች ልብ ለልብ ተግባቡ፡፡ ይሻላል ካሉት ውሳኔ ለመድረስ ጊዜ አልባከነም፡፡

እናት ከልጆቿ ጋር ለመጨረሻ ጊዜ ጎዳናውን ተሰናበተች፡ ፡ የመጀመሪያው ለውጥም ሴት ልጇን ትምህርትቤት በማስገባት ተጀመረ ፡፡ ትንሹ ልጅ በማዕከሉ እያደገ ህይወት በመልካም መስመር ቀጠለ፡፡

እናት ልጆቿ ቦታ ሲይዙ ሙያዊ ስልጠና አገኘች። በማዕከሉ የሸክላ ስራን ተምራ በብቃት አጠናቀቀች፡፡ ስልጠናው ምርጥ ባለሙያ አድርጎ ለምርጫ አቀረባት ።፡ ትናንት ለልመና የተዘረጉ እጆች አሁን ለስራ ሰልተው ተጉ። ቀድሞ በሀፍረት የተሰበረ አንገት ዛሬን በኩራት ተቃና፡፡

ከሸክላው ስራ ጎን ለማዕከሉ እንጀራ የምትጋግረው ሴት በእጇቿ ሙያ የተመረጠች ተደናቂ ሆነች፡፡ ውሎ አድሮ በራስ መተማመኗ ዳበረ ፡፡ ይህኔ ለህይወቷ ይበጃል ያለችውን ስራ ለየች፡፡ ወደፊት ያዋጣል ባለችው የእንጀራ መጋገር ስራም አተኮረች፡፡

በዚህ ፍላጎቷ ሁሉ የሙዳይ በጎ አድራጎት ማህበር ከጎኗ አልራቀም፡፡ የጎደለውን እየሞላ ፣የጠየቀችውን እየሰጠ በእርምጃዋ ልክ ተከተላት፡፡ ልጆቿን በትምህርት አልቃ ራሷን የቻለችው ሴት የትናንት ታሪኳን ለውጣ የደሞዝ ተከፋይ ሆነች።

ውሎ አድሮ ጠንካራዋ ሴት ቤት ተከራይታ ያጣችውን ህይወት መለሰች፡፡ በተሟላ የቤት ዕቃ፣ የጎዳናን ታሪክ ‹‹በነበር›› የተካችው ወይዘሮ ዛሬ ስለሆነላት እንጂ ስለሆነባት ክፉ ታሪክ ብቻ አታስብም ፡፡ ለእሷ የትናንት ታሪኳ በዛሬው ስኬት ተክሷል፡፡ የፈሰሰ ዕንባዋ በጥንካሬዋ ታብሷል፡፡ ያለፈ ፈተናዋ ለዛሬ ማንነቷ ድንቅ አሻራ ነው ፡፡ አዎ! ትናንት በራሱ ታሪክ እንዲህ ሆኖ ታልፏል፡፡ ይህ ይሆን ዘንድ ሙዳይን መሰል በጎ አድራጊ ልቦና እስትንፋስን ለማስቀጠል እውነተኛ አጋር ሆኗል፡፡


# የጨረታ ማስታወቂያ

## የጨረታ ቁጥር 011/2015 ዓ.ም

ድርጅታችን ለ2016 በጀት አመት የጠረጴዛ ካላንደር፣ የግድግዳ ካላንደር እና የኪስ ካላንደር በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም ተጫራቾች፡-

1. የታደሰ ፍቃድና የዘመኑን ግብር ለመክፈላችሁ መረጃ ማቅረብ ይኖርባችኋል፡፡
2. የማይመለስ ቫትን አካቶ በብር 115.00 /አንድ መቶ አስራ አምስት ብር/ በመክፈል ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጨረታ ሠነዱን መካኒሳ በሚገኘው ዋናው መ/ቤት ገንዘብ ቤት ቢሮ ቁጥር 004 በመቅረብ መግዛት የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
3. ፋይናንሻል ሰነድ ኦሪጅናል እና ፎቶ ኮፒ ለየብቻው በታሸገ ኤንቨሎፕ ማቅረብ ይኖርባችኋል፡ ፡ የሚቀርበው ዋጋ ቫትን ያካተተ መሆን አለመሆኑ በግልጽ መቀመጥ አለበት፡፡
4. ለጨረታ ዋስትና የሚሆን የሚያቀርቡትን አጠቃላይ ዋጋ 2% በሲፒኦ ለብቻው በኤንቨሎፕ በማሸግ ማስያዝ ይጠበቅባችኋል፡፡
5. ተጫራቾች ዋጋ ላቀረቡባቸው ካላንደር ናሙና ማቅረብ አለባችሁ፡፡
6. ተጫራቾች የሚያስገቧቸውን ሠነዶች ሰኔ 22 ቀን 2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት መካኒሳ በሚገኘው ዋናው መ/ቤት ግዥ ቢሮ ቁጥር 503 ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

ጨረታው በዚያው ዕለት ከጠዋቱ 4፡15 ሠዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፤

7. ድርጅቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ፖ.ሣ.ቁ. 3516 ስልክ 011-369-05-63 ፋክስ 0115-51-32-99**

**ብሔራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካ**



# የጨረታ ማስታወቂያ

የቡታጅራ ከተማ ማረሚያ ተቋም በህግ ጥላ ስር ለሚገኙ ለህግ ታራሚዎች ከሀምሌ 01/2015 እስከ ታህሳስ 30/2016 ለ6 ወር የምግብ እህል እና ለማጣፈጫ የማገዶ እንጨት አገልግሎት አስከ የሚውሉ

ሎት 1 እህሎች

ሎት 2 ማጣፈጫ

ሎት 3 የማገዶ እንጨት

የዘመኑ የስራ ግብር የከፈሉ ተጫራቾች የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ የ2015 ዓ.ም ፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ/ ኒሮ ተመዝጋቢ የሆኑ የአቅራቢነት የምስክር ወረቀት ያላቸው ይዘው በመቅረብ የማይመለስ ብር 50 ብቻ ከፍለው የጨረታ ሰነድ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ 15 ተከታታይ የስራ ቀናት ከማረምያ ቤቱ ግ/ፋ/ን አስተዳደር ቢሮ ቁጥር 02 መግዛት ይችላሉ፡፡

1. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ለእህል 10,000 ለማጣፈጫ እና ለማገዶ እንጨት ብር 3,000 በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ጋር በማያያዝ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ለዚህ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
2. ጨረታው የሚከፈተው በ16ኛው ቀን 4፡00 ሰዓት ታሽጎ ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ጨረታው 4፡30 ሰዓት ላይ በቡታጅራ ከተማ ማረሚያ ተቋም ግ/ፋ/ን/ አስተዳደር ቢሮ ቁጥር 02 ይከፈታል ባይገኙም ከመከፈት አይታገድም፡፡
3. ተጫራቾች ያሸነፉትን ንብረት በራሳቸው ትራንስፖርት ቡታጅራ ማረሚያ ተቋም ድረስ በመምጣት ማስረከብ አለባቸው፡፡
4. ጨረታው የሚከፈትበት ቀን በስራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን ይሆናል፡፡
5. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
6. ተጫራቾች የእህል ናሙና ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
7. የውል ማስከበሪያ ያሸነፉትን 10 ፐርሰንት ማስያዝ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

**ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር፡- 046-115-10-51/ 046-115-09-03**

**የቡታጅራ ከተማ ማረምያ ተቋም**

# ስፖርት





## ኢትዮጵያ በስፔሻል ኦሊምፒክ በአራት አትሌቶች ትወከላለች

**ዓለማየሁ ግዛው**

የ2023 የዓለም ስፔሻል ኦሊምፒክ ጨዋታዎች ከዛሬ ጀምሮ በጀርመኗ በርሊን ከተማ ለዘጠን ተከታታይ ቀናት ይካሄዳል፡፡ በዘንድሮ ውድድር ከ190 ሀገራት የተወጣጡ 7000 የአእምሮ ውስንነት ያለባቸው አትሌቶች በ26 የስፖርቶች ዓይነቶች በሁለቱም ጾታ ውድድራቸውን ያደርጋሉ፡፡ ኢትዮጵያም ከተሳታፊዎቹ ሀገራት አንዷ ስትሆን በሁለት ወንድና በሁለት ሴት አትሌቶች የምትወከል ይሆናል፡፡ ውድድሩ በጀርመን ኦሊምፒክ ስቴድም የሚካሄድ ሲሆን አትሌቶቹን የሚመሩ 30 ሺ አሰልጣኞች እና ለውድድሩ መሳለጥ 20ሺ በጎ ፍቃደኞች ዝግጁ መሆናቸው ታውቀል፡፡

ኢትዮጵያ እአአ በ2019 አቡ ዳቢ ላይ በተካሄደው የዓለም ስቴሻል ቻምፒዮና ተጋብዛ ተሳትፎዋን ካደረገች በኋላ ዘንድሮ ለ2ኛ ጊዜ ትሳተፋለች፡፡ በመጀመርያ ተሳትፎዋም ሁለት የነሐስ ሜዳለያ ማሳካት ችላለች። ኢትዮጵያ የሚወከለው ብሔራዊ ቡድን የተለያዩ ዝግጅቶችን ሲያደርግ ቆይቶ ከቀናት በፊት ወደ ውድድሩ ስፍራ ሽኝት ተደርጎለታል፡፡ በውድድሩ የሚሳተፉ ስፖርተኞች በልዩ ሁኔታ እንክብካቤና ድጋፍ የሚያስፈልገቸው ቢሆንም ከተለያዩ አካላት የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑን የኢትዮጵያ ስፔሻል ኦሊምፒክ ኮሚቴ አስታውቋል፡፡

የኢትዮጵያ ስፔሻል ኦሊምፒክ ልዑካን ቡድን በታሪኩ ለሁለተኛ ጊዜ በትልቅ ውድድር ለመሳተፍ ወደ ስፍራው ሲያቀና ግን በደማቅ መርሃግብር ተሸኝተል። የስፔሻል ኦሊምፒክ ብሔራዊ ቡድኑ ከስድስት ወር በፊት በተደረገ ሀገር አቀፍ ውድድር የተመረጠ ሲሆን በዘንድሮ ኦሊምፒክ በአትሌቲክስ በተለይም በአጭር ርቀት፣ሪሌይ(ዱላ ቅብብል)ና ርዝመት ዝላይ በዋናነት ይሳተፋል፡፡ ቡድኑ በአትሌቲክስ ስፖርት ምድብ በአራት አትሌቶች (ሚሊዮን ያደታ፣ ኪሩቤል ንጉሴን፣ ጊፍቲ ገረመው እና ኤደን ተስፋዬ) ተወክሏል። ቡድኑ ጥሩ እንቅስቃሴ ለማድረግ እና የተሻለ ሜዳሊያ ውጤት ለማምጣት ጥሩ ዝግጅት ማድረጉም ተጠቁሟል።

የዓለም ስፔሻል (ልዩ) ኦሊምፒክ በየሁለት ዓመቱ የሚካሄድ ሲሆን የአዕምሮ እድገት ውስንንነት ያለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን ያሳትፋል። ውድድሩ የአዕምሮ እክል ያለባቸው ስፖርተኞች ችሎታቸውን ለማሳየት የሚያስችላቸው መድረክ ይፈጥራል ተብሎ ነው የሚካሄደው። ይህም የአካል ጉዳተኞች አካታችነት ለማበረታታት እና የአዕምሮ እድገት እክል ያለባቸውን ስፖርተኞች ችሎታ ለማሳደግ ይረዳል ተብሎ ታምኖበታል። ስፔሻል ኦሊምፒክ የአእምሮ እክል ላለባቸው ስፖርተኞች በተወዳዳሪ ስፖርቶች እንዲሳተፉ፣ በራስ መተማመን እንዲፈጥሩ እና ማህበራዊ ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ ልዩ መድረክ ይፈጥራል። ፉክክሩ ደስታን እንዲለማመዱ፣ ጓደኛ እንዲያፈሩ እና የባለቤትነት ስሜት እንዲሰማቸው አጋጣሚን ይፈጥርላቸዋል ተብሎም ይታሰባል።

የኢትዮጵያ ቡድን በዓለም ስፔሻል ኦሊምፒክ መሳተፉ ሀገሪቱ የአካል ጉዳተኞችን ማካተት እና የአዕምሮ እክል ያለባቸውን ስፖርተኞችን ለመደገፍ ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ እንደሚሆን ተጠቁሟል። ይሁን እንጂ በውድድሩ የሚሳተፉ ስፖርተኞች የበለጠ ድጋፍና ትኩረት ሊሰጣቸውና ተሳትፋቸው ሊጨምር ይገባል፡፡

የኢትዮጵያ ቡድን አዳዲስ እና ነባር አትሌቶች አዋህዶ የያዘ ሲሆን በውድድሩ ላይ ውጤት ያስመዘግባል ተብሎ ይጠበቃል። ስፖርተኞቹ በዚህ ውድድር ላይ ለመሳተፍ ያጋጠሟቸው ፈተናዎች ቀላል እንዳልሆኑ አገር አቀፍ ኮሚቴው አስታውሳል፡፡

እንደ ስፔሻል ኦሊምፒክ ያሉ የስፖርት ተሳትፎዎች የማህበረሰብን ስሜት ለማዳበር እና የስፖርትን የመለወጥ ሃይል ለማጉላት ይረዳሉ። የኢትዮጵያ ስፔሻል ኦሊምፒክ የልዑካን ቡድን በዓለም ልዩ ኦሊምፒክ መሳተፉ ለአገሪቱ እና ለአትሌቶቹ ትልቅ ምዕራፍ ነው። በውድድሩ ላይ ሲሳተፉ ማክበርና ማበረታታት ይገባል። የአዕምሯዊ ውስንነት ላለባቸው ስፖርተኞች ሁሉን አቀፍ ሁኔታዎችን እና እድሎችን መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን ማጉላት፣ የአካል ጉዳተኝነትን፣ ማካተትን ማስተዋወቅ እና የሁሉንም ስፖርተኞች አቅም የማጎልበት ጉዳይ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

የስፔሻል ኦሊምፒክ የአዕምሮ እክል ያለባቸውን ስፖርተኞች በተመለከተ ቀድሞ የግንዛቤ ስራ መስራት ስፖርቱን ለማሳደግ ይበልጥ እድል ከመሰጠቱም በላይ የአዕምሮ እክል ያለባቸው ስፖርተኞች በስፖርት ውስጥ የመሳተፍ እና ንቁ የአኗኗር ዘይቤን የመምራት መሰረታዊ መብት ያጎናፅፋል ተብሎ ይታመናል፡፡



**በስፔሻል ኦሊምፒክ ኢትዮጵያን የሚወክለው ቡድን በርሊን ሲደርስ አቀባበል ተደርጎለታል፣**


## የጨረታ ማስታወቂያ

በዞናችን የደቡብ ምዕ/ሸዋ ዞን ማረሚያ ቤት መምሪያ ከሀምሌ 1/2015 እስከ ታህሳስ 30/2016 ድረስ ለ 6 ወር የሚቆይ በስሩ ለሚያስተዳድራቸው ለህግ ታራሚዎች የበሰለ ምግብ ለሚያቀርቡ በጥቃቅንና አነስተኛ ለተደራጁ ማህበራትም ሆኑ ግለሰብ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ድርጅቶችና ነጋዴዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መመሪያ ማሟላት አለባቸው፡፡ በንግድ ዘርፍ በዘመኑ የታደሰ የንግድ ፍቃድ የአቅራቢዎች ምዝገባ የምስክር ወረቀት ወቅታዊ የግብር ግዴታቸውን የተወጡ ለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡

1. ተጫራቾች የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም የቫት ከፋይነት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
2. የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 50 (ሃምሳ ብር) በመክፈል ይህ ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በስራ ሰዓት ከዞኑ ማረሚያቤት ጽ/ቤት ከቢሮ ቁጥር 3 መግዛት ይችላሉ፡፡
3. ተጫራቾች የሚያቀርቡት የዋጋ ማቅረቢያ በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ በዞኑ ማ/ቤት ጽ/ቤት ለዚሁ በተዘጋጀ የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያው 2% በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ የተመሰከረ ቼክ (CPO) ከጨረታው ሰነዱ ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. በጥቃቅንና አነስተኛ ለተደራጁ ማህበራት የበሰለ ምግብ ለማቅረብ ፍቃደኛ ሆነው ለሚቀርቡት ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡
6. የጨረታ ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለተከታታይ 15 ቀናት ቆይቶ በ16ኛው ቀን ከረፋዱ 4፡00 ሰዓት ላይ ተዘግቶ በዚሁ ሰዓት ዕለት ከረፋዱ 4፡30 ሰዓት ላይ ተወዳዳሪዎች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው የህግ ታራሚዎች ኮሚቴ የመስሪያ ቤቱ ኮሚቴ እና ከዞን ፋይናንስና አቃቢ ህግ ቢሮ በሚወከሉ በተገኙበት ጨረታው ይከፈታል፡፡
7. ምግቡ የሚዘጋጀው በመስሪያ ቤቱ ማብሰያ ውስጥ ሆኖ ለማብሰያ የሚያገለግሉ ዕቃዎች የማረሚያ ቤቱ እንዳለ ሆኖ የጎደለውን ጨረታውን ያሸነፈው ማህበራት ወይም ግለሰብ የማሟላት ግዴታ አለበት፡፡
8. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።
9. ጨረታው የሚከፈትበት ቀን መስሪያ ቤቱ ዝግ ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን ይሆናል፡፡

**አድራሻ፡- የደ/ም/ሸ/ዞን ማ/ቤት መምሪያ ወሊሶ ከተማ**

**ለበለጠ መረጃ ስልክ ቁጥር፡- 011-341-11-90/ 011-341-00-23**

**የደቡብ ምዕ/ሸዋ ዞን ማረሚያ ቤት**



## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክ/ከ ወረዳ 03 የቤት ቁጥር አዲስ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0005593464 ሰላማዊት ሀይለስላሴ እቁባእግዚ ከተመዘገብኩበት ቦሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት ደረሰኝ የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) የእጅ በእጅ ሽያጭ ከቁጥር 001 እስከ 0050 የተሰራበት እና ከቁጥር 00101 እስከ 00250 ያልተሰራበት የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል። ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ቦሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ሰላማዊት ሀይለስላሴ እቁባእግዚ**



## በድጋሚ የወጣ ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

በአፈጻጸም ከሳሽ ዝናቡ በዛ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ እና በአፈጻጸም ተከሳሽ የቆቦ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መካከል ስላለው የአፈጻጸም ክስ ክርክር ጉዳይ የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ደሴ ምድብ ችሎት ግንቦት 25 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ መሰረት የአፈ/ተከሳሽ የቆቦ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ንብረት የሆነ በሰሜን የአፈጻጸም ተከሳሽ መዋዕለ ህጻናት እና የመሰብሰቢያ አዳራሽ፤ በደቡብ የወንዶች ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የገበያ ማእከል፣ በምስራቅ መንገድ እና በምዕራብ የአፈጻጸም ተከሳሽ መኖሪያ ቤት የሚያዋስኑት በቆቦ ከተማ 04 ቀበሌ ክልል ውስጥ የሚገኝ 48 × 24 ሜትር ስፋት ላይ ያረፈ ግንባታው ያልተጠናቀቀ ህንጻ ያለምንም መነሻ ዋጋ በጨረታ እንዲሸጥ ትእዛዝ የሰጠ ስለሆነ እና ከፍተኛ ዋጋ የሰጠ የጨረታው አሸናፊ የሚሆን በመሆኑ ማንኛምው መጫረት የሚፈልግ አካል ሃምሌ 16 ቀን 2015 ዓ.ም ቆቦ ከተማ 04 ቀበሌ ህንጻው ከሚገኝበት ቦታ ላይ ከጠዋቱ 3፡00 ላይ በመገኘት የግልጽ ጨረታ ተሳታፊ መሆኑን የምትችሉ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**ማሳሰቢያ፡-**

* ጨረታው 3፡00 ሰዓት ላይ ጀምሮ 6፡00 ሰዓት ላይ ይጠናቀቃል፡፡
* በጨረታው የሚሳተፍ ማንኛውም አካል የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ይዞ መገኘት አለበት፡፡
* ጨረታውን የሚያሸንፍ አካል ያሸነፈበትን የብር መጠን 1/4ኛ ወዲያውኑ በባንክ ያሲዛል፡፡

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ**
**ፍ/ቤት ደሴ ቋሚ ችሎት**